# ስለ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አንዳንድ ነጥቦች

(ለአውሮጳ የኢዴሃህ ድጋፍ ኮሚቴዎች ለውይይት የቀረበ የውስጥ ሰነድ)

07/06/2007

## <u>መግቢያ</u>

ህብረታችን በግንቦት 97 ምርጫ ሲሳተፍ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ነፃ ምርጫ ይቻላል ከሚል አጉል ህልም ተነስቶ አልነበረም። ዴሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነበት አካባቢ ነፃ ምርጫ አይቻልም ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት የተሳተፈው አላማ በምርጫ ዘመቻው ሳቢያ ሚልዮኖችን አንቀሳቅሶ ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ቀጣይ ህዝባዊ ትግል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር። ይህ ስትራቴጂ በግንቦት ሳቢያ ታሪካዊ ተልእኮውን አከናውኗል። እንዲያውም ከግንቦት ድሎች እንደ መሰረታዊ ሆኖ መቆጠር የሚኖርበት ይህ "ምርጫ ከዴሞክራሲ ይፈልቃል እንጅ ድሮውንም የሌለ ዴሞክራሲ ከምርጫ አይመጣም" የሚለውን ሃቅ ሚልዮኖች እንዲጨብጡት ማስቻሉ ነው። ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንዳንድ ታማኝ ተቃዋሚዎች "ከምርጫ ምርጫ እየተሳተፍን ከምርጫ ምርጫ በሃገሪቱ ያለው ዴሞክራሲ አድማስ እየሰፋ አንድ ቀን የተሟላ ዴሞክራሲ ይሰፍናል" የሚሉት ልፈፋ በግንቦት ድልና በድሉ ማግስት በተከሰተው ቀውስ ምክንያት ታልፎ የሄደና የተያዘው ቅልበሳ አሳሳቢነት ያልገባው ስትራቴጂ ነው።

በኢህአዴግ መሪዎች እየተተከለ ያለው የሽብር አገዛዝ ከአንድ ከማንኛውም ፀረ ዴሞክራቲክ ሃይል ሊጠበቅ የሚችል "አዘቦታዊ" የምንለው የአፈና ሂደት አይደለም። የግንቦት ድሎች ቅልበሳ ስንል የዚህ ዋና ገፅታ ባለፉት አስራ አምስት አመታት ቀስ በቀስ ታጋይ ዜጎች እየሞቱ፤ እየታሰሩ፤ እየተሰደዱ የገነቧቸውንና የወያኔ/ኢህአዴግን መሪዎች ለሽንፈት የዳረጓቸውን ውሱን የነበሩትን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትንና ግኝቶች እንኳን እንዳልነበሩ አድርጎ ለማውደም የሚደረገው ሙከራ ነው። እርግጥ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር የተሟላ ዴሞክራሲ ኖሮ አያውቅም። ነገር ግን የኢህአዴግ መሪዎች ካሉበት የኪሳራ ደረጃ አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ " የተሟላ ዴሞክራሲ " ሳያስፈልገው በቅድመ ግንቦቱ ወቅት በነበረችው የዴሞክራሲ የፍንጭ ፍንጭ ተጠቅሞ በፀረ ህዝቦቹ ላይ የማያወላዳ ድል ለመጎናፀፍ በቅቷል።

የኢህአዴግ መሪዎች ከዚህ "የበኩላቸውን" ትምህርት ቀስመዋል። ገና በእንጭጩ የነበረው የዴሞክራሲ ሂደት ምን ያህል ኪሳራ እንዳደረሰባቸው ተገንዝበዋልና ከእንግዲህ እነዚህ ቀልባሾች በህዝብ ትግል ከመንበርከካቸው በፊት እንደ ዳኝነት ነፃነት፤ የህግ የበላይነት፤ ነፃ ምርጫ፤ ተጠያቂነት ወዘተ የመሳሰሉትን "ከባድ ከባድ" እሴቶች ቀርቶ በቅድመ ግንቦት የነበሩት የዴምክራሲ ፍንጮች እንኳን ተመልሰው እውን እንዲሆኑ አይፈቅዱም። ከዚህ ሁኔታ እኛም የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች የበኩላችንን ትምህርት እንቅሰም ካልን የቅልበሳውን አሳሳቢነት ሳንክድና ስለቀልባሾቹን ቁርጠኝነት በምንም ሳንዘናጋ ስለቀጣይ ምርጫ፤ ስለድርድር፤ ስለ ብሄራዊ እርቅ ከአጉል ልፈፋ ተቆጥበን በቅድሚያ እነዚህን ግኝቶች በመንከባከብ፤ በማስመለስና በነሱ ላይ በመገንባት ላይ ያተኮረ ቁርጠኛ ተጋድሎ ማካሄድ ይኖርብናል ማለት ነው። ህብረታችን ለዩክሬክት ጉባኤ ባዘጋጀው ሰነድ የዚህ አይነቱን የትግል አጀንዳ ወሳኝነት በጠቆመበት ክፍል፤

*" ዛሬ በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ትግል ማንም የፖለቲካ ሃይልም ሆነ ስብስብ የሚያወጣው ስትራቴጂ በአጥፊነትም ሆነ በአልሚነት የሚመዘነው ከነዚህ ድሎች አንፃር በሚወስደው አቋም ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ህልማቸው የህዝብ ድምፅ ሰርቀው ለሌላ አምስት አመት በስልጣን ላይ ለመቆየት ብቻ የሚጥር ህልም አይደለም። ዛሬ በአይናችን ስር እየተካሄደ ካለው ዘግናኝ የሽብር ውርጅብኝ ባሻገር ሙከራቸው ህብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ብቁ ያደረጉትን በመስዋእትነት የተገነቡ እነዚህን ተቋማት በማፈራረስና በህዝባችን ስነ ልቡና የሰረፁትን በጎ ያስተሳሰብ ለውጦች በማውደም የዛሬ ሃያም ሰላሳም አመት የነበረውን " የሽግግር ክፍተት" መልሶ እውን ለማድረግ የሚጥር መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ ነው።"* በማለት የቅልበሳውን አላማና አሳሳቢነት ብቻ ሳይሆን የሃገራችን ዴሞክራቶች ከዚህ አንፃር መከተል ስላለባቸው ስትራቴጂ ያለውን ሃሳብ ሰንዝሯል።

ከዚህ አንፃር ስናየው ዛሬ ተቃዋሚ ነኝ በሚለው ጎራ ይህንን " ከኢህአዴግ አመራር በህዝብ ትግል ተገዶ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት ከመከፈቱ በፊት ምርጫ ትርጉም የለሽ ነው " የሚለውን ለቀጣዩ ትግል ወሳኝ የሆነ ግንዛቤ

የማድበስበስና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ትብብር በድርድርነር ብሄራዊ እርቅ አማካኝነት ስለ ቀጣይ ምርጫና ስለዴሞክ
ራሲ ''ቀስ በቀስ መገንባት'' ብዙ እየተለፈፈ እናያለን። በኛ በኩል በዚህ ጉዳይ ከወዲሁ በጣም ግልፅ የሆነ አቋም ይዘ
ን መራመድ ይኖርብናል። በምንም ምክንያት ይሁን በምን የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች እዚህ ወጥመድ ውስጥ ገ
ብተውና የግንቦትን የትግል ምእራፍ ዘግተው በወያኔ/ኢህአዴግ ስር፤ በወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ፤ በተኮላሸና 'መ
ስመር በገባ' ፕሬስ፤ በስነ ስርአት አድማቂነት በሚሰለፉ ''ተቃዋሚ'' ድርጅቶች ተሳትፎ የሚደረግ ምርጫ ተብየ ነገር
የግንቦት የቀብር ስነ ስርአት ሙከራ እንጂ ሌላ ትርጉም ስለማይኖረው የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች በአለ በሌለ ሃይላቸው
ህዝባችንን ይዘው ሊቋቋሙት ይገባል እንላለን።

በመሆኑም ዛሬ የተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የ
ትም የማያደርስ የተናጠል ትግላቸውን ''ለማፋፋም'' ላይ ታች የሚሉበት፤ ወይም ደግሞ ወገናዊ አጀንዳቸውን ለማራመ
ድ የሚሰሩበት፤ ወይም ደግሞ በህዝብ ፊት ተወዳድረው ስልጣን ለመጨበጥ የሚያካሂዱት ተራ የምርጫ ዘመቻ አይደ
ለም። ከእንግዲህ የሚደረገው ትግል ምንም አይነት ምርጫ ከመታሰቡ እንኳን በፊት ይህንን ግንቦት ትቶ የሄደውን ግ
ንዛቤ በመስዋእትነት የጨበጡትን ሚልዮኖች ይዞ ለነፃ ምርጫ አስፈላጊ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለማምጣት የ
ሚደረግ ትግል ነው። በመሆኑም ትግሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በህብረተሰባችን የዴሞክ
ራሲ እጣ ፈንታ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች በሙሉ በጋራ የሚሳተፉበት የዴሞክራታይዜሽን ትግል ነው። ህብረታችን የሁ
ሉን አቀፍ ጉባኤ ሃሳብ አፍልቆ ሲታገል የቆየው ይህ የጋራ ትግል ግልፅና ቀላል የሆነ አጀንዳ የሚጨብጥበትንና ለዚህ
አጀንዳ ታግሎ የሚያታግል የትግል አመራር መድረክ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።

## <u>1ኛ. ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ስንል</u>

በአንዳንድ አካባቢዎች ''ሁሉን አቀፍ ጉባኤ'' ስንል ግራ በመጋባትም ይሁን ሆን ብሎ ነገሩን ለማጣጣል ''ኢህ
አዴግ እያለ እንዲህ አይነቱ ጉባኤ ሃገር ውስጥ ሊደረግ አይችልም።'' የሚል አነጋገር ይሰነዛራል። ከወዲሁ ግልፅ መሆ
ን ያለበት ዛሬ ባለንበት ሁኔታ የምናወራው ስለሁለት ጉባኤዎች መሆኑ ነው። አንደኛውና የትግሉ ወሳኝ ምእራፍ የሚሆ
ነው በዚህ ህዝባዊ ተጋድሎ የኢህአዴግ መሪዎች እንዲያፈገፍጉ ከተገደዱ በኋላ በሃገራችን ምድር የሚሰየመው ሁሉን
አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ሸንጎ ወይም ጉባኤ እንደሚሆን በተደጋጋሚ በህብረታችን ተጠቁሟል። የዚህ ሁሉን አቀ
ፍ ጉባኤ ተሳታፊዎቹም ሆኑ ተግባራቱም በህብረታችን አማራጭ ፕሮግራምና በተለያዩ ሰነዶች ተዘርዝረው ተቀምጠዋል
። ሁለተኛው ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ለሚደረገው ትግል አስተዋፅኦ ለማድረግ በሁኔታው አስገዳጅነት በውጭ አገር የምን
ጠራውና የጋራ ትግል ስትራቴጂና መዋቅር ዘርግቶ ትግሉን ፈር ለማስያዝ የሚሰራ ጉባኤ ነው። አሁን እዚህ ላይ አንዳን
ድ ሃሳቦች የምንሰጥበት ስለዚህ በውጭ ስለሚደረገው ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ነው።

ተሳታፊዎቹ እነማን ናቸው? ኢዴሃህ በእንዲህ አይነቱ ''ሁሉን አቀፍ'' የሆነ ጉባኤ ስለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍ
ሎች ሲያብራራ ተሳታፊዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች፤ የወጣቶችና የሴቶች፤ የሰራተኞችና
የገበሬዎች፤ የነጋዴዎች፤ የጋዜጠኞች፤ የሙያ፤ የጥቅም፤ የባህል፤ የምሁራንና የባለሙያዎች ማህበራትና ስብስቦች ተ
ወካዮች፤ የሃይማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሎች እንደሚሆኑ በተደጋጋሚ አስታውቋል። በውጭ ሊጠራ በሚታሰበው
ሁሉን አቀፍ ጉባኤ እነዚህ ሁሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ሊወከሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንደሌለ ግልፅ ነ
ው። ሆኖም ከዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ የሚፈልቀው የትግል ስትራቴጂ የተሟላና ሁሉን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያንቀ
ሳቅስ ስትራቴጂ መሆን እንደሚኖርበትም የዚያኑ ያህል ግልፅ ይመስለናል። በመሆኑም ይህንን ጉባኤ ለማዘጋጀት ሃላፊነ
ቱን የሚወስዱ ወገኖች ሊወከሉ ያልቻሉ (ለምሳሌ እንደ ገበሬዎች፤ ስራ አጦች፤ ጎዳና ተዳዳሪዎች፤ የኤችአይቪ ኤይ
ድስ በሽተኞች ወዘተ....) በነዚህ መስኮች ተመክሮና የአማራጭ መፍትሄ ያላቸው ምሁራንም ሆኑ መያዶች የሚወከሉበ
ትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል። ይህ በውይይት መፍትሄ የሚገኝለት ቀላል ችግር ይመስለናል።

ዋናው ከፊታችን የተደቀኑት ሁለት የተያያዙ ችግሮች ይመስሉናል። ምንም እንኳን በተቃዋሚው ጎራ በዚህ ጉ
ባኤ አስፈላጊነት ላይ ላዩን ''አጠቃላይ ስምምነት'' ያለ ቢመስልም ወደ ተግባር ለመሸጋገር ያላስቻሉት ለሁለት የተያያ

ዙ ጥያቄዎች ግልፅና የጋራ መልስ መስጠት ባለመቻላችንን ብቻ ሳይሆን በነዚህ ነጥቦች ላይ ይፋና ግልፅ የሆነ ውይይት
ለማድረግ አለመቻሉ ይመስለናል። የመጀመሪያው ጥያቄ በአጠቃላዩ ሂደት ከፖለቲካ ውጭ ያሉት ከፍ ብለን የጠቀስና
ቸው ስብስቦችና ወገኖች በአጠቃላዩ ሂደት ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና ግልጥልጥ ያለ አቋም የመያዝ ወይም ያለመያዝ
ጥያቄ ይመስለናል። ሁለተኛው ጥያቄ ወደዚህ ወሳኝ የሆነ የሽግግር ጉባኤ የምንሄደው እንዴት ነው. የሚለው ጥያቄ ነው
። ከኢህአዴግ ጋር በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ አማካኝነት ተደራድሮ ወይስ እንደ ነፃ ምርጫ፤ እንደ ዴሞክራሲ ወዘተ በህዝ
ባዊ ትግል መጀመሪ የኢህአዴግ መሪዎች እንዲያፈገፍጉ በማድረግ?

እኛ የምንለው ምንድን ነው? ስብስቦች ሁሉም በሚስማማበት በዚህ ጉዳይ ወደ ተግባር ለመሄድ በተቃዋሚው
ጎራ (እንደኛ በአጠቃላዩ ሂደት የነዚህ በአንድ በኩል ነው ችግር እነዚህ ከፖለቲካ ውጭ ያሉ የጉባኤው ታዳሚዎች
በአጠቃላዩ ሂደት ስለሚኖራቸው ሚና ያሉት አንዳንድ አለመግባባቶች ናቸው። በአንድ በኩል እንደ ህብረታችን ከል
ብ ባያምኑበትም ሌሎችም የዚህ ሁሉን ያካተተ ጉባኤ ጉዳይ የሚቀፋቸውም ወገኖች ( ሲቪል ሶሳይቲ የሚሉትን ነገር
ከጦር የሚፈሩት የትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ አባል ድርጅቶች ጭምር) እንዲህ አይነቱን ጉባኤና እንዲህ አይነቱን
ተሳትፎ አፍ ሞልተው አይቃወሙም። እስካሁን እንደታዘብነው ከሆነ በዚህ ጉዳይ ያለው ትልቅ ልዩነት በኛ በኩል እ
ነዚህን ተሳታፊዎች ከኛው እኩል የትግሉ ባለቤትና ወሳኝ አካል አድርገን በመቁጠር ከወዲሁ ይህ ጉባኤ እውን እንዲ
ሆን በሚደረገው ጥረት በአመራርም ደረጃ መሳተፍ ይኖርባቸዋል የሚል አቋም አለን። የሌሎቹ አካሄድ ቅድሚያ የሚ
ሰጠው የፖለቲካ ድርጅቶች ያደርጋሉ ስለሚባለው "ትግል" ነው። በዚህ አስተሳሰብ መሰረት ለዴሞክራሲ የሚደረገው
የፖለቲካም፤ የዲፕሎማሲም ሆነ ሌላ ትግል በፖለቲካ ድርጅቶች አመራር ተካሂዶ ከዚያ በሃገራችን ዴሞክራሲ ሲሰ
ፍን ይህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ይደረጋል። ያኔ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በዚህ ጉባኤ ላ
ይ "በተጋባዥነት" ይገኛሉ የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። ኢዴሃህ የእንዲህ አይነቱን ጠባብ አካሄድ አደገኛነት ሲ
ጠቁም ለዩክሬክቱ ጉባኤ ባዘጋጀው ሰነድ፤

*" ካለፉት ሂደቶች ተምረን ወደ ፊት እንራመድ ካልን ከወዲሁ መቀበል የሚኖርብን አንድ መሰረታዊ ሃቅ አለ
። ህብረተሰባችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሸጋገር በሚደረገው ትግል የፖለቲካ ድርጅቶች ወሳኝ የሆነ የግንባር
ቀደምነት ሚና ቢኖራቸውም የተጋድሎው አልፋና ኦሜጋ እነሱን ብቻ አድርጎ መውሰድ ሌላ ታሪካዊ ስህተት ይሆናል
።"* ካለ በኋላ ከዚህ ይልቅ በሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች
በሁሉን አቀፍ ጉባኤ አማካኝነት በተራ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በአመራርም ደረጃ በትግሉ የሚሳተፉበት ሰፊ አገራዊ መ
ድረክና ታግሎ የሚያታግል አካል ማቋቋም የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ እንደሆነ ጠቁሟል።

የጉባኤው ተግባራት ምን ይሆናሉ? በዚህ ጉዳይ ከወዲሁ ዝርዝር መግባት አይቻልም። ግን አንድ ጉባኤ አብሮ
ለመጥራትና የጋራ ትግል አጀንዳና የዚህ ትግል አቀነባባሪ አካል ለመፍጠር ስንነሳ "ለጋራ ትግል" ብለን የሆነ ያልሆነው
ን እንደማንቀበል ከወዲሁ ግልፅ መሆን ያስፈልጋል። ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚባለው ስብስብ ውስጥ ኢዴሃ
ህ ላለመግባት የመረጠው የጋራ ትግል ጠልቶ አይደለም። ዋናው ያልገባበት ምክንያት ህብረቱ ከዚህ ስብስብ መስራቾ
ች ጋር በትግሉ አጀንዳም ሆነ በትግሉ ዘዴ መሰረታዊ ልዩነት ስለነበረው ነው። አሁንም ቢሆን እነዚህ በጉባኤው ላይ
ይገኙ የምንላቸው ሃይሎች በእርግጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው እስካልን ድረስ ከዚህ ጉባኤ ስለሚፈል
ቀው የጋራ ትግል አጀንዳና ይህንን አጀንዳ በተግባር ለመተርጎም ስለሚጠብቀን ተግባር ከነሱ መክረን የምንወስነው ቢ
ሆንም የኛን አቋምና አካሄድ ከወዲሁ ለውይይት በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርብናል። በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ህብረቱ ስለ
ሚያራምደው አቋም በግልፅ መቀመጥ ያለባቸው ሶስት ቁም ነገሮች አሉ።

አንደኛ የጋራ ትግል ካልን የጋራ የሆነ ህዝባዊ አጀንዳ መጨበጥ ይኖርብናል። ይህ ህዝባዊ አጀንዳ ደግሞ በኛ
በኩል በተደጋጋሚ እንዳልነው የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በእነሱ ላይ መገንባት፤ መስመር የሳተውን የዴሞክራታይዜ
ሽን ሂደት መልሶ በእግሩ ማቆም የሚለው አጀንዳ ነው። የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በነሱ ላይ መገንባት ማለት ከእን
ግዲህ በኢህአዴግ አመራር ስር ምርጫ ብሎ ነገር ለፀረ ህዝቦች አገዛዝ ህጋዊ ሽፋን ከመስጠት ሌላ ምንም የሚፈይደ
ው ነገር የለም የሚለውን ሚልዮኖች በከባድ መስዋእትነት ያገኙትን ግንዛቤ አንግበን በዚህ አጀንዳ ተንቀሳቅሶ ማንቀሳ
ቀስ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሁለተኛ የሚልዮኖችን ድል የማስመለሱ ጉዳይ ከኢህአዴግ አገዛዝ ለህዝብ ፈቃድ መገዛት በፊት እውን ሲሆን እንደማይችል ተገንዝቦ ይህንን አጀንዳ ለማራመድ ሚልዮኖችን የሚያንቀሳቅስ ህዝባዊ የትግል ማእበል እንደሚያስፈልግ በጣም ግልፅ አድርጎ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይህ ህዝባዊ የትግል ማእበል እንዲንቀሳቀስ ሳንሰራ ከዚያ በፊት የሃገራችንን ችግር በአለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተብየው አጋፋሪነት፤ በህዝብ ትግል ባልታጀበ ድርድር ወይም ደግሞ ''ብሄራዊ እርቅ'' በሚሉ አጓጉል መፈክር ለመተካት መሞከር የለብንም። በመሆኑም ሁሉን አቀፍ የምንለው ጉባኤ አንዱ አጀንዳ የግንቦቱ ህዝባዊ የትግል ማእበል መልሶ ስለሚቀሰቀስበት ሁኔታና ስትራቴጂ የሚመክርና የሚወስን ጉባኤ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው።

ሶስተኛ በህዝባዊ አጀንዳና ህዝባዊ ትግል ስንል ይህንን በተግባር ለመተርጎም የሚያስችል ከፖለቲካ ድርጅቶች እጅግ የሰፋ ''ህዝባዊ አመራር'' ያስፈልጋል ማለት ነው። ይህንን መሰረታዊ እውነታ ባለመቀበል እኛ ትግሉ በጠቅላላው በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የጋራ ትግል ነው ስንል የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ አድርገው የሚያዩ፤ ይህ አልበቃ ብሎ ደግሞ ከፖለቲካ ድርጅቶች እንኳን ''የኛ ብቻ''' ነው በሚል አጉል አቅጣጫ የተሰማሩ ወገኖች እንዳሉ እየታዘብን ነው። እነዚህ ወገኖች እርግጥ የኢትዮድያ ህዝብ ''እንደ አንድ ሰው'' ሆኖ እንዲነሳ በተደጋጋሚ ጥሪ ያደርጋሉ። ነገር ግን ይህ ጥሪያቸው ''እንደ አንድ ሰው ሆነህ ከኛ ጀርባ ተሰለፍ'' የሚል እጅግ ጠባብና አስገራሚ ጥሪ ነው። በኛ እምነት የዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አላማ ይህንን ህዝባዊ አጀንዳ አንግቦ ለሚንቀሳቀስ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ''ሁሉን አቀፍ'' አመራር የምንሰይምበት ጉባኤ መሆን ይኖርበታል።

በዚህ መልክ ''ለህዝባዊ አጀንዳ፤ ህዝባዊ ትግል፤ በህዝባዊ አመራር'' ብለን አቋማችንን ብንሰነዝርም ''የኛ አቋም ይኸ ነው፤ በዚህ የማይስማሙ ሃይሎች በዚህ ጉባኤ ላይ መገኘት አይችሉም'' የሚል ፀረ ዴሞክራቲክ አቋም ማስተጋባት የለብንም። ከዚህ ውጭ ሌላ አካሄድ አለን የሚሉ የፖለቲካም ሆኑ የሲቪክ ድርጅቶች ከዚህ የተለየ ሃሳባቸውን ይዘው ለመከራከር በጉባኤው እንገኝ ካሉ የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል። ሆኖም በዚህ ጉባኤ ዝግጅት ወቅት በኛ በኩል ይህ ህዝባዊ፤ ዴሞክራሲያዊና አገራዊ አካሄዳችን በሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ዘንድ ሰፊ የሆነ ተቀባይነት እንዲያገኝ በፅሁፍም ሆነ በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት በሰፊው ተንቀሳቅሰን የነዚህን ወገኖች አጉል አካሄድ መታገልና እስካሁን የያዙትን ሸሸት ትተው በህዝብ ፊት እንዲከራከሩ ማስገደድ ይኖርብናል።

## 2. አካሄዳችን በተጨባጭ

ይህንን የሁሉን አቀፍ ጉባኤ ሃሳብ የሚደግፉ ዜጎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቢሆኑም ኢዴሃህ ይህንን ሃሳብ አንስቶ ለዚህም እውንነት አንድ ''የቀውጢ ጊዜ ግብረ ሃይል'' እንዲቋቋም በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። ሆኖም ይህ ጥሪያችን እስካሁን ድረስ እውን እንዳልሆነም የዚያኑ ያህል ግልፅ ነው። በሶስተኛው አስቸኳይ ሸንጎ በዚሁ ጉዳይ እንደገና ጥሪ አድርገን ለዚያውም የራሳችን የሆነ ግብረ ሃይል ስንፈጥር ይህ የዛሬው አካሄድ ካለፉት የሚለየው በሁለት ነገሮች ነው። አንደኛ እንደ እስካሁኑ የዚህን ጉባኤ ዝግጅት ጉዳይ ''ሌሎች ይዘውታል'' ብለን ለነሱ ብቻ መተው ሳይሆን ራሳችን ኢኒሸቲቩን ወስደን እስከመጨረሻው እንድንገፋበትና ሁለተኛ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ይህ ሃሳብ በኢትዮድያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች አካባቢ ሰፊ ድጋፍ እንዳለው በመገንዘብ ''ሁሉም እስኪስማማ'' ከሚል አባዜ ተላቀን በዚህ ሃሳብ ከሚስማሙ ወገኖች ጋር ወደፊት ለመራመድ ወስነናል።

ይህ ማለት በቅድሚያ ከዚህ በፊት በጉዳዩ ''ኢንተረስት'' ያሳዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን፤ የሲቪክ ማህበራት መሪዎችንና ታዋቂ ግለሰቦችን ተገናኝቶ በተቻለ ፍጥነት በጉዳዩ ላይ ውይይት መክፈት ማለት ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ በአሜሪካ ተጀምሯል። በዚህ በአውሮፓም በኩል ይህ ስራ ባፋጣኝ መልክ መያዝ ስላለበት በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ውይይት ተደርጎ ወደፊት መራመድ ያስፈልጋል።

1. አካሄዳችን ራሳችንን እንደ ጉባኤ አዘጋጅና ሌሎችን ወገኖች እንደ ''ተጋባዥ'' አድርጎ መውሰድ የለበትም። ጉባኤው ላይ ይሳተፉሉ ከምንላቸው የፖለቲካና የሲቪክ ማህበራት መሪዎች፤ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ ቢያንስ ከላይ እ

ንደተባለው ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ኢንተረስት ካሳዩት መሃል ዋና ዋናዎቹ በሂደቱ ውስጥ ገና ከጥንስሱ እንዲሳተፉ በጣም መምከር ያስፈልጋል። በዝግጅቱ ጉዳይ ማንኛውም ቅስቀሳም ሆነ ሌላ ይፋ የሚሆን ነገር የሚደረገው ቢያንስ ቢያንስ ከህብረቱ ሰፋ ብሎ ሌሎች በተካተቱበት አካል መሆን ይኖርበታል።

2. ባለፈው ውይይታችን እንደተስማማነው ለዚህ ስራ በየሃገሩ ራሳቸውን የቻሉ ኮሚቴዎች ማቋቋም አስፈላጊ አይሆንም። ሁሉም በየሃገሩ ያለ የድጋፍ ኮሚቴ አባል በስራው መሳተፍ ሲኖርበት ይህንን ለማቀነባበር አንድ ሰው በሃላፊነት እንዲመደብ/እንድትመደብና የእነዚህ ሃላፊዎች ስም በአስቸኳይ እንዲተላለፍ-ን ያስፈልጋል።

3. በዚህ መሰረት በአውሮፓ አገሮች በያለንበት ከጥንስሱ በጉዳዩ በባለቤትነት ሊገቡ ይችላሉ የምንላቸውን ድርጅቶችና ግለሰቦች ሊስት ይዋል ይደር ሳንል አውጥተን እንዲሁ በያለንበት (እንግሊዝ አገር፤ ስዊድን፤ ስዊስ፤ ሆላንድ ወዘተ) ከነዚህ ሰዎች ጋር ስለ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ "የምክክር ስብሰባ" መጥራት ይቻላል። ለዚህ የጊዜ ገደብ በእሁዱ ውይይታችን ላይ እንወስናለን።

4. እነዚህን የምክክር ስብሰባዎች በየሃገሩ የሁሉን አቀፍ ጉባኤ "ስቲሪንግ ኮሚቴ" በማቋቋም መቋጠርና ከዚያ ከነሱ ጋር እንዲህ አይነቱ ኮሚቴ በአውሮዳ ደረጃ ስለሚመሰረትበት አካሄድ በየሃገሩ ያሉ ኮሚቴዎች ተወካዮች በአንድ ፓል ቶክ ወይም ቴሌ ኮንፈራንስ ተገናኝተው የሚወያዩበት መንገድ ማዘጋጀት ይኖርብናል

5. የዚህ ውይይት አላማ ጉባኤውን በተጨባጭ የሚያሰናዳ አንድ እንደ "ሴክሬታርየት" ያለ ቋሚ ግብረ ሃይል ማቋቋም ይሆናል። ይህ ግብረ ሃይል ስለስብሰባው ቦታና ቀን፤ ስለፋይናንስ አቅም ግንባታ፤ የህዝባዊ ግንኙነትና የጉባኤው ዝግጅት በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያስፈልገውን የቅስቀሳ ስራ ያቀነባብራል። ስራውን እንደጀመረ ለዚህ ጉባኤ ከነዚህ ወገኖች ሰፊ የፖለቲካና የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ስለ አላማው፤ ስለ አካሄዱ ወዘተ "ግልፅ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች" የሚል አጭር መልእክት አዘጋጅቶ በሰፊው እንዲሰራጭ ያደርጋል።

6. የህብረታችን አመራር አውሮዳም ሆነ በሰሜን አሜሪካ የሚካሄደው ጉባኤ በተቀላጠፈና ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ እንዲቋጠር (ከዚህ በፊት በፓሪስ ጉባኤዎች እንደተደረገው ሁሉ) የሁለት ሰነዶች ረቂቅ ቢያሰናዳና በቅድሚያ ተሳታፊዎች ከሚወክሏቸው አካላት ጋር ውይይት እንዲያደርጉበት ቢያሰራጭ መልካም ይሆናል። እነዚህ ዶኩሜንቶች አንዱ በአጠቃላይ የትግል አቅጣጫን በተመለከተ ከሰፊ ውይይት በኋላ ስምምነት የምንደርስበት "ሜሞራንደም ኦፍ አንደርስታንዲንግ" ሰነድ አይነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዚህ ጉባኤ ስለሚፈልቀው ሁሉን አቀፍ የትግል አስተባባሪ አካልና በያለበት ለዚህ ትግል ስለሚቋቋሙት የድጋፍ ኮሚቴዎች አሰራርና አወቃቀር ዝርዝር የሚቀመጥበት ሰነድ ይሆናል። ከህብረቱ አመራር ጋር ምክክር ተደርጎ ለነዚህ ሰነዶች አዘጋጅ ግብረ ሃይሎች በቶሎ መመደብና ስራ ተከፋፍሎ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

ከሰላምታ ጋራ
ነገደ ጎበዜ
01/06/07

# ስለ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አንዳንድ ነጥቦች

**ሐ/ ህዝባዊ አመራር**

ሚልዮኖችን እንደገና ወደ ትግሉ ለመመለስ በሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ የመጀመሪያ መጀመሪያ የሚሆነው ተግባራችን ለራሳችንም ሆነ ለታጋዩ ህዝባችን ''የግንቦትን ድሎች ማስመለስ ማለት ምን ማለት ነው?'' የሚለውን ጥያቄ ግልፅና ቀላል በሆነ መልክ መመለስ ያስፈልጋል። የግንቦትን ድል እናስመልስ ማለት የዛሬ ሁለት አመት ምርጫው ተ
ጭበርብሯልና የህዝቡ ድምፅ እንደገና ይቆጠር ማለት አይደለም። በወቅቱ የነበሩት ማስረጃዎች በኢህአዴግ ምርጫ ቦ
ርድ ተዘርፈው ከጥቅም ውጭ በመሆናቸውና በሌሎች በርካታ ምክንያቶች የተነሳ ይህ አይነቱ አካሄድ የሚያዋጣ አይ
ሆንም። የግንቦትን ድሎች ማስከበር ማለት ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታና ከኢህአዴግ ቁጥጥር ውጭ ነፃ ሆኖ በሚሰራ የምርጫ ቦርድ ሌላ ምርጫ ይደረግ ማለት እንደሆነ በነሃሴ ወር 1998 ኢ.ም. የተደረገው የኢዴሃህ ሸንጎ በግልፅ ያሰመረ
ው ጉዳይ ነው። ለዚህ ህዝባዊ አላማ የሚደረገው ትግል ከወዲሁ ይዞ መነሳት ያለበት አንድ መሰረታዊ ግንዛቤ ይኖራል
። ከእንግዲህ በህዝባዊ ተጋድሎ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት ካልከፈትን በሃገራችን እንዲህ አይነቱ ምርጫ የሚካሄ
ድበት ሁኔታ ጨርሶ ሊኖር አይችልም።

ድርጅታችንም ሆነ ኢዴሃህ በዚህ በዴሞክራሲ መስፈንና በነፃ ምርጫ መሃከል ስላለው ዝምድና ያላቸውን ግ
ንዛቤ ደግመው ደጋግመው ገልፀዋል። ከፍ ብለን እንዳልነው ህብረቱ ምርጫው ውስጥ ሲገባ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ነ
ፃ ምርጫ ይቻላል ከሚል አጉል ህልም ተነስቶ አልነበረም። ዴሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነበት አካባቢ ነፃ ምርጫ አ
ይቻልም ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት የተሳተፎው አላማ በዘመቻው ሳቢያ ሚልዮኖችን አንቀሳቅሶ ለዴሞክራሲ ለሚደረ
ገው ቀጣይ ትግል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚል ስትራቴጂ ነበር።

የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በነሱ ላይ መገንባት ማለት ሚልዮኖች በትግልና በመስዋእትነት ባገኙት በዚህ ታሪ
ካዊ ግንዛቤ ተመርኩዞ ከእንግዲህ በወያኔ/ኢህአዴግ አመራር ስር ምርጫ ብሎ ነገር ለፀረ ህዝቦች አገዛዝ ህጋዊ ሽፋን
ከመስጠት ሌላ ምንም የሚፈይደው ነገር እንደሌለ ተገንዝቦ ከማንኛውም የምርጫ ሂደት በፊት በህዝባዊ ተጋድሎ የዴ
ሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት ለመክፈት መታገል ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት መጀመሪያ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስ
ርአት ለመሸጋገር ያስፈልገናል ስለምንለው ''ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ'' ያለንን ሃሳብ አመልክተን ሁለ
ተኛ እንደዚህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊው ትግል ድል መቋጠሪያ የሚሆን ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ከወያኔ/ኢህአዴግ አመራ
ር ለህዝብ ፈቃድ መንበርከክ በመለስ የማይታሰብ ስለሆነ ወደዚህ ድል ስለሚያደርሰን የትግል ጉዞ ያለንን አስተያየት ለ
መሰንዘር እንሞክራለን። (በውጭ ሁሉን አቀፍ - በሃገር ውስጥ ህቡእ)

### አንደኛ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ምንነት፤ አስፈላጊነትና ተግባራት -

መኢሶን ከአምስት አመታት በፊት ''ተሸጋጋሪው ማነው? አሸጋጋሪውስ?'' በሚል ርእስ ባሰራጨው ሰነድ ይህ የጊዜው አ
ንገብጋቢ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉዳይ ከፖለቲካ ድርጅቶችም፤ ከምርጫ ሰሞን ግርግርም፤ ከመንግስት ስልጣን
ቅብብሎሽ ሂደትም አልፎ የሚሄድ ሰፊ አገራዊ አጀንዳ እንደሆነ ሲጠቁም

*''ዛሬ ከለንደኑም ጉባኤ ጉድለቶችም ሆነ ከሃገራችን 'የሽግግሮች' ታሪክ መቅሰም ያለብን ትም-ህርት ሽግግር በ
አመፅ፤ ጊዜያዊ የበላይነትን ያገኘው ወገን የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ህብረተሰቡን እስከ ወዲያ
ኛው 'አሸንፍኩ' በሚልበት ፍጥጫ፤ በአሸናፊና ተሸናፊ መሃከል ወይም ደግሞ በባእዳን አቀነባባሪነትና አስተናጋጅነት '
አሉ' በሚባሉ ጥቂት የፖለቲካ ሃይሎች መሃከል በዝግ ችሎት የሚደረግ የስልጣን ቅብብሎሽ ላይ ማተኮር የለበትም የ
ሚል ትምህርት ነው። ከዚህ ይልቅ ሽግግሩ እስከ ተቻለ ድረስ በስምምነት፤ በ'ኮም-ፕሮማይዝ' እንዲከናወን፤ ሁ-ብረተሰ
ባች-ንም በዚህ የሽግግር ወቅት በእያን-ዳንዱ ቀን ይበልጥ ዴሞክራቲክና ይበልጥ የተረጋጋ መልክ እየያዘ፤ ሁ-ዝባች-ን
በእያንዳንዷ ቀን ይበልጥ ንቁ ተሳትፎ እያደረገና ይበልጥ እየተደራጀ፤ ለመጭ-ው የተሻለ ስርአት ይበልጥ ራሱን እያ
መቻቸ የሚሄድበት የታሪክ ወቅት እንዲሆን መታገል ያስፈልጋል ማለት ነው። ዴሞክራሲያዊው ስርአት በሁሉም ተሳ
ትፎ በሽግግሩ ወቅት ከእለት እለት እየዳበረና ስር እየሰደደ የሚሄድ እንጂ የሽግግሩ ዘመን ሲያከትም 'የሚጀመር' ወይ
ም ደግሞ የሂደቱ መቋጠሪያ መሆን ከሚገባው ምርጫ የሚፈልቅ ስርአት አይሆንም።'* መኢሶን በዚህ ሰነዱ ላይ ሃገራ

ችን የሚያስፈልጋት "የህብረተሰብ ሽግግር" እንደሆነ በግልፅ ካስረገጠ በኋላ እንደዝህ አይነቱ ሽግግር የማን ሃላፊነትና
በማን ላይ የተጣለ አደራ እንደሚሆን በጠቆመበት ክፍል፤

*"ተሸጋጋሪው ህብረተሰባችን እንደአለ እንደ መሆኑ መጠን አሸጋጋሪውም ራሱ ህብረተሰቡ መሆን ይገባዋል እን
ላለን። ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ.....የዚህ የሽግግር ሃላፊነት ለማንም ይሁን ለማን 'ሃገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስር
አት አሸጋግራለሁ' ብሎ ቃል ለሚገባ ጊዜያዊ ይባል የሽግግር፤ ጥምር ይሁን አንድ 'ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ግንባር' ለ
ሚመራው መንግስት የሚተው ጉዳይ መሆን የለበትም። ይህ ሃላፊነት እንደ ደቡብ አፍሪካው የሽግግር ሂደት ከማንኛው
ም መንግስት ውጭ ሆኖ ለሚሰራ፤ በአጠቃላይ የሃገሪቱን የዴሞክራታይዜሽን ሂደት ከማንም የፖለቲካ ሆነ ሌላ ሃይል
ወገናዊ ቁጥጥር ውጭ በበላይነት ለሚያቅድና ለሚያስፈፅም አካል መተው ይኖርበታል።*

መኢሶን ለእንዲህ አይነቱ ከስልጣን ቅብብሎሽ እጅግ አልፎ የሚሄድ የሽግግር ሂደት ህብረተሰባችን ምንኛ ብ
ቁና ዝግጁ እንደሆነ ሲያስረግጥ *"ምንም እንኳን በእጃችን ያለውን ወርቅ እንደ መዳብ ቆጥረን ልብ ባንለውም ቅሉ ሀ
ብረተሰባችን ዛሬ አስፈላጊ የሆነው መድረክ ከተመቻቸለት ከአብራኩ በሚፈልቁ ራሱ በሚቆጣጠራቸው ተቋማትና በነ
ዚህም አማካኝነት ከዳር ድንበር መንደር እስከ አዲስ አበባ ድረስ በየደረጃው በሚያደርገው እንቅስቃሴ በተረጋጋ ሁኔ
ታ እራሱን በራሱ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ይገኛል.......ያለንበት ችግር
ይህንን ሁሉ በጎ ሃይል ወደ አንድ የጋራ አቅጣጫ መርቶ ዛሬ የተከፋፈለውንና የተዳከመውን የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስ
ት በህዝብ ሃይል ወደ ብሄራዊ ውይይት ሊያመጣ የሚችል፤ ይህንን አሻፈረኝ ካለ ደግሞ ይህንን መንግስት በህዝብ ትግ
ል አስወግዶ ሃገሪቱን የሚያድን ማንም ሊበግረው የማይችል አንድ አወንታዊ ሃይል የማድረግ ችግር ብቻ ነው።"* በማለ
ት ካለንበት ታሪካዊ አመቺ ሁኔታ አንፃር ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ለመታገል ዝግጁ የሆኑትን ሚልዮኖች አንድ "የማይ
በገር አወንታዊ ሃይል ለማድረግ" የህዝባዊ አመራርን ጥያቄ ወሳኝነት ለማስመር ሞክሯል።

እነዚህ ቃላት ከተፃፉ ሶስት አመታት በኋላ የተካሄደው የግንቦት ምርጫ ሂደት ህብረተሰባችን ለዴሞክራሲያ
ዊ ሽግግር ያለውን ብቃት፤ ህዝባችን ለዚህ እውንነት ለመታገልና ለመሰዋት ያለውን ቁርጠኝነት ምንም በማያወላዳ ሁኔ
ታ ለማሳየት በቅቷል። በዚያው ልክ ደግሞ ግንባር ቀደም የሆኑት የፖለቲካ ሃይሎች ለዚህ ህዝባዊ ብቃት የሚመጥን
ህዝባዊ አመራር መስጠት አለመቻላው ዛሬ ላለንበት ከባድ ችግር ዳርጎናል። ይህንን ችግር በአስቸኳይ ተወጥተን ትግ
ሉን መልክ ማስያዝ ካልቻልን ከጊዜ ጋር ይህ የተመቻቸ ሁኔታ ከስሞ ሃገራችንና ህዝባችን ለባሰና ምናልባትም ሊወጡ
ት የማይችሉት ቀውስ ውስጥ የሚገቡበት አደጋ ይኖራል የሚል ስጋት አለን። ከዚህ በመነሳት መጀመሪያ ወደ ተረጋጋ
ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ያስፈልገናል ስለምንለው "ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ" ያለንን ሃሳብ
አመልክተን ሁለተኛ እንደዚህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊው ትግል ድል መቋጠሪያ የሚሆን ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ከወያኔ/
ኢህአዴግ አመራር ለህዝብ ፈቃድ መንበርከክ በመለስ የማይታሰብ ስለሆነ ወደዚህ ድል ስለሚያደርሰን የትግል ጉዞ ያ
ለንን አስተያየት ለመሰንዘር እንሞክራለን። (በውጭ ሁሉን አቀፍ - በሃገር ውስጥ ህቡእ)

አንደኛ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ምንነት፤ አስፈላጊነትና ተግባራት -

በመሆኑም ዛሬ የሚካሄደው ተጋድሎ ከእንግዲህ ምንም አይነት ምርጫ ከመታሰቡ በፊት ይህንን ለማስቻል አ
ስፈላጊ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ የማመቻቸት ትግል ነው። ዛሬ የተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ ዴሞክራሲ በሰፈነበ
ት ህብረተሰብ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህዝብ ፊት ተወዳድረው ስልጣን ለመጨበጥ የሚያካሂዱት የምርጫ ዘ
መቻ እንዳይደለ ከፀሃይ ደርቶ የሚታይ ሃቅ ነው። ትግሉ በህብረተሰባችን የዴሞክራሲ እጣ ፈንታ ያገባናል የሚሉ ሃይ
ሎች በሙሉ በጋራ የሚሳተፉበት የዴሞክራታይዜሽን ትግል ነው። ይህ ሁኔታ ምናልባት ከኛ ይበልጥ የገባቸው የኢህአ
ዴግ መሪዎች የተያያዙት የአፈና ውርጅብኝ በፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ከ
የትም የፖለቲካ ድርጅት ሳይወግኑ ከኢህአዴግ አንፃር እንኳን የግድ በተቃዋሚነት ሳይቆሙ ለዴሞክራታይዜሽኑ ሂደት
መጎልበት በቆሙ ዜጎች፤ በነፃው ፕሬስ ባልደረቦች፤ በሲቪኩ ማህበረሰብ አራማጆች ላይ የጅምላ አፈና ሂደት እንደ
ሆነ እናያለን።ይህንን መሰረታዊ እውነታ መገንዘብ ያቃታቸው ወገኖች እኛ ትግሉ በጠቅላላው በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ
ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የጋራ ትግል ነው ስንል የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ እንደሆነ፤ ይህ አልበቃ ብሎ ከፖለቲ
ካ ድርጅቶች እንኳን "የኛ ብቻ" ነው በሚል አጉል አቅጣጫ የያዙ ወገኖች እንዳሉ እየታዘብን ነው። እነዚህ ወገኖች

እርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ''እንደ አንድ ሰው'' ሆኖ እንዲነሳ በተደጋጋሚ ጥሪ ያደርጋሉ። ነገር ግን ይህ ጥሪያቸው ''
እንደ አንድ ሰው ሆነህ ከኛ ጀርባ ተሰለፍ'' የሚል አስገራሚ ጥሪ ነው። እነዚህ ወገኖች እርግጥ ''ለመድበለ ፓርቲ ስር
አት እንታገላለን'' ይላሉ። ነገር ግን ህልማቸውና አካሄዳቸው የአንድ ድርጅትን አገዛዝ በአንድ ድርጅት ተቃዋሚ ሃይ
ል ለመጣል የሚደረግ በቅራኔ የተሞላ አካሄድ ነው። ኢዴሃህ በዚህ እጅግ ጠባብና አደገኛ እይታ ጉዳይ ለዩክሬክቱ ጉ
ባኤ ባሰናዳው ሰነዱ ላይ በትክክል እንዳስቀመጠው

'' *ካለፉት ሂደቶች ተምረን ወደ ፊት እንራመድ ካልን ከወዲሁ መቀበል የሚኖርብን አንድ መሰረታዊ ሃቅ አለ
። ህብረተሰባችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሸጋገር በሚደረገው ትግል የፖለቲካ ድርጅቶች ወሳኝ የሆነ የግንባር
ቀደምነት ሚና ቢኖራቸውም የተጋድሎው አልፋና ኦሜጋ እነሱን ብቻ አድርጎ መውሰድ ሌላ ታሪካዊ ስህተት ይሆናል
።* '' ካለ በኋላ ከዚህ ይልቅ በሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች
በሁሉን አቀፍ የሽግግር ጉባኤ አማካኝነት በተራ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በአመራርም ደረጃ በትግሉ የሚሳተፉበት ሰፊ አ
ገራዊ መድረክና ታግሎ የሚያታግል አካል ማቋቋም የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ እንደሆነ ጠቁሟል።

''ህዝባዊ አመራር'' ብለን የምንጠቁመው ሃሳብ ይበልጥ ግልፅ እንዲሆን ዛሬ ከፊታችን የተደቀነው የህብረተሰ
ባችን ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመሸጋገር ሂደት ምን መልክ እንዳለው በጥቂቱም ቢሆን ማብራራትና ከዚም
ይህንን ሂደት በተጨባጭ እውን ለማድረግ ስለሚያስፈልጉን ተቋማት ያለንን ሃሳብ እንሰነዝራለን።

ለዚህ ሽግግር ወሳኝ ምእራፍ ይሆናል የምንለው በሃገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ ለመጥራት የሚ
ያስችል በህዝባዊ ተጋድሎ ለዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የሚያደላ የሃይል ሚዛን ሲፈጠር ብቻ ነው። ኢዴሃህ ለዩክትሬክ
ቱ ጉባኤ ባስናዳው ሰነድ እንዲህ አይነቱ ወሳኝ የሆነ ጉባኤ በሃገሪቱ ውስጥ እንዲደረግ ከታሰበ መጀመሪያ በህዝባዊ ት
ግል ኢህአዴግን የማስገደድቅድመ-ሁኔታ እንዳለ ከጠቆመ በኋላ በዚህ ጉባኤ ላይ ስለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችና ስ
ለሚጠብቀው ተግባር በጥቅሉ ሲያቀርብ፤

'' *.....የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች፤ የወጣቶችና የሴቶች፤ የሰራተኞችና የገበሬዎች፤ የነ
ጋዴዎች፤ የጋዜጠኞች፤ የሙያ፤ የጥቅም፤ የባህል፤ የምሁራንና የባለሙያዎች ማህበራትና ስብስቦች ተወካዮች፤ የሃይ
ማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሎች፤ እንዲሁም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች የሚሳተፉበት ሰፊ አገር አ
ቀፍ ጉባኤ*'' እንደሚሆን ግልፅ በሆነ ሁኔታ አስቀምጧል።'' ከዚህም በማያያዝና ካለፉት በመንግስት ደረጃ ተቀምጠው
''ሽግግሩን'' እናካሂዳለን እያሉ ህብረተሰቡን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሳይሆን ፀረ ህዝቦችን ከጊዜያዊነት ወደ ቋሚ
አንባገነንነት ካሸጋገሩ የኪሳራ ሂደቶች በተቀሰመው ትምህርት በመነሳት የሽግግሩ ጉዳይ ለማንም ይሁን ለማን (እነዚህ
**የተላያዩ ሃይሎች ወደ ዚህ ስብሰባ በተጋባዥነት አይመጡም። መጀመሪያ ለዚህ እውንነት በሚደረገው ትግል ተሳትፎ.....
በምርጫ ዘመቻው የተሳተፉ ሁሉ ትግላውን አስተባብረው የሚቀጥሉበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል...)**

የግንቦትን ድሎች ማስመለስ ስንል? የሁለት ጉባኤዎች ጥያቄ - ዋናው በሃገር ቤት የሽግግር ጉባኤ ማካሄድና በ
ህብረቱ እምነት ወደ ተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ሁለት መሰረታዊ የሆኑ የሽግግር ተቋማት መሰየም -
ወደዚህ በሚደረገው የትግል ጉዞ ሁለት ጉዳዮች በጣም በግልፅ መቀመጥ አለባቸው።

አንደኛ *በዚህ ጉባኤ የሚሳተፉ ሃይሎች መጀመሪያ 'በፖለቲካ ድርጅቶች' ትግል ተካሂዶ ዴሞክራሲያዊ ሲሰፍ
ን? አይደለም። እነዚህ ሁሉ ሃይሎች የትግሉ ባለቤት እንጂ የፖለቲካ ድርጅቶች ታግለው በሚያመቻቹት መድረክ ''ተ
ጋብዘው'' የሚመጡ አይደሉም። ለዚህ ጉባኤ እውንነት በሚደረገው ትግል እስከ አመራር ድረስ ተሳትፎ ማድረግ አለባ
ቸው። በነሱ አማካኝነት መጀመሪያ የህዝባዊ ትግሉን ማእበል ለመቀስቀስ መስራት። እንዴት? ስራ አጡ፤ መናጢ ደሃ
ው፤ በአጠቃላይ በምርጫው ወይም በህዝብ ድምፅ መነጠቅ ካለበት ችግር እንዲወጣ ተቀይሰው የነበሩት ፖሊሲዎች
ስራ ላይ መዋል ባለመቻላቸውና የወያኔ አጥፊ ፖሊሲዎች መቀጠል ከችግር ችግር፤ ከቀውስ ቀውስ እየያዛው የሚነጉ
ደው የህብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን ከግንቦት ድል መነጠቅ ጋር እያያያዙ ለነዚህ መመለስ ማለትም ከዴሞክራሲያ
ዊ ስርአት መስፈን በመለስ ችግራው እንደማይፈታ ተገንዝበው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ። ይህ ሁሉ ደግሞ ከተባለ ሚል
ዮኖችን በተናጠል ብሶታቸውና በአጠቃላዩ ህዝባዊ አጀንዳ ለማንቀሳቀስ ይህንን ሰፊ ተግባር የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ
ማለቱ ቀልድ ነው። በአንድ በኩል እንደ ፖለቲካ ሃይሎችና እንደ ተማሪና ወጣት ''አጠቃላዩን'' የሚያነሱ በሌላ በኩል*

ደግሞ እንደ ነጋዴው፤ ስራ አጡ፤ ሰራተኛው፤ ድሃው ገበሬ በራሳቸው ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚን ቀሳቀሱ - እንደ የካቲት!!!! የካቲትን ህዝባዊ ማእበል ያደረገው - ግብታዊነት? አይደለም። የመደራጀት የኮሚቴዎች ት ኩሳት - ሁሉም ብሶቱን ግን ሁሉም ደግሞ "የእርዳ ተራዳ" በወቅቱ የመኢሶን በራሪ እንዳለው በየእድሩ፤ በየፋብሪካው ፤ በየጦር ሰፈሩ፤ ካህኑ ሳይቀር .......

ሁለተኛ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ በሚደረገው ትግል በውጭ ያሉ ዴሞክራቶችና ስብስቦች ሁኔታው ይፈቅድላቸዋል ና እነሱም ለትግሉ አስተዋፅኦ ለማድረግ በውጭ ሃገር ቤት ነገ ከህዝባዊው ድል ጋር ተያይዞ በሚጠራው ጉባኤ መልክ በውጭ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጠርተው ይህንን ትግል የሚያግዙበት የጋራ ስትራቴጂና የጋራ መድረክ መፍጠር ይኖርባቸዋ ል። ለዚህ ትግል ሚልዮኖችን እንዴትና ማን ያንቀሳቅሳቸው?

## ህዝባዊ አመራር

ህዝባዊ አመራር ስንል ምን ማለት እንደሆን ለማብራራት ከመሞከራችን በፊት ከእን-ግዲህ በሃገራችን ስለተያዘው ትግል ምንነት መጀመሪያ ግልፅ ግንዛቤ ያስፈልገናል።

1ኛ. የተያዘው ትግል ምንድን ነው?

ትግሉ የምርጫም የስልጣን ቅብብሎሽም ላይ ያተኮረ የፖለቲካ ትግል አይደለም። ግንቦት ምርጫ ስንሳተፍ በ ቅድሚያ ዴሞክራሲ ባልሰፈነበት ሁኔታ ነፃ ምርጫ ተካሂዶ፤ የህዝብ ድምፅ ያለአንዳች መሸራረፍ ተከብሮ የተረጋጋ ዴ ሞክራሲያዊ ስርአት በምርጫ እናመጣለን ብለን አልነበረም። መኢሶን በተደጋጋሚ እንዳለው ነፃ ምርጫ ለዴሞክራሲ የ ሚካሄደው ትግል አይሎ ገዥዎች ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ደረጃ ሲደርስ የሚደረግ 'የድል መቋጠሪያ' ሂደት እንጂ እ ስከዚህም በቅድሚያ በህብረተሰቡ ውስጥ የሌለ ለዴሞክራሲ የሚያደላ አዲስ የሃይል ሚዛን የሚፈጥር ሂደት አይደለም። መድበለ ፓርቲ ምርጫ እንዳይደረግ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ህገ መንግስታዊ እን-ቅፋት ባለበት ስርአት ስር ምርጫ እንሳ ተፍ ያልነው ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስታዊ ስርአት እውን ለማድረግ ቁልፍ የሆነውን የሚልዮኖች ህዝባዊ የትግል ማእበ ል ለመቀስቀስ ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ የግንቦት ቅልበሳ የተገበረው የህዝብ ልጆች ደምና እንባ ተገብሮበትም ቢሆን የ ዚህን ትንተና ትክክለኛነት አረጋግጦ ለቀጣዩ ትግል ቁልፍ የሚሆኑ ሁለት ትምህርቶች ለሚልዮኖች ለማስጨበጥ የበቃ ሂ ደት ነው።

አንደኛ ፀረ ዴሞክራሲያዊው ስርአት ቆሞ እስከሄደ ድረስ ነፃ ምርጫ ተብሎ ነገር የሚታሰብ እንዳይደለ። ሁለ ተኛ በምርጫው ዘመቻ የተንቀሳቀሱት በግንቦት ቅልበሳ ሳቢያ ይህንን መሰረታዊ ሃቅ ለመገንዘብና በምርጫና በዴሞክራሲ መሃከል ያለውን ግንኙነት በጠራ ሁኔታ ለመረዳት በቅተዋል። በመሆኑም ከእንግዲህ የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በ ቅድሚያና በትግል ዴሞክራሲ ከመስፈኑ በፊት እንደገና በኢህአዴግ ስርአት ስር 'ተነስ! ታገል! ተሰዋ! ምረጥ' እያልን ህዝ ባችንን እንቀሰቅሳለን ቢሉ አፍ ከማበላሸት ሌላ የሚያመጡት ፋይዳ የላቸውም። ይህም በመሆኑ ዛሬ የተያዘው ትግል ግን ቦት ያንቀሳቀሳቸውን ብቻ ሳይሆን ይህ ነው የማይባል ጥራት የሰጣቸውን ሚልዮኖች ይህ ጥራት ደብዛው ከመጥፋቱ በፊ ት አንቀሳቅሰው የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት እንዲከፈት ማድረግ ይሆናል ማለት ነው።

2ኛ. እንደዚህም በመሆኑ ዛሬ የምንያያዘው ትግል

# ስለ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አንዳንድ ነጥቦች

## ዋናው ሃሳብ

1. እንሰባሰብ ስንል - የፖለቲካ አቋዋም፣ የትግል ስልት፣ የአደረጃጀት አይነት (ሲቢክ፣ ፖለቲካ፣ የሙያ፣ የሃ ይማኖት፣ የወጣት የሴቶች-) ወዘተ ሳይባል ለዚች አንዲት አገራችን አንድነት፣ ሰላም፣ ብልፅግና፣ ክብር የጋራ የሆነ ራ

እይ ያለን ኢትዮጵያውያን አንድነቱዋን፣ ሰላሙዋን፣ ክብሩዋን ፎር ግራንትድ አንውሰደው፣ ጊዜው በሚጠይቀው ፍጥ
ነትና ቆራጥነት ካልተንቀሳቀስን፣ እነዚህ የጋራ እሴቶቻችን በተለይ ገንጣይና አስገንጣይ የሆነ አጥፊ ቡድን በታሪካችን
ለመጀመሪያ ጊዜ በመሃል መንግስትነት ተሰይሞ ባለበት አደገኛ ሁኔታ እነዚህ ሁሉ እሴቶች እዚህ ግባ የሚባል ሰብሳቢ
አጥተው የሚቀጥሉበት አደገኛ ሁኔታ።

2. ከግንቦት ቅልበሳ ጋር ተያይዘው በአንድ በኩል በለየለት የሸብር አገዛዝ በተሰማሩ ጥቂቶች በሌላ በኩል ደ
ግሞ በአመራር ክፍተት የተነሳ ህብረተሰባችን በአን-ድ በኩል የቅልበሳው መዘዝ በሆኑት የማህበራዊና የኢኮኖሚ ቀውሶ
ች በሌላ በኩል በጨለምተኝነትና ትጥቅ መፍታት አባዜ ውስጥ እየዋኘ መገኘቱ። ይህ ችግር በአስቸኳዋይ ተገቢ የህዝ
ቡን ራእይ ያነገበ አመራር ካላገኘ የጣናማ አፀፋ ጉዳይ። ትግሉ ይቆማል ማለት አይደለም በአንድ በኩል ወያኔዎች በሌላ
በኩል ደግሞ የግንቦትን እሴቶች የኛ በማይሉ (በሁለት ፀረ ግንቦት ሃይሎች በቀልባሾቹና ግንቦትን እሴቶች የኛ በማይሉ
ሃይሎች፣ የግንቦት እሴቶች ጋር እምብዛም ግ-ንኙነት በሌላቸው ብቻ ሳይሆን ጭራሹን እነሱን በሚፃረሩ አጀንዳዎች ለሁ
ዝባችን እያስጨበጡየአጉል አፀፋ ሃይሎች (የካቲት ማግ-ስት አይተነዋል) እየገነኑ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በአካባቢ ሰበቦች
ትርምብ፣ እልቂት ደም መፋሰስ....የሰፈኑት ማህበራው የኢኮኖሚ ችግሮች

2. እንደሳር ቅጠል መብዛታችን፣ ህዝባችን በግንቦት ወቅት ለነዚህ እሴቶች መቆሙን በማያወላዳ ሁኔታ አሳይ
ቱዋልና የመዘናጋት ብሎም የዳተኝነት አባዜ ተጠናውቶናል። በድርጅት አጥር ተኮፍሰናል። የወቅቱ አጣዳፊነት አልገባን
ም። ሁኔታው ከቀጠለ ትጥቅ መፍታት፣ ውዥንብር እየነገሱ ከእለት እለት ውጥንቅጡ የወጣ አደገኛ ብሃሬዊ፣ የአካባ
ቢና አለም አቀፍ ሁኔታ። ግንቦት 83 እንዲህ አይነት "የኢትዮጵያዊነት ክፍተት" ተፈጥሮ ከኛ ከኢት ዴሞክራቶችና
አገር ወዳድ ሃይሎች፣ ከዚያም አልፎ ከዋናው ባለቤት ከኢትዮ ህዝብ ውጭ የዚች አገራችን እጣ ፈንታ አንድነቱዋ ሳ
ይቀር በባእዳንና ይህ አጀንዳ በማይመለከታቸው ሃይሎች ሲወሰን አይተናል።

<u>መግቢያ</u>

ህብረታችን በግንቦት 97 ምርጫ ሲሳተፍ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ነፃ ምርጫ ይቻላል ከሚል አጉል ህልም ተነ
ስቶ አልነበረም። ዴሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነበት አካባቢ ነፃ ምርጫ አይቻልም ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት የተሳት
ፎው አላማ በምርጫ ዘመቻው ሳቢያ ሚልዮኖችን አንቀሳቅሶ ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ቀጣይ ህዝባዊ ትግል ሁኔታዎች
ን ለማመቻቸት ነበር። ይህ ስትራቴጂ በግንቦት ሳቢያ ታሪካዊ ተልእኮውን አከናውኗል። እንዲያውም ከግንቦት ድሎች
እንደ መሰረታዊ ሆኖ መቆጠር የሚኖርበት ይህ "ምርጫ ከዴሞክራሲ ይፈልቃል እንጅ ድሮውንም የሌለ ዴሞክራሲ
ከምርጫ አይመጣም" የሚለውን ሃቅ ሚልዮኖች እንዲጨብጡት ማስቻሉ ነው። ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔ
ታ አንዳንድ ታማኝ ተቃዋሚዎች ከምርጫ ምርጫ እየተሳተፍን ከምርጫ ምርጫ በሃገሪቱ ያለው ዴሞክራሲ አድማስ
እየሰፋ አንድ ቀን የተሟላ ዴሞክራሲ ይሰፍናል የሚሉት ልፈፋ በግንቦት ድልና በድሉ ማግስት በተከሰተው ቀውስ ምክ
ንያት ታልፎ የሄደ ስትራቴጂ ነው። በኛ ግምት ከእንግዲህ በሌላ ህዝባዊ ትግል ማእበል በሃገራችን የተሟላ ዴሞክራሲ
እስካላሰፈንን ድረስ ነፃ ምርጫ ቀርቶ የእህአዴግን መሪዎች ለከባድ ኪሳራ ያበቃቻው በቅድመ ግንቦቱ ዘመን የነበረው
የዴሞክራሲ የፍንጭ ፍንጭ እንኳን ይኖራል ብሎ ማሰብ ወይ የለየለት የዋህነት ነው አለበለዚያ በህዝብ ትግል ከማሾ
ፍ ሌላ ምንም ትርጉም አይኖረውም። ከእንግዲህ እንደ ቅድመ ግንቦቱ ወቅት "በምርጫ ሂደት በመሳተፍ ዴሞክራሲን
እናራምዳለን" የሚለው ስትራቴጂ ከሃገራችን ዴሞክራቶች ብቻ ሳይሆን ሚልዮኖችም በመራራ መስዋእትነት በቀሰሙት
ግንዛቤ የተነሳ ከትግል አጀንዳቸው የፋቁት ስትራቴጂ ነው።

ዛሬ በግንቦት ማግስት የኢህአዴግ አመራር በዝረራ ተሸንፎ ያንን መቀበል አቅቶት በሽብር አገዛዝ ተሰማርቷል
። የተያዘው የቅልበሳ ሂደት እጅግ አሳሳቢ የሚሆነው ዛሬ በአይናችን ስር በመካሄድ ላይ ካለው የአፈና ውርጅብኝ ባሻ
ገር የወያኔ/ኢህአዴግ አካሄድ ላለፉት አስራ አምስት አመታት ህዝባችን በመስዋእትነት የገነባቸውን የዴሞክራሲ ሽግግ

ር ተቋማትና ሌሎችም በጎ የፖለቲካና ስነልቡናዊ ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርጎ በማውደም (ለዩትሬክት የተፃፈው ሰነድ
ጥቅስ)ይዘት እነዚህን ተከላክሎ የመንከባከብ

የግንቦት ድሎች ቅልበሳ ስንል የዚህ ቅልበሳ አሳሳቢነትና መዘዘኛነት ዋና ገፅታ ባለፉት አስራ አምስት አመታት
ቀስ በቀስ ታጋይ ዜጎች እየሞቱ፤ እየታሰሩ፤ እየተሰደዱ የገነቧቸውንና የወያኔ/ኢህአዴግን መሪዎች ለሸንፈት የዳረጓቸው
ን ውሱን የነበሩትን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትንና ግኝቶች እንኳን እንዳልነበሩ አድርጎ ለማውደም የሚደረገው ሙከራ ነው
። እርግጥ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር የተሟላ ዴሞክራሲ ኖሮ አያውቅም። ነገር ግን የኢህአዴግ መሪዎች ካሉበት የኪሳራ
ደረጃ አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ " የተሟላ ዴሞክራሲ " ሳያስፈልገው በቅድመ ግንቦቱ ወቅት በነበረችው የዴሞክራሲ
የፍንጭ ፍንጭ ተጠቅሞ በፀረ ህዝቦቹ ላይ የማያወላዳ ድል ለመጎናፀፍ በቅቷል። ከዚህ መቅሰም ያለብን ትምህርት በጣ
ም ግልፅ ይመስለናል። ገና በእንጭጩ የነበረው የዴሞክራሲ ሂደት ምን ያህል ኪሳራ እንዳደረሰባቸው ተገንዝበው በለየለ
ት ሽብር ለመሰማራት በመረጡት የኢህአዴግ መሪዎች ስር ከእንግዲህ እነዚህ ቀልባሾች በህዝብ ትግል ከመንበርከካቸ
ው በፊት እንደ ዳኝነት ነፃነት፤ የህግ የበላይነት፤ ነፃ ምርጫ፤ ተጠያቂነት ወዘተ የመሳሰሉት ከባድ ከባድ እሴቶች ቀርቶ
ቅድመ ግንቦት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች እንኳን ተመልሰው እውን ይሆናሉ ብሎ ማሰብ የለየለት የዋህነት ብቻ አይ
ደለም። የቅልበሳውን አሳሳቢነት የሚክድ፤ የቀልባሾቹን ቁርጠኝነት የማይገነዘብ በህዝብ ትግልና መስዋእትነት የሚያፌዝ
አደገኛ አስተሳሰብ ነው። ህብረታችን ለዩክሬክት ጉባኤ ባዘጋጀው ሰነድ በዚህ ጉዳይ ትክክለኛ ግንዛቤ መጨበጥ ለቀጣዩ
ትግል ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ሲጠቁም፤

*" ዛሬ በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ትግል ማንም የፖለቲካ ሃይልም ሆነ ስብስብ የሚያወጣ
ው ስትራቴጂ በአጥፊነትም ሆነ በአልሚነት የሚመዘነው ከነዚህ ድሎች አንፃር በሚወስደው አቋም ነው። ከዚህ አንፃር
ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ህልማቸው የህዝብ ድምፅ ሰርቀው ለሌላ አምስት አመት በስልጣን ላይ
ለመቆየት ብቻ የሚጥር ህልም አይደለም። ዛሬ በአይናችን ስር እየተካሄደ ካለው ዘግናኝ የሽብር ውርጅብኝ ባሻገር ሙከ
ራቸው ህብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ብቁ ያደረጉትን በመስዋእትነት የተገነቡ እነዚህን ተቋማት በማፈራረስና
በህዝባችን ስነ ልቡና የሰረፁትን በጎ ያስተሳሰብ ለውጦች በማውደም የዛሬ ሃያም ሰላሳም አመት የነበረውን "የሽግግር ክ
ፍተት" መልሶ እውን ለማድረግ የሚጥር መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ ነው።" (ለኡትሬክት ደብዳቤ....)*

ይህ መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ በሌላ ገፅታው ከእንግዲህ ያለ ዴሞክራሲ ምርጫ ብሎ ነገር አይታሰብም የሚለው
ን ለቀጣዩ ትግል ወሳኝ የሆነ ግንዛቤ የማድበስበስና በአንዳንድ ተቃዋሚ ተብየዎችና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ትብብር ስለ
ቀጣይ ምርጫ በመለፈፍ የወቅቱን ዋና አጀንዳ ማለትም ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር የመዋደቁን ነገር እንደ አክራሪዎች ጥያ
ቄ አድርጎ የማቅረብ ሙከራ ነው። በምንም ምክንያት ይሁን በምን የሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች እዚህ ወጥመድ
ውስጥ ገብተውና የግንቦትን የትግል ምእራፍ ዘግተው በወያኔ/ኢህአዴግ ስር፤ በወያኔ/ኢህአዴግ የምርጫ ቦርድ፤ በተኮላሸ
ና 'መስመር በገባ' ፕሬስ፤ ትርጉም ካለው ተቃውሞ ይልቅ በስነ ስርአት አድማቂነት በተሰለፉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ተሳት
ፎ የሚደረግ ምርጫ ተብየ ነገር የግንቦት የቀብር ስነ ስርአት ሙከራ እንጂ ሌላ ትርጉም አይኖረውም።

በመሆኑም ዛሬ የተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የ
ተናጠል ትግላቸውን "ለማፋፋም" ላይ ታች የሚሉበት ወይም ደግሞ በህዝብ ፊት ተወዳድረው ስልጣን ለመጨበጥ የ
ሚያካሂዱት ተራ የምርጫ ዘመቻ አይደለም። ከእንግዲህ ምንም አይነት ምርጫ ከመታሰቡ እንኳን በፊት ይህንን ግን
ዛቤ በመስዋእትነትና በትግል የጨበጡትን ሚልዮኖች ይዞ ለነፃ ምርጫ አስፈላጊ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለማ
ምጣት የሚደረግ ትግል ነው። በመሆኑም ትግሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግል ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የሃገርና የዴሞክ
ራሲ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች የጋራ ትግል መሆን ይኖርበታል። ህብረታችን የሁሉን አቀፍ ጉባኤ ሃሳብ አፍልቆ
ሲታገል የቆየው ይህ የጋራ ትግል ግልፅና ቀላል የሆነ አጀንዳ የሚጨብጥበትንና ለዚህ አጀንዳ ታግሎ የሚያታግል የት
ግል አመራር መድረክ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።

## ሐ/ ህዝባዊ አመራር

ሚልዮኖችን እንደገና ወደ ትግሉ ለመመለስ በሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ የመጀመሪያ መጀመሪያ የሚሆነው ተግባራችን ለራሳችንም ሆነ ለታጋዩ ህዝባችን "የግንቦትን ድሎች ማስመለስ ማለት ምን ማለት ነው?" የሚለውን ጥያቄ ግልፅና ቀላል በሆነ መልክ መመለስ ያስፈልጋል። የግንቦትን ድል እናስመልስ ማለት የዛሬ ሁለት አመት ምርጫው ተ ጭበርብሯልና የህዝቡ ድምፅ እንደገና ይቆጠር ማለት አይደለም። በወቅቱ የነበሩት ማስረጃዎች በኢህአዴግ ምርጫ ቦ ርድ ተዘርፈው ከጥቅም ውጭ በመሆናቸውና በሌሎች በርካታ ምክንያቶች የተነሳ ይህ አይነቱ አካሄድ የሚያዋጣ አይ ሆንም። የግንቦትን ድሎች ማስከበር ማለት ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታና ከኢህአዴግ ቁጥጥር ውጭ ነፃ ሆኖ በሚሰራ የምርጫ ቦርድ ሌላ ምርጫ ይደረግ ማለት እንደሆነ በነሃሴ ወር 1998 እ.ም. የተደረገው የኢዴሃህ ሸንጎ በግልፅ ያሰመረ ው ጉዳይ ነው። ለዚህ ህዝባዊ አላማ የሚደረገው ትግል ከወዲሁ ይዞ መነሳት ያለበት አንድ መሰረታዊ ግንዛቤ ይኖራል ። ከእንግዲህ በህዝባዊ ተጋድሎ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት ካልከፈትን በሃገራችን እንዲህ አይነቱ ምርጫ የሚካሄ ድበት ሁኔታ ጨርሶ ሊኖር አይችልም።

ድርጅታችንም ሆነ ኢዴሃህ በዚህ በዴሞክራሲ መስፈንና በነፃ ምርጫ መሃከል ስላለው ዝምድና ያላቸውን ግ ንዛቤ ደግመው ደጋግመው ገልፀዋል። ከፍ ብለን እንዳልነው ህብረቱ ምርጫው ውስጥ ሲገባ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ነ ፃ ምርጫ ይቻላል ከሚል አጉል ህልም ተነስቶ አልነበረም። ዴሞክራሲ በቅድሚያ ባልሰፈነበት አካባቢ ነፃ ምርጫ አ ይቻልም ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት የተሳትፎው አላማ በዘመቻው ሳቢያ ሚልዮኖችን አንቀሳቅሶ ለዴሞክራሲ ለሚደረ ገው ቀጣይ ትግል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚል ስትራቴጂ ነበር።

የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በነሱ ላይ መገንባት ማለት ሚልዮኖች በትግልና በመስዋእትነት ባገኙት በዚህ ታሪ ካዊ ግንዛቤ ተመርኩዞ ከእንግዲህ በወያኔ/ኢህአዴግ አመራር ስር ምርጫ ብሎ ነገር ለፀረ ህዝቦች አገዛዝ ህጋዊ ሽፋን ከመስጠት ሌላ ምንም የሚፈይደው ነገር እንደሌለ ተገንዝቦ ከማንኛውም የምርጫ ሂደት በፊት በህዝባዊ ተጋድሎ የዴ ሞክራሲያዊ ሽግግር ወቅት ለመክፈት መታገል ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት መጀመሪያ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስ ርአት ለመሸጋገር ያስፈልገናል ስለምንለው "ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ" ያለንን ሃሳብ አመልክተን ሁለ ተኛ እንደዚህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊው ትግል ድል መቋጠሪያ የሚሆን ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ከወያኔ/ኢህአዴግ አመራ ር ለህዝብ ፈቃድ መንበርከክ በመለስ የማይታሰብ ስለሆነ ወደዚህ ድል ስለሚያደርሰን የትግል ጉዞ ያለንን አስተያየት ለ መሰንዘር እንሞክራለን። (በውጭ ሁሉን አቀፍ - በሃገር ውስጥ ህቡእ)

ይህንን መሰረታዊ እውነታ መገንዘብ ያቃታቸው ወገኖች እኛ ትግሉ በጠቅላላው በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዴሞክራሲያ ዊ ሃይሎች የጋራ ትግል ነው ስንል የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ ብቻ እንደሆነ፤ ይህ አልበቃ ብሎ ከፖለቲካ ድርጅቶች እንኳን "የኛ ብቻ" ነው በሚል አጉል አቅጣጫ የያዙ ወገኖች እንዳሉ እየታዘብን ነው። እነዚህ ወገኖች እርግጥ የኢ ትዮጵያ ህዝብ "እንደ አንድ ሰው" ሆኖ እንዲነሳ በተደጋጋሚ ጥሪ ያደርጋሉ። ነገር ግን ይህ ጥሪያቸው "እንደ አንድ ሰው ሆነህ ከኛ ጀርባ ተሰለፍ" የሚል አስገራሚ ጥሪ ነው። እነዚህ ወገኖች እርግጥ "ለመድብለ ፓርቲ ስርአት እንታገላ ለን" ይላሉ። ነገር ግን ህልማቸውና አካሄዳቸው የአንድ ድርጅትን አገዛዝ በአንድ ድርጅት ተቃዋሚ ሃይል ለመጣል የ ሚደረግ በቅራኔ የተሞላ አካሄድ ነው።

የግንቦት ምርጫ ሂደት ህብረተሰባችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ያለውን ብቃት፤ ህዝባችን ለዚህ እውንነት ለመታገልና ለመሰዋት ያለውን ቁርጠኝነት ምንም በማያወላዳ ሁኔታ ለማሳየት በቅቷል። በዚያው ልክ ደግሞ ግንባር ቀደም የሆኑት የፖለቲካ ሃይሎች ለዚህ ህዝባዊ ብቃት የሚመጥን ህዝባዊ አመራር መስጠት አለመቻላው ዛሬ ላለንበት ከባድ ችግር ዳርጎናል። ይህንን ችግር በአስቸኳይ ተወጥተን ትግሉን መልክ ማስያዝ ካልቻልን ከጊዜ ጋር ይህ የተመቻቸ ሁኔታ ከስ

ም ሃገራችንና ህዝባችን ለባሰና ምናልባትም ሊወጡት የማይችሉት ቀውስ ውስጥ የሚገቡበት አደጋ ይኖራል የሚል ስጋት አለን። ከዚህ በመነሳት መጀመሪያ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ያስፈልገናል ስለምንለው "ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ" ያለንን ሃሳብ አመልክተን ሁለተኛ እንደዚህ አይነቱ የዴሞክራሲያዊው ትግል ድል መቋጠሪያ የሚሆን ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ከወያኔ/ኢህአዴግ አመራር ለህዝብ ፈቃድ መንበርከክ በመለስ የማይታሰብ ስለሆነ ወደዚህ ድል ስለሚያደርሰን የትግል ጉዞ ያለንን አስተያየት ለመሰንዘር እንሞክራለን።

ከዚህ ታሪካዊ ተልእኮ አንፃር ሲታይ ይህ የታሰበው ጉባኤ የትግላችን የመጀመሪያው ምእራፍ እንደመሆኑ መጠን ዋና ተግባሩ ወደ አገር አቀፉ ሰፊ ጉባኤ የሚመራን የጋራ ትግል ስትራቴጂ የሚነደፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው ብለን እናምናለን።

ከዚህ እይታ በመነሳት በህብረቱ በኩል ስለ መጭው ስብሰባ አካሄድና ተግባር የሚከተሉትን ነጥቦች ለማቅረብ እንወዳለን።

1ኛ. የጉባኤውን ተልእኮና ምንነት በተመለከተ

የዚህ ጉባኤ ዋና ተልእኮ ከፍ ብለን በጠቀስነው መልክ የተለያዩ የህብረተሰብና በፖለቲካውም ሆነ ሌላ መስኮች ለሰፊ አገር አቀፍ ጉባኤና ብሎም ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚታገሉ ሃይሎች ጥረታቸውን ለማስተባበር ስለሚችሉበት ሁኔታ ውይይት የሚካሄድበት የቅድመ ዝግጅት (ፕሬሊሚነሪ) ስብሰባ መልክ እንዲይዝ ሃሳብ እናቀርባለን።

2ኛ. የጉባኤውን አጀንዳ በተመለከተ

ጉባኤው ለዚህ አላማ እስከተጠራ ድረስ በኛ በኩል አጀንዳው

ሀ/ ስለሽግግሩ ትግል አጠቃላይ ውይይት ማካሄድና የጋራ ግንዛቤ ላይ መድረስ

ለ/ የሽግግሩን ትግል ለማጠናከር ለሚደረገው ቀጣይ ጉባኤ ተሳታፊዎች ጉዳይ መወያየት

ሐ/ ለቀጣዩ ጉባኤ ዝግጅት ከሁሉም ድርጅቶች የተውጣጣ የቀውጢ ጊዜ ግብረ ሃይል

መሰየም፤ ስለዚህ ግብረሃይል በተለይም ስለትግል ፕሮግራም፤ መዋቅር ወዘተ ስለሚዘጋጁ ሰነዶችና ሌሎች ተግባራት ዝርዝር መመሪያ ማውጣት

መ/ በጋራ ግንዛቤዎች ተመርኩዞ ስለቀጣዩ ትግል ለህዝባችን አቅጣጫ የሚያመለክት መግለጫ ማውጣት በአጀንዳው ውስጥ እንዲካተት ሃሳብ እናቀርባለን።

3ኛ. የአጀንዳ ረቂቅ ስለመለዋወጥ አስፈላጊነት

ይህ በህብረቱ በኩል የቀረበ የአጀንዳ ረቂቅ በአንድ በኩል የተሟላ ላይሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም አጀንዳ ቢሆን አስቀድሞ ለተሳታፊ ድርጅቶች ተሰራጭቶ ተወያይተውበት በውክልና ለሚልኳቸው ተሳታፊዎች መመሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ተሳታፊ ድርጅቶች ይጠቅማል የሚሉትን የአጀንዳ ረቂቅ ጉባኤውን የማዘጋጀት ሃላፊነት በወሰዱት ወገኖቻችን በኩል ለሌሎቹም ተሳታፊዎች ከጉባኤው በፊት እንዲያስተላልፉ ሃሳብ እናቀርባለን።

4ኛ. ስለጉባኤው ቀንና ቦታ

ጉባኤው ሆላንድ በመደረጉ ብዙ ችግር አይፈጥርም። እንስማማለን። ሆኖም ከፍ ብለን ከተቀስነው ቅ
ድመ ዝግጅት አንፃርም ሆነ ህብረታችን ከጊዜው እጥረት አንፃር ከሚያጋጥሙት ችግሮች የተነሳ የጉባኤው ቀን ቢያንስ
ለሁለት ሳምንታት ያህል ወደ ፊት ቢገፋ ይመረጣል።

## ውይይት በሃገር ጉዳይ! በቁም ነገር!

ከሁለት አመታት ጀምሮ ከሳምንት ሳምንትና ከወር ወር እየተባባሰ በመጣው የሃገራችን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ አሁ
ን ደግሞ በቅንጅት ወገኖቻችን ጎራ የምንታዘበው አሳዛኝ ሁኔታ ሲጨመርበት ጥራት ስንል ውዥንብርን፣ የትግል አንድ
ነት ስንል ክፍፍልን እያገዘ ህዝባችን የታገለላቸውና የተሰዋላቸው የግንቦት ታሪካዊ እሴቶች ሰብሳቢ አጥተው ኢትዮጵ
ያ ባለቤት ያጣች የምትሆንበት አደጋ በአይናችን ስር እየተከሰተ ነው። ለመድበለ ፓርቲ ህብረተሰብ እየታገልን ልዩነቶ
ች አይኑሩ አንልም። ይኖራሉ። መኖርም አለባቸው። ሆኖም አሁን እንደምንታዘበው ከሆነ በተለይ በአንዳንድ ስድ የሆ
ኑና አክራሪ ወገንተኝነት የያዙ ድህረገፆች እየተስተጋቡ አደባባይ ወጥተው ክርክር ሳይሆን እንካስላንትያ የሚካሄድባቸ
ው ነጥቦች ምንም ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ይዘት የላቸውም። የምንታዘበው ያሉት ልዩነቶች ጥቃቅን የአሰራር፣ የሰዎች፣
የገንዘብ፣ የስልጣን .... ልዩነቶች ከሆኑ እንዳሁኑ የህዝባችንን የትግል ቅስም ሊሰብር በሚችል ንትርክ ሳይሆን "ገበና ሳ
ያሳዩ" በውስጥ የሰከነ ውይይት እንዲፈቱ፣ አሉ የሚባሉ ልዩነቶች የፖለቲካ ከሆኑ ደግሞ በህዝብ ፊት በግልፅ ይፋ ወ
ጥተው ውይይት እንዲደረግባቸው አገራዊ ጥራያችንን እናስተላልፍላቸዋለን።

ይህ ጥሪያችን ለነዚህ ወገኖቻችን ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ለሃገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎችም
ነው። ከትግላችን አላማዎች አንዱ በህብረተሰባችን ዴሞክራሲና ተጠያቂነት እንዲሰፍኑ ለማድረግ ነው። ነገር ግን ተ
ጠያቂነትን ከኢህአዴግ መሪዎች ብቻ አንጠይቅም። አንድ ትግል የተዋጣ የሚሆነው ጥሩ መሪዎች ብቻ ሳይሆን ጥሩ
ተመሪዎች ሲኖሩት ነው። ጥሩ ተመሪ ደግሞ የቆመው ለአላማ፣ ለሃገር፣ ለወገን እንጂ ለድርጅትና ለግለሰብ ስላይደለ
ከመሪዎቹም ተጠያቂነትን መጠየቅ አለበት እንላለን። ይህንን ድርጅት በጭፍን፣ ይህንን ግለሰብ በሙሉ እምነት፣ ያንን
ቡድን አይን ጨፍነን እንደግፋለን በሚል ወገንተኛነት ሳይሆን ጎራ ከመለየት በፊት ሁሉም ረጋ ብሎ ምን አቋም? ምን
መስመር? ምን ስትራቴጂ፣ ምን የፖለቲካ ልዩነት ብሎ ራስን መጠየቅ ይኖርበታል።

ዛሬ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረው ችግር ለጠቅላላው ለትግላችን እንዳይተርፍ፣ ዛሬ ካለው ውዥንብር ትግላ
ችንና መስመራችን ጥራት ይዞ እንዲወጣ ከተፈለገ የሃገራችን ዴሞክራቶች የድርጅትንም ሆነ የግለሰብ ተገዥነትን አጥ
ር ሰባብረው "ወዴት እየሄድን ነው? ወዴት እየወሰዳችሁን ነው?" የሚሉትን ጥያቄዎች አቅርበው በቁም ነገር ላይ ያተ
ኮሩ .ክርክሮች እንዲካሄዱ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ወርቅማ ጊዜያችንን እጅ እግር የሌላቸው በሚመስሉ ንትርኮች ስና
ባክን ልብ አላልናቸው እንደሆን እንጂ ዛሬ በሃገራችን ውስብስብ ሁኔታ ትግላችንን፣ ስትራቴጂያችንን ....በተመለከተ ብ
ዙ ውይይትና ጥራት የሚፈልጉ ቁም ነገሮች አሉ። እነዚህ ነጥቦች ምንድን ናው? ከነሱ አንፃር የህብረታችን አቋም ም
ንድን ነው? ከዚህ አካሄድ ውጭ የሚቀርቡት ስትራቴጂዎች ምንድን ናቸው? አደጋቸውስ?

አንደኛ የኛም ሆነ የሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች አላማ ም
ንድን ነው? ደጋግመን እንዳልነው አላማችን ኢትዮጵያን እርቅ ወደወረደበት፣ ዴሞክራሲና ፍትህ ወደ ሰፈኑበት የተረጋ
ጋ ህብረተሰብ የማሸጋገር አላማ ነው። በኛ እምነት ይህ ታሪካዊ ተጋድሎ አንድ ወሳኝ ምእራፍ የሚደርሰውና እውን የ
ሚሆነው በሃገራችን ምድር በሚሰየም በአንድ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ አማካኝነት ስለሆነ ሁላችንም
ይህንን መፌክር አንግበን መታገል ይጠበቅብናል። እንዲህ አይነቱ ጉባኤ በአጠቃላይ በሃገራችን አሉ የሚባሉ የፖለቲ
ካ ሃይሎች፣ የሲቪኩ ማህበራትና የነፃው ፕሬስ ተወካዮች፣ ከየአካባቢው የሚመጡ የሃገር ሽማግሌች ፣ የሃይማኖት
አባቶች፣ የወጣቶች የሴቶች የሙያና ሌሎች ማህበራት ስብሰቦች፣ ምሁራን ወዘተ የሚሳተፉበትና የሃገራችንን እጣ ፈን
ታ ተወያይተው የሚቀይሱበት ጉባኤ ይሆናል። በአማራጭ ፕሮግራማችንም በግልፅ እንደተቀመጠው ሃገራችንን ወደ ዴ

ሞክራሲያዊ ስርአት እናሸጋግር ካልን የዚህ ሃላፊነት በዚህ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለሚመረጥ የዴሞክራታይዜሽን ኮሚሽን
የሚተው ይሆናል። በሃገራችን ትርጉም ያለው ብሄራዊ እርቅ ከተባለ የዚህ ሃላፊነት ደግሞ እንደዚሁ በዚህ ጉባኤ ለሚ
ሰየም "የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን" መተው ይኖርበታል።

ሁለተኛ ይህን ሁሉን አቀፍ የሽግግር ጉባኤ በቅድሚያ በትግልና በህዝብ ድል በተረጋገጠ ዴሞክራሲ ተጠቅሞ
በሰከነ ውይይት የነገይቱን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በጋራ ስምምነት መልክ የሚያስይዝ ጉባኤ እንጂ በሃገሪቱ የሌለ
ዴሞክራሲን "የሚያመጣ" መድረክ አድርገን አናየውም። ። ከዚህ የምንደርስበት መደምደሚያ ግልፅ ነው። ዛሬ ሃገራ
ችን የምትገኝበት ሁኔታ እንኳን እንዲህ አይነቱ ሰፊ ውይይት ቀርቶ በቅድመ ግንቦቱ ወቅት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍን
ጮች ደብዛቸው የጠፋበት፣ የመደራጀት መብት የተነፈገበት፣ በህዝባችን የትግል ተሳትፎ ህገ ወጥ ተአቅቦ የተደረገበ
ት፣ ነፃው ፕሬስ የወደመበት ሁኔታ ነው። እነዚህ መብቶችና ተቋማት ለዚህ ውድመት የበቁት በአጋጣሚ አይደለም።
ከእንግዲህ የኢህአዴግ መሪዎች በስልጣን የመቀየቱ እድል ተንጠልጥሎ የተያዘው ተመልሰው እውን አለመሆናቸውን በ
ማረጋገጥ ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም ያለ መራራ ትግል ተመልሰው እውን ይሆናሉ ብሎ ማለም እነ አቶ መለስ ዜናዊ ከ
ስልጣን ኮርቻቸው በገዛ ፈቃዳቸው ለመውረድ ዝግጁ ይሆናሉ እንደማለት ያህል የኢህአዴግን መሪዎች የአላማ ፅናትና
ቁርጠኝነት ከቁጥር የማያስገባ አደገኛ አስተሳሰብ ነው። በመሆኑም በሃገራችን ትርጉም ያለው ብሄራዊ እርቅና ዴሞክ
ራሲያዊ ሽግግር እውን እንዲሆን በቅድሚያ እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ከያዙት አክራሪ፣ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ሸብርተኛ
አካሄድ ሚልዮኖችን በሚያሳትፍ ህዝባዊ ትግል እንዲያፈገፍጉ መገደድ ይኖርባቸዋል።

ሶስተኛ ከዚህ ከፊታችን አፍጦና አግጦ ከተደቀነው ሃቅ እንነሳ ካልን የህዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ መልሶ
ከትግሉ የመደባለቁ ጉዳይ በዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጎራ እንደ ዋና አጀንዳ መያዝና ጥረታችን ሁሉ ለዚህ መሆን
ይኖርበታል። በዚህ ጉዳይ የኢህአዴግ መሪዎች አቋምና አካሄድ ከፀሃይ ደርቶ የሚታይ ነው። የነሱ ዋና የትግል አጀን
ዳ በቅድመ ግንቦቱም ወቅት ሆነ ከዚያ በተከተሉት ወራት እንደታየው ህዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ ተመልሶ ትግሉ
ውስጥ እንዳይደባለቅባቸው ነው። በመሆኑም ህዝባችንን ይዘን በሰላማዊ ሰልፍም፣ በስራ ማቆም አድማም ሆነ በሌሎች
ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልቶች እየተጠቀምን ወደፊት እንዳንራመድ ዛሬ በሃገራችን ህዝብን ይዞ ታግሎ ማታገል በህ
ገ ወጥነት የተፈረጀ ወንጀል ሆኗል። ሸብርተኞቹ ገዥዎች በዚህ በኩል ያላቸውን ቁርጠኝነት የቅንጅትን መሪዎች "እ
ጅ ተወርች" አስረው ሲፈቷቸው በግልፅ ያሳዩ ይመስለናል። የህዝባችን ተሳትፎ በዚህ መልክ ህገወጥ በሆነ ተአቅቦ በ
ተገደበበት ሁኔታ ይህንን አሻፈረኝ ብሎ ትግሉን ለማፋፋም ቢሞክር እነዚህ የጥፋት ሃይሎች በህዝባችን ላይ በለየለት
አመፅ እንደሚሰማሩበት ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

አራተኛ ከዚህ እውነታ በመነሳት ዛሬ በሃገራችን ህዝብን ይዞ መታገል አስቸጋሪ ነው ለሚሉ ወገኖች ሊኖሩ ይ
ችላሉ። ለነዚህ ወገኖቻችን ያለን መልስ " አወን አስቸጋሪ ነው የኢትዮጵያችን የነፃነት ተጋድሎ የአልጋ ባልጋ ጉዞ ሆ
ኖም አያውቅ፣ አይደለም ወደፊትም አይሆንምም" የሚል ነው። እንዲያውም የትግል ስትራቴጂያችንን ለመንደፍ ስንነ
ሳ መንደርደሪያ አድርገን የምንወስደው ይህንን መራራ ሃቅ አስቀድመን በመቀበል ከዚህ የሚፈልቁትን የአላማ ፅናት፣
የትግል አንድነት ወዘተ የመሳሰሉትን እሴቶች በማንገብ ነው እንላቸዋለን። ከዚያ አልፈው በዚህ ሁኔታ እንዲህ አይነቱ
ህዝባዊ ትግል "አይቻልም" ለማለት ለሚቃጣቸው ሃይሎች እንዳሉም የዚያኑ ያህል ግልፅ ነው። ለነዚህ ደግሞ ያለን
አጭር መልስ የሃገር ህልውና፣ የሃገር ሰላም፣ የሃገር አንድነትና ብልፅግና ጉዳይ ስለሆነ "መቻል አለበት" የሚልና ላለ
ው ሽብርተኛ አገዛዝ የሚመጥን የጋራ ትግል ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልገናል የሚል ብቻ ይሆናል። "መቻል አለበት"
ብለን ከተነሳን ደግሞ በአድርባይነትም ሆነ በትግሉ ከባድነት ተሸንፈው ህዝባችንን ይዞ መታገል አይቻልም የሚለውን
ተንበርካኪ እምነታቸውን ለመሸፋፈን ሲሉ ብቻ ይህ አይነቱ ትግል "አያስፈልግም" ሌላ የተሻለ፣ የሰለጠነና የሰከነ የ
ድርድር፣ የሽምግልና፣ የአለም አቀፍ ጫና የሚሉ አካሄድ አለን የሚሉ ሃይሎችን ለትግላችን ጥራት፣ አንድነትና ጥንካ
ሬ ስንል ልንታገላቸው ይገባናል።

እንዲያውም በቅንጅቱ ውስጥ የፖለቲካ ልዩነቶች አሉ ከተባለ ሌላ ሌላውን ሁሉ ትተን እነዚህ ልዩነቶች ከዚ
ህ የሃገራችን ዴሞክራቶችና ሃገር ወዳድ ሃይሎች ፅኑ አላማና የጋራ ስትራቴጂ አንግበ እየተፈተሹ ማን ከህዝብ ወገን ቆ
ሞ ህዝባን ይዤ ልታገል እንደሚል ማን ደግሞ ህዝባዊውን ትግል የሚያዘናጋ አካሄድ እንደያዘ ግልጥልጥ ብሎ የሚወ

ጣበት በቁም ነገር ላይ ያተኮረ ክርክር እንዲካሄድ ይህንን አሻፈረኝ ብሎ ደግሞ ከክርክር ለመሸሽ የሚሞክር ወገን ካለ ደግሞ በህዝብ ፊት በትግል እንቅፋትነቱ እንዲጋለጥ መጣር አስፈላጊ ይሆናል።

ክርክር የግድ የሚሆንበት ምክንያት ለኛ በጣም ግልፅ ነው። ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ''ጥቃቅን'' ሊባሉና በማንታረክ ላይ ካሉት ልዩነቶች በስተጀርባ ባለፉት ሁለት አመታት ከታማኝ ''ተቃዋሚዎች'' ጎራ ሲንፀባረቅ የቆየው ትግል አዘናጊ አቋም ''በሰለጠነ ፖለቲካ'' ሰበብ መልሶ በሌሎች ሊቀርብልን ዳር ዳር እየተባለ እያየን ነው። ይህ ''የትግል'' ስትራቴጂ የኢህአዴግ መሪዎች በሽብር የጨበጡትን ስልጣን በድርድር፣ በብሄራዊ እርቅ መንፈስ፣ በሃገር ሽማግሎች ጥረትና በአለም አቀፉ ጫና አስለቅቀን የሃገራችንን ችግሮች የህዝባዊ ትግል ''ጫጫታና ግርግር'' ሳያስፈልገን በሰከነና ''በሰለጠነ'' ፖለቲካ እንፈታለን የሚል ከፍ ብለን እንደጠቀምነው የፀረ ህዝቦቹን የአላማ ጥራትና ቁርጠኝነት ከቁጥር የማያስገባ እጅግ አደገኛና ትግል አዘናጊ አካሄድ ነው። አሁን ዳርዳር እንደሚባለው ከሆነ የዚህ ሴረኛ አካሄድ ሁለት ምእራፎች ወይም ''መቋጠሪያዎች'' እየታቀዱለት እንደሆነ የሚጠቁሙ አንዳንድ ክስተቶች እየታዩ ነው።

በአንድ በኩል በህዝባዊነታቸው ፀንተው የቆሙትን ሃይሎች ''በአክራሪነት'' ፈርጆ በሚያገልል ሁኔታ የሃገራችንን ችግሮች አንዳንድ ተቃዋሚ ተብየዎችን፣ የኢህአዴግ ተወካዮችን፣ የሃገር ''ሽማግሎችንና'' አንዳንድ ባእዳንን ባካተቱ ድርድር ተብየ መመሳጠሮች አማካኝነት ''ለመፍታት'' ሙከራዎች እየተደረጉ ናቸው። በመሞከር ላይ ያለው አጥፊ ሂደት በነዚህ ማንም ባለወከላቸው ሃይሎች መሃከል ስለቀጣዩ ምርጫ ''የሆነ ስምምነት'' እንዲደረስና በዚህ መልክ የግንቦት ታሪካዊ የትግል ምእራፍ ስርአተ ቀብር ተካሂዶ ''ዴሞክራሲ በሂደት'' በሚል ሰበብ ህዝባችን ከምርጫ ምርጫ እየተንከራተተ በአልሆነ አቅጣጫ እንዲኳትን የሚጋብዝ አደገኛ ሴራ ነው። በእንዲህ አይነቱ ህብረተሰቡን አግልሎ በፀረ ህዝቦቹና ማንንም በማይወክሉ ''ተቃዋሚዎች'' መሃከል በፈረንጆቹ አማካኝነት በሚደረግ መደራደር/መመሳጠር የሃገራችን ችግር ይፈታል ማለት የስመ ጥፉውን የለንደን ኮንፈራንስ አደገኛ አካሄድ መድገም ስለሚሆን ህዝባችንን ይዘን በአንድ የተባበረና የጋራ ድምፅ ''አድርሰናል'' ማለት ይኖርብናል። እንዲህ አይነቱ ''አሻፈረን'' ባይነት ብቻውን ለንደን ላይ የትም እንዳላደረሰን ሁሉ ዛሬም የትም አያደርሰንም።

የለንደን ኮንፈራንስ ለምን በተካሄደበት መልክ ተካሂዶ ለሃገራችን የጥፋት ምእራፍ ለመክፈት ቻለ? በዚያም የታሪክ ወቅት የሃገር አንድነት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የብሃራዊ ክብር አጀንዳ ልክ እንደዛሬው ሚልዮኖች ከዳር እስከ ዳር ያነገቡት አጀንዳና ህልም ነበር። ሆኖም በዚህ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያችን እጣ ፈንታ በጥቂቶች ሲወሰን ይህ የህዝብ ራእይና አጀንዳ - ከተበታተኑ ሚልዮኖች በስተቀር - ተአማኒነት ያለው ሰብሳቢ ሃይል ስላልነበረው ሰላሟና ዴሞክራሲዋ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ አንድነቷንና ህልውናዋን እንኳን የቅድሚያ ቅድሚያቸው ባልሆኑ ሃይሎች ብቻ ተወሰነ።

ዛሬም ቢሆን እነዚህ እሴቶች የሚልዮኖች ናቸውና.....እያልን የምንዘናጋበት ምንም ምክንያት የለም። የሚልዮኖች ህልም በጥቂቶች ሴራ ለጊዜውም ቢሆን እንደ ለንደኑ ሊጠለፍ ይችላል። ደጋግመን ለመጠቆም እንደሞከርነው ዛሬም እንደትላንቱ በግንቦት 97 ሳቢያ ህዝባችን ጥማቱን ብቻ ሳይሆን ብቁነቱን ያሳየባቸውን የአንድነት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የፍትህ እሴቶች ሰብሳቢ ሃይል እንዲያጡና ''የሽግግር ክፍተት'' እንዲፈጠር እየተሞከረ ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች በጋራ መቆማቸውን ትተው በምንም ምክንያት ይሁን በምን እንዲህ አይነቱ መዘዘኛ ሴራ እንዲቀጥልና እንዲሳካ ከፈቀዱና እንደ ለንደኑ ወቅት ይቺ አገር ባለቤት ያጣች ወና ቤት ከሆነች የየካቲት ቅልበሳ የጀመረውን ፈተና ግንቦት ሊጨርሰው የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህንን ከፍተኛ አደጋ ለመከላከል በህዝባችን እሴቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች በፀረ ህዝቦቹ ከመቀደማቸው በፊት የኢትዮጵያችን እጣ ፈንታ ሲወሰን ማንም ሊያልፈው የማይችል በህዝባችንም ፊት ሆነ በማንም ይሁን በማን አይን ተአማኒነት ያለው ሰፊ የጋራ መድረክ የማቋቋሙ ጉዳይ እጅግ አጣዳፊ ተግባርና አገራዊ ግዴታ ነው እንላለን።

ዛሬ በቅንጅት የተለያዩ ክፍሎችም ሆነ በጠቅላላው በተቃዋሚው ጎራ ልዩነት፣ ክርክር ወዘተ አለ ከተባለ በነዚህ ቁምነገሮች ላይና በጠራ መስመር በጋራ ስለመታገል ጉዳይ ሁሉም ያለውን አቋም በግልፅ አንግቦ እንዲከራከር መጋበዝም አሻፈረኝ ካለ ደግሞ መገደድም ይኖርበታል። እንዲህ አይነቱ የሰከነ ውይይትና ክርክር ለቀጣዩ ትግል ወሳኝ የሚ

ሆነውን ያህል በአንዳንድ ወገኖቻችን በኩል ከዚህ አይነቱ ጤናማ ሂደት የመሸሽ ሁኔታ እንዳለ ባለፉት ሁለት አመታ
ት ስንታዘብ ቆይተናል። በአዳራሽ ስብሰባዎችም፣ በነፃ ሬድዮኖችም፣ በተለያዩ የውይይት መድረኮችም በህዝብ ፊት
እንከራከር ስንል፣ ወሳኝ ወደ ሆነው ወደ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ እንስራ እያልን "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ" ቢልም ዛሬ ድምፅ
ለሌለው ህዝባችን ድምፅ ሆነን እርሮ ስናማ ይህ ሁሉ ጆሮ ዳባ ሲባል ቆይቷል። ለትግላችን ጥራት ሲባል ይህ ከእንግ
ዲህ መቆም ያለበት እንላለን። ዛሬ ካለንበት አደገኛ ውዥንብር ወጥተን ለሃገራችን አንድ ቁምነገር እንስራ የሚል ዜጋ
ሁሉ በያለበት በትርኪ ምርኪውና በአልባሌ ነጥቦች ላይ መራኮቱን ትቶ በነዚህ ቁም ነገሮች ላይ ብቻ የሰከነ ክርክር
እንዲካሄድ መጠየቅ የዜግነት መብቱና የታጋይነት ግዴታው ነው። አንዳንዶች ትግላችንንና ሃገራችንን በጥፋት ጎዳና
ይዘው ለመንጎድ ቢሞክሩ ታጋዩ ህዝብ ይህንን አሻፈረን ብሎ፣ ተስፋ አስቆርጦ በሃገር ጉዳይ በቁም ነገር የሰከነ ውይይ
ት እንዲካሄድ ሁሉም የተቻለውን አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል። ህብረታችን የትም ቢሆን፣ በየትኛውም ጊዜና ቦ
ታ ለእንዲህ አይነቱ ጤናማ ውይይትና ከዚህ ብቻ ሊፈልቅ ለሚችለው የጋራ ትግል መድረክ የሚጠበቅበትን ሃገራዊ ግ
ዳታ ለመወጣት እንደ ምንጊዜውም ዛሬም ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት

## ነገ በአለቀ ሰአት ከመንደፋደፍ...........

"ዛሬ በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ትግል ማንም የፖለቲካ ሃይልም ሆነ ስብስብ የሚያወጣ
ው ስትራቴጂ በአጥፊነትም ሆነ በአልሚነት የሚመዘነው ከነዚህ ድሎች አንፃር በሚወስደው አቋም ነው። ከዚህ አንፃ
ር ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ህልማቸው የህዝብ ድምፅ ሰርቀው ለሌላ አምስት አመት በስልጣን
ላይ ለመቆየት ብቻ የሚጥር ህልም አይደለም። ዛሬ በአይናችን ስር እየተካሄደ ካለው ዘግናኝ የሽብር ውርጅብኝ ባሻገ
ር ሙከራቸው ህብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ብቁ ያደረጉትን በመስዋእትነት የተገነቡ እነዚህን ተቋማት በማ
ፈራረስና በህዝባችን ስነ ልቡና የሰረፁትን በጎ የአስተሳሰብ ለውጦች በማውደም የዛሬ ሃያም ሰላሳም አመት የነበረውን '
'የሽግግር ክፍተት" መልሶ እውን ለማድረግ የሚጥር መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ ነው።"

እነዚህ መስመሮች የተፃፉት ድርጅታችን ከሶስት አመታት በፊት ኢዴሃህ ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተ
ባለው ስብስብ ለተመሰረተበት ለዩክሬክት (ሆላንድ) ስብሰባ ባስተላለፈው የአቋም መግለጫ ሰነድ ነበር። ከዚያን ወዲህ
አገራችን ምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች? በሰነዱ እንደተባለው የቅድመ ግንቦቱ ተቋማት ፈራርሰው፣ ነፃ ፕሬሱ ደብዛው ጠ
ፍቶ፣ የድርጅት ነፃነት እንዳልነበረ ሆኖ ተኮላሽቶ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ጨለምተኝነትና ትጥቅ መፍታት በሰፈነበት
ህብረተሰብ በሰላም፣ በሃገር አንድነት፣ በህዝቦች ወንድማማችነት፣ በሰላም፣ በብሄራዊ እርቅ ዙሪያ ተቃኝተው የነበሩ
ት የግንቦት እሴቶች ከእለት እለት እየከሰሙ የሚሄዱበት ሁኔታ ተመቻችቶ እናያለን። ይህ ዛሬ ያለው ሁኔታ ነው። በ
መጭው ጊዜ ደግሞ እዛው በዛው በሽብርና በአመራር ክፍተት ግራ በተጋባና የትግል ቅስሙ በተሰበረ ህብረተሰብ ውስ
ጥ የቅልበሳው ዋንኛ መዘዝ የሆኑት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች እየከፉና እየሰፉ መሄዳቸው አይቀሬ ነው።

እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ከዚህ ዛሬ አስቸጋሪና ነገ ደግሞ ውጥንቅጡ የወጣ ሊሆ
ን ከሚችል ሁኔታ ለመውጣት ከተነሳንና ለወደቀብን አገር አድን ታሪካዊ ሃላፊነት ብቁ ለመሆን ከፈለግን ስትራቴጂያች
ን ከግንቦት አሸብራቂ ህዝባዊ ድሎች አንፃር ዛሬ በሃገሪቱ ካለው ተጨባጭ የሃይሎች አሰላለፍ መነሳትና በዚህ አሰላለ
ፍ ውስጥ የኛና የህዝባችን ቦታ የት ላይ እንደሆነ ጠንቅቀን ማወቅ ይጠበቅብናል። ከነዚህ ህዝባችን በሚልዮን እየተቆ
ጠረና አይከፍሉ መስዋእትነት እየከፈለ ከገነባቸውና በነቂስ ወጥቶ ትግሬዩ ለትግራይ፣ ኦሮሞው ለኦሮሞ፣ አማራው ለአ
ማራ፣ ክርስቲያኑ ለክርስቲያን፣ እስላሙ ለሙስሊም ሳይል "ለአንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ" ብሎ በሬፈራንደም
ካፀደቃቸው የዴሞክራሲ፣ የሰላም፣ የብሄራዊ እርቅ፣ የህዝቦች ወንድማማችነት እሴቶች አንፃር በፖለቲካውና በትግ

ሉ መድረክ ዛሬ ያለው ተጨባጭ የሃይል ሚዛን ለፀረ ህዝቦችና ፀረ ኢትዮድያ ሃይሎች የሚያደላ ቢሆንም በፍጥጫ ላ
ይ ያሉት ዋና ዋና ሃይሎች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያው በወያኔ መሩ ኢህአዴግ የሚወከለው የግንቦት ቀልባሾች ጎራ ነው። ይህ ጎራ የግንቦትን የህዝብ
ድሎች አሻፈረኝ ብሎ፣ ህዝቡ ለዴሞክራሲ ሳይሆን ለአፋኝ አገዛዜ ድምፁን ሰጥቷል ብሎ ሸፍጦ፣ ህዝባችን የዘረጋለ
ትን የሰላምና የብሄራዊ እርቅ እጅ አሻፈረኝ ብሎ ሃገራችንን የብዙሃን ሲኦል፣ የጥቂቶች ገነታዊ ደሴት ለማድረግ በለየ
ለት የሸብር አገዛዝ የተሰማራ ሃይል ነው። ሌላው ጎራ በግንቦት እሴቶቹ ዙሪያ ሚልዮኖችን የሚያካትት ከህዝባችን ጎን
የቆሙ የዴሞክራሲና የአገር ፍቅር ሃይሎች የተሰለፉበት ጎራ ነው። ከዴሞክራሲ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎች
አልፎ ተርፎ በሃገራችን በኢትዮድያ ህልውናም ጉዳይ በእነዚህ ሁለት ሃይሎች መሃከል እየተካሄደ ባለው ታሪካዊ ትን
ንቅ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ያላቸው ሃይሎች ናቸው።

የወያኔ/ኢህአዴግ ሰፈር ድክመቱና ጥንካሬው ምንድን ነው? ትልቁና ምን ጊዜም ሊወጣው የማይችለው ድክመ
ቱ እየተገነባ ያለው ግፈኛ ስርአት በሚልዮኖች ጥቅምና ህልውና መቃብር ላይ በአምቻ ጋብቻ፣ በዘመድ አዝማድና በ
ዙሪያቸው ለተኮለኮሉ ጥቂቶች የቆመ ግፈኛ ስርአት እንደመሆኑ መጠን በምንም አይነት ህዝባዊ ድጋፍ ሊያገኝ የማይ
ችል መሆኑ ነው። ሆኖም ይህንን "ለማካካስ" በሚያደርገው ጥረት የመንግስት ፋይናንስ መቆጣጠሩ፣ የጦርና የፖሊስ ሰ
ራዊት ማደረጀቱ፣ የሰለላ መዋቅሩን በመላ ሃገሪቱ መዘርጋቱ፣ አገር እየሸጠም ሆነ ለፖለቲካ ደላላዎች በሎቢ ስም በ
ሚልዮን የሚቆጠር ሃብት በማፍሰስ የባእዳን ድጋፍ ማረጋገጡ ወዘተ  የማይናቁ "የጥንካሬ" ምንጮች እንደሆኑ መካድ
አይቻልም። ይህ ፀረ ህዝብ ሃይል ይህንን አቅሙን ከእለት እለት እያዳበረ ለመሄድ ከሚያደርገው ሙከራ በተጓዳኝ የ
ዴሞክራቶች፣ አገር ወዳዶችና በጠቅላላውም የህዝቡን ሰፈር ለማዳከም በሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎች ተሰማርቶ እናየ
ዋለን።

አንደኛው አቅጣጫ ህዝባችን በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ተንቀሳቅሶ እንዳያስቸግረው በለየለት ሸብር ከመሰማራ
ት አልፎ በየጊዜው ከነዚህ እሴቶች ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውና እንዲያውም እነሱን የሚቃረኑ የተለያዩ አጀንዳዎ
ች ለህብረተሰቡ እያስጨበጠ በነሱ ዙሪያ እርስ በእርስ እንዲባላ ለማድረግ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የአካባቢ ግጭቶች እየ
ተበራከቱ እንዲሄዱ ማድረግ ነው። ሁለተኛ ስትራቴጂው ደግሞ ግንባር ቀደሙ ሃይል ተባብሮና በአንድነት ቆሞ ለዚህ
ህዝባዊ ትግል ብቁ የሆነ አመራር እንዳይሰጥ በአለው የገንዘብ አቅም በሚገዛቸውና "በታማኝ ተቃዋሚነት" በሚያሰል
ፋቸው ደካሞችና በሚያሰማራቸው ሰላዮች አማካኝነት የሃቀኛ ዴሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ሰፈር ማበጣበጥ፣ መከ
ፋፈልና ማዳከም ሆኖ እናገኘዋለን።

ከዚህ የግንቦት ቀልባሾች "የጥንካሬ" ሁኔታና የጥፋት ስትራቴጂ አንፃር በግንቦት ሃይሎች አካባቢ ምንም የእ
ይታ ችግር ያለ አይመስለንም። የኛን የጥንካሬና የእነሱን ወሳኝ የሆነ የድክመት ምንጭ ምን እንደሆነም እናውቀዋለን።
እንደ እነሱ የመንግስት ካዝና አንቆጣጠርም፣ እንደ እነሱ የዳበረ የጦርና የፖሊስ ሰራዊት የለንም፣ እንደ እነሱ ሃገሪቱ
ን በሰላዮች መዋቅር አላባበስንም፣ አገር ወዳዶችና "ኢትዮድያዊነት" ብለን ለዚች አገር ነፃነት፣ ለዚች አገር አንድነት
ና ክብር ቆመናልና እንደነሱ ለባእዳን በባንዳነት አድረን ድጋፋቸውን አንጠይቅም አናገኝምም። ግን ደግሞ ዴሞክራቶ
ችና ሃገር ወዳዶች ነንና እነሱ ምን ቢሉ ምን መቼም ይሁን መቼ ሊደርሱበት የማይችሉትን ህዝባዊ ሃይል ለማንቀሳቀስ
የምንችል ነን። ከዚህም በመነሳት ስለ ግንቦት ድሎችና እሴቶች በተነሳ ቁጥር፣ እነዚህ ድሎችና ዛሬ በተከላካይነት ያ
ሉትን እሴቶች መልሶ በሃገራችን ለማንገስ በሚደረገው ትግል ግልፅ የሆነ ስትራቴጂ አለን።

የግንቦት ድሎች የሚልዮኖች ትግል ውጤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የግንቦት ድሎች ህዝባችን በነቂስ ወጥ
ቶ እያንዳንዱ/እያንዳንዷ ዜጋ የእጣ ፈንታቸው ባለቤትነት ተሰምቷቸው ከዳር ዳር ተንቀሳቅሰው ያስመዘገቧቸው ድሎ
ች እንደመሆናቸው መጠን፣ ቅልበሳ ሲባል ደግሞ ዛሬ በተጨባጭ እንደሚታየው የመዘዞቹን ገፈት የሚቀምሱት እነሱ
እንደመሆናቸው መጠን የትግላችን ስትራቴጂ የማእዘን ዲንጋይ ዛሬ ከትግሉ መድረክ በሸብርና በአመራር ክፍተት የተገ
ለሉትን ሚልዮኖች መልሶ የእጣ ፈንታቸውና የትግሉ ባለቤት ማድረግ እንደሆነ አጠቃላይ ስምምነት አለ። ይህንን እው
ን ለማድረግ ደግሞ ቀልባሾቹ ሊያፍኑት፣ ሊያተራምሱትና በህዝብ ፊት ተአማኒነት ሊያሳጡት የሚሞክሩትን የዴሞክራ
ቶችና የሃገር ወዳዶች ግንባር ቀደም ሃይል በጋራ ስትራቴጂና በጋራ ታግሎ አታጋይ አካል አማካኝነት በአንድ አቅጣጫ

ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል የሚለውን የታሪክ ግዴታ ተቀብያለሁ እያለ ለዚህ እውንነት ጥረት አደርጋለሁ የማይል የፖለቲካም ሆነ ሌላ ስብስብ እስካሁን አላጋጠመንም። ከዚህም ተያይዞ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎች፣ የሙያ ማህበራት፣ የሴቶችና የወጣቶች ስብስቦች ተወካዮች፣ የሃይማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሌዎች በአጠቃላይ የዚች አገራችን ዴሞክራሲና ህልውና ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በአንድ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ አማካኝነት እንዲሰባሰቡ እስከዛሬ ተግባራዊ አልሆነም እንጂ ከየአቅጣጫው ጥሪዎች ሲስተጋቡ አመታት እየተቆጠሩ ነው። አሁንም ቢሆን የቀልባሾቹን ፀረ ህዝብ ስትራቴጂ ለማክሸፍ፣ ህዝባችንን ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው አመራር አሳይቶ መልሶ የትግሉ ባለቤት ለማድረግ ከዚህ ሌላ ምንም መፍትሄ እንደሌለ ስለምናምን ይህንን ወሳኝ የሆነ እርምጃ እንዳንወስድ አንቀው የያዙን አባዜዎች ምንድን ናቸው የሚለውን ጥያቄ አንስቶ ተገቢ መልስ መስጠት አስፈላጊ ይመስለናል።

የብዙ ወገኖቻችንን አስተሳሰብ የሚነሳው "የቆምንለት ቅዱስ አላማ ሚልዮኖች ከዳር እስከዳር የቆሙለትና የሚጋሩት ራእይ ነው" ከሚለው ትክክለኛ ግንዛቤ ነው። ከዚህም በመነሳት የግንቦት ቅልበሳ የፈጠራቸውና እያባባሳቸው የሚሄዱት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች እየከፉና እየሰፉ ሲሄዱ "ጊዜው ሲመጣ ሁኔታው ሲፈቅድ" እነዚህ ሚልዮኖች ወሳኝና ሚዛን የሚደፋ ሃይላቸውን በማንቀሳቀስ ይህንን የጥፋት ሂደት መግታታቸው አይቀሬ የሆነ የታሪክ ሂደትና ሃቅ ነው የሚል ለተጠናወተን መዘናጋትና ዳተኝነት በር የከፈተ ጨርሶ አደገኛ የሆነ አስተሳሰብ የሰፈነ ይመስላል። እንዲህ አይነቱ ስሌት ቀጣይነትና ተአማኒነት ያለው አመራር በጎደለበት ሁኔታ ቀውሶች እየተበራከቱና እየከፉ ሲሄዱ አንድ ህብረተሰብ ለነዚህ ቀውሶች ጤናማ የሆነ አፀፋ ለመስጠት ያለው ፍላጎትና አቅም እየሟሸሸ እንደሚሄድ ከኛ ከራሳችን ከየካቲት ቅልበሳ ታሪክም ሆነ ዛሬ ከግንቦት ወዲህ በአይናችን ስር እየሰፈነ ካለው ሁኔታም ምንም ትምህርት ያልቀሰመ አካሄድ ነው።

በግንቦት 83 በሃገራችን ከደርግ ወደ ወያኔ አገዛዝ ሽግግር ሲደረግ ሚልዮኖች በአመታት የአፈና አገዛዝ የትግል ቅስማቸው ተሰብሮ፣ ይህ ነው በማይባሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች ህልውናቸው ጥያቄ ውስጥ ገብቶ፣ የካቲት ላይ ህዝባችን በመስዋእትነት ገንብቷቸው የነበሩት እዛው በዛው የትግሉ አራማጅም የትግሉ ውጤትም የነበሩት ተቋማቱ ፈራርሰው፣ ከዚህም ተያይዞ የካቲት ላይ አንግቦ የተንቀሳቀሰላቸው የዴሞክራሲ፣ የማህበራዊ ፍትህ፣ የሃገር አንድነትና የህዝቦች ወንድማማችነት እሴቶች ሁነኛ ሰብሳቢ ሃይል አጥተው የተንሳፈፉበት ሁኔታ ነበር። በዚያን ወቅት ወያኔ/ኢህአዴግና ሻብያ ዘው ብለው የገቡበት "የኢትዮጵያዊነትና" የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ተቋማት ክፍተት ነበር። ያኔ ህዝባችን በሚልዮን እየተቆጠረ ለእነዚህ ክቡር እሴቶች መቆሙ ይህ ብቻውን ለዚች አገራችን ዴሞክራሲን፣ ሰላምን፣ አንድነትን አላመጣላትም። ጥቂቶች ለንደን ላይ በር ዘግተው፣ ከባእዳን ተመሳጥረው የሃገራችንን ህልውና ጉዳይ ሲወስኑ፣ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ እንኳን ማንም ኢትዮጵያዊ ሊያስበው ቀርቶ ሊያልመው በማይችል ሁኔታ አዲስ አበባ የተቀመጠ መአከላዊ መንግስት ኤርትራን ገንጥሉልኝ ብሎ ለተመድ ማመልከቻ ሲያቀርብ እንኳን የኢትዮጵያ ህዝብ ሆ ብሎ ከዳር እስከዳር አልተነሳም። ይህ የሆነው ግን ህዝባችን ይህንን አካሄድ ስለፈቀደው ሳይሆን በእነዚህ እሴቶች ዙሪያ ሰብሳቢና የትግል አቀናባሪ ሃይል አጥቶ ቆሽቱ እያረረ አንገቱን ለመድፋት ስለተገደደ ብቻ ነበር።

በተያዘው አካሄድ ከተቀጠለ ዛሬም ቢሆን ሌላ ነገር መጠበቅ አይቻልም። የግንቦት እሴቶች በህዝባችን ከዳር እስከዳር ተቀባይነት ማግኘታቸው ብቻውን ሃያልና የማይበገሩ አያደርጋቸውም። እነዚህ ሚልዮኖችና ሃገራዊ ራእያቸው ሰብሳቢ ሃይል እስካጡ ድረስ ዛሬ እየተንፀባረቀ ያለው "የኢትዮጵያዊነት" ክፍተት እየሰፋና እየከፋ መሄዱ አይቀሬ ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ እኛና ህዝባችን ሳንሆን የግንቦት ቀልባሾች፣ የግንቦትን እሴቶች "የኛ" የማይሉ ሃይሎችና እንዲሁም የቅርብና የሩቅ ባእዳን የትግሉ ዋና ተዋንያን ሆነው ብቅ የሚሉበትና ብቻቸውን የሃገራችንንና የህዝባችንን እጣ ፈንታ በአሻቸውና እንዳሻቸው ሊወስኑ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ለሚንፀባረቀው መዘናጋትና አደገኛ የዳተኝነት አባዜ ሊሰጥ የሚችል ሌላው ምክንያት ጊዜ ለእኛ ሳይሆን ለቀልባሾቹ የሚሰራ መሆኑን ያለመገንዘብ ችግር ይመስለናል። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የህዝቡን ሰፈር ለማተራመስና ለማዳከም የሚጠቀሙበት መሳሪያ ሽብር ብቻ አይደለም። ከፍ ብለን እንደጠቀምነው ህብረተሰባችን ይበልጥ በውዥንብር ውስጥ እንዲዘፈቅ፣ ነገ ይበልጥ ተግባብቶና ተስማምቶ በአንድነት እንዳይነሳባቸው ቅስሙን ለመስበር ሁሉም ደም ተቃብቶ ሁሉም ተያይዞ የሚዳከምበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሌት ተቀን የሚሰሩበት ሁኔታ ውስጥ ነን። በአጭሩ ህዝባዊ

ው ሰፊር ተአማኒነት ያለው የጋራ የሆነ ህዝባዊ አመራር እስካላገኘ ድረስ ከጊዜና ከቅልበሳው ስር እየሰደደ መሄድ ጋር
እየተፋፋሙ የሚሄዱት ግጭቶች በግልፅ ህዝባዊና ፀረ ህዝብ አጀንዳዎችና አማራጮች ዙሪያ አይሆኑም። ከቀዝቃዛ
ው ጦርነት ማከተም ወዲህ በአፍሪካ ከአራት ሚልዮን በላይ ህይወት የቀሰፉትን የመሳሪያ፣ የድረግና የማእድን ኮንትሮ
ባንድ ነጋዴዎች ገብተው የሚፈተፍቱባቸውን እጅ እግር የሌላቸው ግጭቶች ሰላሳና አርባ አመታት ቀደም ብለው ይካ
ሄዱ እንደነበሩት ትግሎች ግልፅና አገር አቀፍ በሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የሚካሄዱ
አይደሉም። እኛም አገር ቢሆን ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ ከዚህ ሌላ ምንም መጠበቅ አይቻልም። የኢትዮጵያ ዴሞክ
ራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች በጋራ ቆመው ታሪካዊ ግዴታቸውን ለመወጣት እስካልተነሳሱ ድረስ በመጭው ጊዜ በእኛ
ም አገር እነዚህ እጅ እግር የሌላቸው ትርምሶች እየተበራከቱ ቀስ በቀስ የህዝባችንንና የሃገራችንን ህልውና ጉዳይ “መ
መለሻ የሌላቸው” የቀውስ አዙሪቶች ውስጥ ሊከቷቸው እንደሚችሉ መገንዘብ የግድ ይሆናል። ይህ ማለት ደግሞ ዛሬ
በይደር እያስቀመጥነው ያለው የታጋዮች ህብረት ጉዳይ ከጊዜ ጋር በሃገር አንድነት፣ በብሄሮች መብትና በሃይማኖት ል
ዩነቶች ስም የሚነሱ አክራሪዎች እያየሉ የሚሄዱበትና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ለብሄሮች መብት ለሃይማኖት እኩ
ልነት ለቆሙ ሃቀኛ ዴሞክራቶች ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነ ድሮውንም ቢሆን አልጋ በአልጋ ያልሆነው ትግላችን ከእለት
እለት ይበልጡን የአቀበት ጉዞ እየሆነ ሊሄድ የሚችልበት አደጋ እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይህንን ጠንቅቀን ተገንዝበናል ካልን የወቅቱ ዋና ጥያቄ ከፍ ብለን እንዳልነው ዛሬ ከትግሉ መድረክ የተገፉት
ሚልዮኖች መልሰው የትግሉና የእጣ ፈንታቸው ባለቤት እንዲሆኑ ተአማኒነት ያለው የጋራ አመራር ለመስጠት በአስቸ
ኳይ መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ይህንን ተአማኒነት ያለው የጋራ አመራር እውን ለማድረግ “በአንድነት ተነስ” እያልን ለ
ምንጠራው ህዝባችን መጀመሪያ እኛ ከመጠላለፍ ይልቅ ተደጋግፈን በአንድነት በመቆም አርአያነት ማሳየት ይጠበቅብ
ናል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የቅድሚያ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ጉዳይ ደግመን ደጋግመን እንዳልነው አንድ ሁሉን
አቀፍ ጉባኤ በመጥራት የጋራ ስትራቴጂያችን የሚንፀባረቅበት የትግል ሰነድ ተወያይተን ማፅደቅ፣ ይህንን ሰነድ ተግባ
ራዊ ለማድረግ የሚደገውን ትግል ለማቀነባበር አንድ የጋራ ታግሎ አታጋይ አካል መሰየም ትላንትና አጣዳፊ የነበረና ዛ
ሬ ይበልጥ አንገብጋቢ የሆነ ተግባር ብቻ አይመስለንም። በአደገኛ ዳተኝነት ጉዞ ከቀጠልን በቀውሶች መክፋትና መበራ
ከት የተነሳ ነገ ደግሞ ጨርሶ የማይታሰብ የሚሆንበት አደጋ ውስጥ ነን። በመሆኑም ነገ በባከነ ሰአት ሃገራችንን ለማዳን
አጉል ከመንደፋደፍ ዛሬውኑ በዚህ በዴሞክራቶችና በሃገር ወዳዶች ሰፊር ሳር ቅጠሉ እደግፈዋለሁ በሚለው የሁሉን
አቀፍ ጉባኤ ጉዳይ ተጨባጭ እርምጃዎችን መውሰድ መጀመር ያስፈልጋል።ባለቤት እንዳጣ መቀጠል የለበትም።

ኢዴሃህ ዛሬ ሃገራችን ካለችበት ፈታኝ ሁኔታ እንድትወጣ ከተፈለገ ይህ የታጋዮች በአንድ ግልፅ አጀንዳ ዙሪ
ያ መሰባሰብ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው ብሎ ያምናል። በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ በሰየመው ልዩ
ግብረሃይል አማካኝነት ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች ጋር ላለፉት ወራት ሰፊ ምክክሮች
አካሂዷል። አሁንም እያካሄደ ይገኛል። ይህ የሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጉዳይ የሃገራችንን ዴሞክራቶች በሙሉ የሚመለከ
ት ሰፊ አጀንዳ በመሆኑም አንዱ ጋባዥ ሌላው ተጋባዥ ሳይሆን ገና ከጥንስሱ በዚህ ጉዳይ ይፋ አቋም የገለፁና ጥሪ ያ
ስተጋቡ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ስብስቦች፣ የሃገር ሽማግሌዎች ወዘተ ተወያይተው አንድ ጉዳዩን የሚከታተል የ
ጋራ ግብረ ሃይል ማቋቋማቸው በምንም አይነት በይደር የሚተው ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም እስካሁን በዚህ ጉዳይ
ጥሪ ሲያስተላልፉ የቆዩ ወገኖች በዙሪያቸው ከአሉ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ስብስቦች እየተገናኙ ስለተጨባጭ እርም
ጃዎች እንዲወያዩ፣ ህብረታችን ከአቋቋመው ግብረ ሃይል ጋር በአድራሻችን በመገናኘት እንዲሰሩና ለዚህ ሂደት የመ
ጀመሪያ መጀመሪያ ሊሆን ወደሚችለው ሰፋ ያለ “የምክክር ስብሰባ” ለመሄድ በጋራ ርምጃዎችን እንዲወስዱ አገራዊ
ጥሪያችንን እናስተላልፍላቸዋለን።

**ነጥሎ ኮፒ ፔስት አርጎና ርእሱን ቀይሮ መላክ**

**በምርጫ ሳይሆን በህዝባዊ ትግል ድል ብቻ እውን የሚሆኑ
አማራጮች**

## መነሻ ነጥቦች - ስለሁኔታው ግልፅነትና ውስብስብነት

### አንደኛ የሁኔታው ግልፅነት

ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በኢህአዴግ አገዛዝ ስር እስካለን ድረስ በምርጫ ሂደት ምንም እንደማይገኝ ተብሎ ተብሎ ያለቀለት ጉዳይ ነው። ምርጫ 2002 ይህንን እውነታ ለኛም ለህዝባችንም ምንም በማያወላዳ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ግልፅ አድርጎታል። ከዚህ ሌላ ግልፅ የሆነ ነገር ቢኖር ኢህአዴግ ከምርጫ ምርጫ ‘‘አሸንፍኩ’’ ባለ ቁጥር አገራችንንና ህዝባችንን ወደ ጥፋት እያዳፉ የሚወስድዋቸውን ግፈኛና አውዳሚ የሆኑትን የኢኮኖሚና የሶሻል ፖሊሲዎች እቀጥልባቸዋለሁ ማለቱ ስለሆነ እነዚህ ፖሊሲዎች አዳዲስ ቀውሶችን እየፈጠሩ ከቀን ቀን የማንወጣው የጥፋት አዙሪት ውስጥ እየገባን እንደምንሄድ ሌላው ቢቀር ከግንቦት 97 በፊት ያልነበረው አዲስ የባእዳን የመሬት ማጋበስ ክስተት ያረጋግጥልናል።

በዚህ ሁኔታ ሌላ ያለው ግልፅ ነገር ተቃዋሚዎች ላለፉት በርካታ አመታት ይህንን ስርአት በጋራ ታግሎ ጥሎ አዲስ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ምእራፍ መክፈት ይኖርባቸዋል፣ ለዚህ ደግሞ ህዝባችንን ማእከል ያደረገ ሁለገብ የጋራ ትግል ማካሄድ አለባቸው የሚለውና ሁሉም አምንበታለሁ እያለ እስካሁን ግን በተጨባጭ ያልታየ የጋራ ትግል አጀንዳ ነው። በአጭሩ ከእንግዲህ ከኢህአዴግ ምንም አይጠበቅ በጋራ ትግል ይህንን ሃይል ማንበርከክና ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መሸጋገር ያስፈልጋል የሚል የደፈና ስምምነት አለ።

### ሁለተኛ ያለንበት ውስብስብ ሁኔታ

እዚህ ላይ አንድ ትልቅ ፓራዶክስ ይታያል። የህዝባችን የህልውና ቀውስ ተባብሶ ከዛሬ አምስት አመት ዛሬ ይበልጥ አፍጦና አግጦ የሚታይበት ደረጃ ላይ እያለን የዚያኑ ያህል ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ የጨለምተኝነቱ፣ የግራ መጋባቱና የትጥቅ መፍታቱ አባዜ ከዛሬ አምስት አመት ይልቅ ዛሬ እንዲሁ ይበልጥ አፍጦ አግጦ ያለ ሃቅ ነው። ለዚህ አስከፊ ክስተት ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚው ጎራም አስተዋፅኦ እያደረጉ የሚሄዱበት ሁኔታ ውስጥ ነን።

የኢህአዴግ አስተዋፅኦ። የኢህአዴግ አካሄድ የተቃውሞ የፍንጭ ፍንጭ የሚያሳዩትን ዜጎች በማፈንና ህብረተሰቡን በሽብር በመያዝ ብቻ አይወሰንም። ተቃውሞን ለመቀነስ በሚልዮን በሚቆጠሩ ዜጎች ( ገበሬዎችን ማዳበሪያ በመንፈግ፣ ከመሬት በመንቀል፣ ርሃብተኞችን በተለይ ከአመት አመት የሴፍቲ ኔት ተጠቃሚ የሆኑ ወደ ስድስት ሚልዮን የሚጠጉ መናጢ ድሃ ገበሬዎችንና፣ በየአመቱ የሚከሰቱ አዳዲስ ርሃብተኞችን እርዳታ በመንፈግ በህልውናቸው ሲመጣባቸው፣ የመንግስት ሰራተኞችን፣ ወጣት ተማሪዎችን ወዘተ እንደዚሁ በስራ መያዦ (ብላክ ሜል በማድረግ) ባይደግፋትም እንዳይቃወሙት ያደርጋል። ሌላም ጨርሶ ልብ ለማለት የማንፈልገው አዲስ ክስተትም አለ። ኢህአዴግ እርግጥ መሪዎቹ እንደሚሉትና ምርጫ 2002 “አሳይቷል” እንደሚባለው ከዳር እስከዳር በህብረተሰቡ የሚደገፍ ሃይል አይደለም። ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ደግሞ ከዳር እስከዳር በህብረተሰቡ የተተፋ ሃይል አይደለም። ከዚህ የዘለቀ ድጋፍ እያሰባሰበና እያደራጀ የሚሄድ ሃይል መሆኑን መዘንጋት ጨርሶ የሚያዋጣ አይደለም።

የኢህአዴግ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ከአመት አመት እየሰፉና እየከፉ የሚልዮኖችን ህልውና እየተፈታተነ ቢሆንም ከተጎጂው የህብረተሰብ ክፍል አንፃር ሲታዩ “እፍኝ የማይሞሉ” ሊባሉ የሚችሉ ነባርና አዳዲስ ደጋፊ/ተጠቃሚዎቹን ከእለት እለት እያደራጀና እያጠናከረ የሚሄድ ሃይል ሆኗል። በነባርና ይህ ነው የማይባል ሃብት እያጋበሱ ካሉት የጥቅም ተጋሪዎቹ በተጨማሪ አዳዲስ “ፍርፋሪ” በሚባል ደረጃ ህልውናቸውን ከዚህ ሃይል ጋር እያስተሳሰሩ የሚሄዱ ወጣቶች፣ ነጋዴዎች፣ ሰራተኞች ወዘተ እያፈራና ከሁሉም ከሁሉም በላይ እያደራጀ መሆኑ የሚካድ አይደለም። ይህ አዲስ እየተፈጠረ ያለው “የፍርፋሪ ተጠቃሚ ሰራዊት” እድሜ ለኢህአዴግ ከነጣ ድህነትና ማጣት ወጣሁ የሚል፣ ወይም ወደ ነጣ ድህነት ከመውረድ ተረፍኩ የሚል ሃይል እንደ ዋናዎቹ የስርአቱ ተጠቃሚዎች “ሎው ፕሮፋይ

ል" የያዘ ሃይል አይደለም። በይፋ ተንቀሳቅሶ ህብረተሰቡን የማንቀሳቀስ ተልእኮ ያለው "ቮካል" ወይም "ተናካሽ" የሆነ በተለይ ወጣቱን ያካተተ ሃይል ነው። ይህ የኢህአዴግ መሪዎች "ካለፈው ስህተታችን ተማርን" በሚል ለአምስት አመት ያህል የገነቡት ስትራቴጂ እየሰጠ ያለውን ፍሬ በምርጫ 2002 ዘመቻ ወቅትም ሆነ በማግስቱ ለመለስ ዜናዊ በመስቀል አደባባይ የተደረገው የድጋፍ ሰልፍ በግል አሳይተውናል።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ በቀጣዮቹ አመታት የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ከተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች አንፃር። ጥቅማቸውን ሊያረጋግጡላቸው ለማይችሉዋቸው ሚልዮኖች "ግራ ከተጋባ፣ ከተልፈሰፈሰና ከተከፋፈለ ተቃዋሚው ወገን ተሰልፈህ የትም አትደርስም" "ፋይዳ ለሌለውና የትም ለማያደርስ ተቃውሞ ብለህ ከነሱ ጎን በመሰለፍ ከሴፍቲ ኔት እንዳትገለል፣ ከመሬትህ እንዳትነቀል፣ ከስራህ እንዳትፈናቀል፣ ራስህንና ቤተሰብህን ለችግር እንዳትዳርግ።" በሚል ዛሬ ባለው ሁኔታና ተስፋ መቁረጥ ተቀባይነት እያገኝ የሚሄድ ቅስቀሳ ላይ እንዳሉና በቀጣዩም ወቅት በዚህ አካሄድ እንደሚቀጥሉ የታወቀ ነው። በዚህ መልክ ትጥቅ በሚያስፈቱት ህብረተሰብ ውስጥ ደግሞ ከአዲስ አበባ እስከ ዳር ድንበር መንደር በየቀበሌው፣ በየ መስሪያ ቤቱ፣ በየ ትምህርት ቤቱ ሌላው ቀርቶ እስከታች ወርደው በማደራጀት ላይ ባሉት የቤተሰብ ስብስቦች ውስጥ የፍርፋሪ ተጠቃሚዎችን ይበልጥ ቮካል ሆነው ይበልጥ ተደራጅተው በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋሉ። እዛው በዛው ደግሞ እነሱ በዚህ መልክ ጉልህ እንቅስቃሴ እያደረጉ የፖለቲካውን መድረክ ሲያጣብቡ ተቃዋሚዎች መንቀሳቀስ ቀርቶ "መላወስ" እንዳይችሉና በዚህም ይበልጥ ተአማኒነት እንዲያጡ በቀጥታ አፈና ብቻ ሳይሆን ወደ ህዝቡም እንዳይደርሱ የህዝባዊ ስብሰባ፣ የሰላማዊ ሰልፎች፣ የፕሬስ ነፃነትን ወዘተ በሮችን ሁሉ ጥርቅም አድርገው ይዘጋሉ። በሰርጎ ገቦቻቸውና በአንዳንድ ደካማ ተቃዋሚዎች በመጠቀም ይህንን ጎራ የመከፋፈሉንና የማናከሱን ጥረት ሳያሰልሱ ይቀጥሉበታል። በዚህ ሁሉ የህብረሰቡን የትጥቅ መፍታትንና የጨለምተኝነት ሂደት አግዘው ይበልጥ "እየተደላደሉ" ለመሄድ ይሞክራሉ። ይህንን አካሄድ የማክሸፉ ተልእኮ በዴሞክራትና አገር ወዳድ ግንባር ቀደም ሃይሎች ትከሻ ላይ የወደቀ መሆኑን ማውሳት እንኳዋን አስፈላጊ አይመስለንም። ግን ሁለት ጥያቄዎች አሉ። አንደኛ የተቃዋሚው ጎራ ይህንን የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድና ስትራቴጂ እያገዘ ነው ወይስ የምር እየተዋጋው? ሁለተኛ ዛሬ ከአለንበትና ስር ነቀል በሆነ የአይታ ለውጥ ታግዞ በእርግጥ ተግባራዊ ለመሆን ምን መደረግ አለበት? ሰፊ ውይይት የሚያስፈልገው አጀንዳ ይህ ይመስለናል።

### የተቃዋሚው ጎራ ይህንን ክስተት እያገዘ ነው ወይስ የምር እየተዋጋው?

የኢህአዴግ መሪዎች አንድ ዋና ቅስቀሳና የትግል ቅስም ሰባሪ ፕሮፓጋንዳ ተቃዋሚው ጎራ ምንም መፍትሄ ለማምጣት የሚችል አማራጭ ሃይል አይደለም የሚል ቅስቀሳ ነው። ለዚህ ለአለንበት የድክመት ደረጃ ከማርያም መቀነት የረዘሙ ምክንያቶች ልንደረድር እንችላለን። ያለው ሃቅ ግን የኢህአዴጎችን ፕሮፓጋንዳ የሚያጎለብት እንጂ የሚንድ አይደለም። ዛሬ በህብረተሰቡ ውስጥ ይህ ስሜት የተስፋፋ በመሆኑ በዚህ አጥፊ ሃይል ፖሊሲ ህልውናቸው ጥያቄ ውስጥ እየገባ የሚሄዱ ሚልዮኖች አስተማማኝ የሆነ ታግሎ በግልፅ አጀንዳ የሚያታግል ሃይል ጨርሶ የማያዩበት ደረጃ ላይ ናቸው። በአለው ሁኔታ እነዚህን ከህዝባችን ከዘጠና በመቶ በላይ የሆኑ ወገኖቻችንን በጋራ በአንድ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ አልቻልንም። የተከፋፈለ ተቃዋሚ ሃይል ነው ይሉናል። እውነትም የተከፋፈለና አንዳንዴም እርስ በእርሱ የሚናከስ ሃይል ነው። ግራ የተጋባና ተአማኒነት ያለው አማራጭ የማያቀርብ ይሉናል። በአምስት አመት በምርጫ ሰሞን በአማራጮች ዙሪያ ሰፊ ቅስቀሳ ይካሄድና ምርጫው ተጭበርብሮ ሲጠናቀቅ "የህዝብ ድምፅ ይከበር" "የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች ይሙዋሉ" እየተባለ አንድ ሰሞን ትግል ይካሄዳል። በመሃል በምርጫው ዘመቻ ሰሞን ቀርበው የነበሩት ህዝባዊ አማራጮች ወደ ጎን ይተውና አማራጭ ፕሮግራሞች "የክት ቀን ሰነዶች" ሆነው እንደገና እንዲነሱ ቀጣዩ ፋይዳ ቢስ ምርጫ ይጠበቃል። ለምሳሌ ለሃገራችን ገበሬዎች ከአንገብጋቢነትም አልፎ የህልውና ጥያቄ የሆነው የመሬት ይዞታ ዋስትና ጉዳይ በምርጫ 97 ከፍተኛ ቅስቀሳ ተካሂዶበት የገበሬውን ድጋፍ ያገኘ አማራጭ ነበር። ከምርጫው ጭብርብር በኋላ በተካሄዱት አምስት አመታት በዚህ ጥያቄ ላይ አንድም ህዝባዊ ስብሰባ ሳይጠራ፣ አንድም ሰልፍ ሳይደረግ፣ አንድም የረባ መግለጫ ሳይወጣና አንድም ጊዜ "የህዝብ ድምፅ መሰረቅ" ማለት የዚህ ህዝባዊ አማ

ራጭም መዘረፍ ነው በሚል፣ በኢህአዴግ ስር ነፃ ምርጫ አይቻልም ካልን በዚህ ስርአት ስር የገበሬው የመሬት ይዞታ ዋስትና ህልም እንደሆነ በሚል የተካሄደ ቅስቀሳ አልነበረም። ጥያቄው አምስት አመት ቆይቶ በምርጫ 2002 ሳቢያ እን ደገና ተነሳ። ምርጫው በተካሄበት ሁኔታ ተካሄደ። ኢህአዴግ ጠቅልሎ አሸነፈ። የተቃዋሚው ትግል እንደ 97ቱ ማግስ ት አሁንም "የህዝብ ድምፅ ይከበር" በሚለው መፈክር ተቃኝቶ ሲንቀሳቀስ ይታያል። ለዚያውም እንግዲህ እንደ ምር ጫ 97 ህዝባችን በዚህ ግንጥል መፈክር ዙሪያ እንኳን እንዲንቀሳቀስ ጥሪ እየተደረገለት አይደለም። "ግንባር ቀደም" የሆኑ ሃይሎች ነድፈናል ከሚሉት ስትራቴጂ አንፃር "የታጋይ ተመልካች" እንዲሆን እንጂ ለሰላማዊ ሰልፍ ቀርቶ ለአዳ ራሽ ስብሰባ እንኳዋን እየተቀሰቀሰ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ብዙ የሚጠበቅበት መድረክ በአለፈው ሳምንት ባወጣው አ ስገራሚ መግለጫ መጨረሻ ላይ ያደረገው ጥሪ "ህዝቡ በሰላማዊ አግባብ የህዝብን ድምፅ ለማስከበር <u>የምናደርጋቸውን ትግሎች ተረጋግቶ እንዲከታተል ጥሪያችንን እናስተላልፋለን" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። በግንጥል መፈክር ዙሪያ ህዝባ ዊ ሳይሆን ግንጥል የግንባር ቀደሞች ፍልሚያ።</u>

የሚካሄደው ትግል በዚህ መልክ በአንድ በኩል በኢህአዴግ መሪዎችና በሌላ በኩል በተቃዋሚ ድርጅቶች (ማ ለትም በሁለት አናሳ ሃይሎች) እስከታጠረ ድረስ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች በድል አድራጊነት የሚወጡበት ምንም አይነት ተአምር አይኖርም። በዚህ ፍልሚያ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በአለው የገንዘብ አቅም ታግዞ በመቶ ሽ ህ በሚቆጠሩ ተናካሽ ካድሬዎች ሃገሪቱን አሳብሱዋል። እንደ መንግስት ደግሞ ሰራዊት፣ ፖሊስ፣ የመረጃ መረብ፣ ሬድ ዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ፕሬስ ተቋማት ብቸኛ ተጠቃሚ ከመሆን አልፎ የሃገሪቱን ካዝና ብቻ ሳይሆን የመሬቷም ብቸኛ አዛዥ ሆኖ በሚልዮኖች ህልውና የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን አለው። ተቃዋሚው ጎራ ይህንን ሁሉ ለማካካስ የሚችለው የ ኢህአዴግ መሪዎች በአጥፊ ፖሊሲዎቻቸው አማካኝነት በምንም አይነት ሊደርሱበት የማይችሉትን ሰፊውን ህዝብ ከጎ ኑ በማሰለፍ ብቻ ነው። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል እይታ፣ አጀንዳና ድፍረት እስከሌለ ድረስ በሁለቱ ወገኖች የሚ ደረገው ትግል የሽክላና የብረት ድስት ፍልሚያ ስለሚሆን ውጤቱን ከወዲሁ መተንበይ አያስቸግርም።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ካሉበት አጣብቂኝ ወጥተው ለነፃነቱ ትግል የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ከፈለግን መጀመሪያ በህብረታችን ደረጃ ጥራት ያለው የጋራ አቋም መያዝና ይህንን ደግሞ ሌሎች ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች እንዲጋሩ ትግል ማካሄድ ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ በአን ዳንድ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት አካሂደን ጥራት ያለው ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልገናል። እነዚህ ዋና ዋና ውይይት የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች እንደሚከተለው ሊዘረዘሩ ይችላሉ።

## አንደኛ የትግላችንን ዘላቂ አላማ ከወዲሁ በግልፅ የማስቀመጡ ጥያቄ

በምርጫ 97 ወቅት ያቀረብነው አማራጭ ሰነድ በኢኮኖፖ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢ ወዘተ ጉዳዮች ላይ ብዙ ቁም ነገሮችን የያዙ ነጥቦች ቢካተቱበትምና የትግላችን ዋና አላማ መድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲን የሚያፀድቅ ህገ መንግስታዊ ስርአት የመገንባት ራእዩ በግልፅ የተጠቆሙ ቢሆኑም ወደዚህ ሁኔታ የሚያደርሰንም ሂደት በሰነዱ ክፍል ሁለት በትክ ክል ተቀምጦ ነበር። በዚህ "ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ስርአት ሽግግር" ሂደት እንደ ወሳኝ ምእራፍ የተቆጠረው በ ሃገራችን ኢህአዴግን በህዝባዊ ትግል ከጥፋት ሂደቱ እንዲታገድ አድርጎ አንድ "የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አገር አቀፍ ጉባኤ" ሃሳብ ቀርቦ ነበር። ዛሬም ቢሆን ተቃዋሚ ሃይሎች ለዴሞክራሲ፣ ለፍትህ፣ ለህግ የበላይነት ወዘተ በሚያደርጉት ትግል በግልፅ አጀንዳ እንዲመራ ከተፈለገ የዚህ ትግል መቋጠሪያ ይህ በሃገራችን ምድር የሚሰየም የዴሞክራሲያዊ ሽ ግግር ጉባኤ እንደሆነ ከወዲሁ አስረግጦ ለማስቀመጥ ይህንን የአማራጭ ፕሮግራማችንን ክፍል (የሚታረመውን አርሞና የሚጎድለውን ጨምሮ) እንደገና ማቅረብ ይርብናል። ይህ ምንም ችግር የሌለው ተግባር ነው። ዋናው ችግር ከአለንበት የድክመት አዙሪት ወጥተን እዚህ ወሳኝ የትግልና የድል ምእራፍ የምንደርሰው እንዴት ነው የሚለውን ውስብስብና አ ስቸጋሪ ጥያቄ በቅጡ አንስቶ የመመለስና ተግባራዊ የማድረግ ችግር ነው።

## ሁለተኛ ሁሉም የሚስማማበት "የህዝባዊ ትግል-" ችግሮች

ህዝባዊ ትግል ስንል እንደ ግንቦት 97 ማግስት ህዝቡ ሆ ብሎ ወጥቶ በያለበት የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች፣ የስራ ማቆም አድማዎች ወዘተ የምንል ከሆነ ዛሬ በአለው ሁኔታ ይህ በአጭር ጊዜ የሚታሰብ እንኳን አይመስልም። የተመሪም የመሪም ችግር አለበት። ህዝባችን ዛሬ በአለበት ሁኔታና ተቃዋሚ ሃይሎች በአሉበት "የኢታማኒነት" ደረጃ ሰልፍ ውጣ ቢባል ጥቂት ቁርጠኛ ወገኖች ይወጡ ይሆናል እንጂ አይን በሚስብ ብዛት የሚንቀሳቀስ የህብረተሰብ ክፍል አይኖርም። በዚያ ላይ ከፍ ብለን እንዳየነው በተቃዋሚዎችም አመራር አካባቢ ለህዝቡ የሚደረገው ጥሪ "ተንስ ተንቀሳቀስ ታገል" የሚል ሳይሆን እኛ የምናደርገውን ትግል "ተረጋግተህ ተከታተል" የሚል ጥሪ ነው። በዚህ ሁኔታ እንዲህ አይነቱ ጥሪ ቢደረግ እንኳን አዳማጭ አጥቶ በኢህአዴግ ካድሬዎች ፊት ለመሳቂያነት የሚዳርግና የትጥቅ መፍትቱን ሂደት የሚያግዝ አካሄድ ከመሆን አያልፍም። እንዲህ አይነቱ ትግል እውንና ፍሬያማ እንዲሆን ህብረተሰቡ ጥራፖርችንን እንዲሰማ መጀመሪያ የተቃዋሚውን ጎራ ተአማኒነት መገንባት ሁለተኛ ደግሞ የህዝባዊውን ትግል ቅስም ለመስበር የኢህአዴግ መሪዎች በአመፅ እንደሚሰማሩ ከወዲሁ አውቆ ቀጣይነት ያለው አመራር እውን የሚሆንበት ሁኔታ ደረጃ በደረጃ ማመቻቸት ያስፈልጋል። እዚህ ላይ እንግዲህ መመለስ ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ። አንደኛ ህዝባችን እዚህ ደረጃ እንዲደርስ በምን አጀንዳ ዙሪያ እንቀስቅሰው? ሁለተኛ በነዚህ አጀንዳዎች ዙሪያ ቀስ በቀስ ሰፊ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለመገንባት አሁን ካለው የግራ መጋባትና የትጥቅ መፍታት ሁኔታ አንፃር ምን አይነት ትግል ማካሄድ ይቻላል?

**አንደኛ የትግል አጀንዳ ጥያቄ።** አሁን በአለው ሁኔታ የትግል አጀንዳን በተመለከተ እየተንፀባረቀ ያለው ችግር ለመብት (ማለትም በፖለቲካ ጥያቄዎች ዙሪያ) የሚደረገው ወይም ይደረግ የሚባለው ትግል ለህልውና (ማለትም በኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች ዙሪያ) ከሚደረገው ትግል ገንጥሎ የማየት ችግር ነው። እንደ ግንቦት 7 አይነቶቹ ድርጅቶች ዋና አጀንዳችን የሚሉት በዴሞክራሲያዊ "ራእይ" ዙሪያ የሚካሄደው ትግል ሆኖ አፍጠው አግጠው ህዝባችንን ጉረሮ አንቀው የያዙትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች "ነገ ዴሞክራሲን ስናሰፍን" እንያያዛቸዋለን የሚል ግልፅ አካሄድ ነው።

"የሰመረ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለማቆም እጅግ ወሳኙ ጉዳይ የተጨባጩን አለም ውሱን ድንበሮች ጥሶ፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ያገጠጠ ሃቅ ርቆና ንቆ፣ በምናባዊ ሃይል ወደሳሉት ዴሞክራሲያዊ እፁብነት (ፔርፌክሽን) ለመድረስ፣ ለመንፏቀቅ፣ ለማቃተት፣ ለመዳህ ብሎም ለመሮጥ በቁርጠኝነት መወሰን ነው።"(ስርዝ የተጨመረ) (ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ "የግንቦት ድምፅ" ቁጥር 61 ሃምሌ 9 2001 አ.ም.)

በዚህ "ዛሬ ለራእይህ ነገ ለህልውናህ" በሚል እንግዳ የሆነ መፈክር ብዙ መተቸት ይቻላል። ለጊዜው ግን ሁለት ቁም ነገሮችን አስቀምጠን እንለፈው። አንደኛ ህዝባዊ ሰላማዊ ትግል ብለን "ሁሉም ብሶቱን አንግቦ ይንቀሳቀስ፣ ሁሉም ብሶትህ ብሶቴ ብሎ ይተጋገዝ፣ ሁሉም ይህ ሁሉ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሲመሰረት መሆኑን አውቆ ለስርአት ለውጥ በአንድ አቅጣጫ ይግፋ" ከሚለው አቋማችን ጋር እንደ ሰማይና ምድር ይራራቃል። ሁለተኛ ዛሬ ህዝባችን በሚገኝበት የህልውና ቀውስ እንዲህ አይነቱ "ከሰማይ የራቀ" መፈክር ህዝባችንን መልሶ ወደ ትግሉ ያመጣል ማለት ጨርሶ የማይታሰብ ነው።

እንኳን ይኸ ቀርቶ ከዚህ ትንሽ ወረድ ብለን አሁን በሃገር ውስጥ ያሉ መሪዎች እንደሚሞክሩት "የህዝብ ድምፅ ይከበር" በሚል የፖለቲካ አጀንዳ የሚደረገው ትግልም ቢሆን ብቻውን የትም የሚያደርስ አይደለም። ይህ በግንቦት 97 ማግስት እንዳየነው ለተወሰነ ጊዜ ህዝብ አንቀሳቃሽ መፈክር ሊሆን ይችላል። ለዚያውም ከፍ ብለን እንዳየነው ዛሬ በአለው ሁኔታ አይሰራም እንጂ ከጊዜ ጋር እየፈዘዘ የሚሄድ አጀንዳ ነው። በዚያው ልክ ደግሞ ከጊዜ ጋር እየጎሉ እየከፉ የሚሄዱት የህዝባችን የህልውና ችግሮች እንደሆኑ የግንቦት 97 ሁኔታ በግልፅ አሳይቶናል።

በመሆኑም ካለፈው በመማርም ሆነ ዛሬ ካለንበት ሁኔታ በመነሳት ህዝባችን መልሶ ከትግሉ እንዲደባለቅ ለማድረግ የሚቻለው ከጊዜ ጋር እየጎሉ በሚሄዱት ተጨባጭ ቀውሶችና በምናቀርባቸው ህዝባዊ አማራጮች ዙሪያ መቃኘት እንደሚኖርበት ግልፅ ይመስለናል። ግን ደግሞ በትግሉ አጀንዳ ዙሪያ ስምምነት መድረሱ ብቻውን በቂ አይሆንም።

ከዚህ አልፈን በህዝባዊ መፈክሮቻችንና አጀንዳችን ዙሪያ ዛሬ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ቀስ በቀስና ደረጃ በደ
ረጃ ሰፊ፣ የተባበረና በአንድ አቅጣጫ የሚገፋ ህዝባዊ ትግል እውን ስለሚሆንበትም ሁኔታ መወያየት ያስፈልጋል።

**ሁለተኛ ደረጃ በደረጃ ህዝባዊ ትግል ስለሚገነባበት ሁኔታ።** የአነገብነው የትግል መፈክር ምን ያህል ትክክልና
ህዝባዊ ቢሆን ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአንድ ጊዜ የምንፈልገውን ሰፊ ህዝባዊ ትግል እ-ውን የምናደርግበት ሁኔታ
አይኖርም። የሰላማዊ ሰልፍ፣ የስራ ማቆም አድማ ወዘተ ችግሮችን ከፍ ብለን ጠቁመናል። ዛሬ የህዝቡ ትግል ባለበት
ደረጃ እንዲህ አይነቱ የትግል ስልት ከኢህአግ ህጋዊ ፈቃድ አግኝቶ ሊካሄድ የሚችልም አይደለም። በመሆኑም በአን
ዴ ሚልዮን ህዝብ ሰልፍ ለማስወጣት ከመጣር በፊት ለጊዜው የሚያዋጣው አካሄድ ልክ እንደ ምርጫ ዘመቻው ወቅት
በተጨባጭ አማራጮች ዙሪያና እነዚህን ከዴሞክራሲ ጥያቄ ጋር እያያያዙ ትናንሽ ስብሰባዎች መጥራትና ከተለያዩ የ
ህብረተሰብ ክፍሎች - ከገበሬው፣ ከወጣቱ፣ ከስራ አጡ፣ ከነጋዴው፣ ከሰራተኛው ወዘተ ጋር ችግሮቹና መፍትሄዎቻቸ
ው ላይ ያተኮሩ ውይይቶች ማካሄድ የሚጠቅም ይመስለናል። በዚህ ሂደት ቀስ በቀስ በእነዚህ የተላያዩ የህብረተሰብ ክ
ፍሎች (በተለይ በወጣቱ) ውስጥ ግንባር ቀደም የሆኑትን በማደራጀት አንድ ደረጃ ሲደረስ እነዚህ ሃይሎች በጋራ ሊንቀ
ሳቀሱና በተለያዩ የሰላማዊ ትግል ስልቶች የኢህአዴግን አገዛዝ ሊጋፈጡ የሚችሉበት ሁኔታ የማይፈጠርበት ምክንያት
አይኖርም።

በዚህ አካሄድ ስምምነት ካለ ተቃዋሚዎች ከደፈና ቅስቀሳ ዘልቆ የሚሄድና አሳማኝ የሚሆን ውይይት ለማካሄ
ድ "ሲርየስ" የሆነ የአደረጃጀት መስተካከል ያስፈልጋቸዋል። አሁን በግልፅ እንደሚታየው የኢህአዴግ መሪዎችና ካድ
ሬዎች የሚያራምዱዋቸውን የጥፋት ፖሊሲዎች "ቀስ በቀስ ሃገሪቱን ወደ ምድራዊ ገነት እየቀየሩዋት" ነው በሚል የሆ
ነ ያልሆነ ስታቲስቲክ ሳይቀር መደርደር ይቃጣቸዋል። በየመስኩ የሚተገበሩትን አጥፊ ፖሊሲዎች ሽንጣቸውን ገትረ
ው ለመደገፍና ህዝብ ለማደናገር ሚኒስቴር ብቻ ሳይሆን የሰለጠኑና የሚሉትን የሚያውቁ "ተከራካሪዎች" አፍርተዋል።
በተቃዋሚው ጎራ ግን ያለው አካሄድ ከልማዳዊው አሰራር ያልተላቀቀ የፖለቲካ መሪ ከተባለ "ሁሉም በሁሉም መስክ
አዋቂ" ሆኖ የሚቀርብበት አካሄድ ነው። ይህ አካሄድ የኢህአዴግ መንግስት በየመስኩ የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች በ
ተጨባጭ ለመቃወምና አማራጮችን አሳማን በሆነ ዘዴ ለማስተላለፍ እንቅፋት መሆኑ እስካሁን ታይቱዋል። ከዚህ በመ
ነሳት የተቃዋሚ ድ-ርጅቶች አደረጃጀታቸውን ልክ እንደመንግ-ስት አድርገው ለየመስኩ የእርሻ መስክ ይሁን፣ የመከላ
ከያ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ይሁን የህክምና፣ የትምህርት ይሁን የአካባቢ ጥበቃ፣ የወጣቶች ይሁን የሴቶች ጉዳይ፣ የመ
ከላከያ ይሁን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ወዘተ "ሻዶ ካቢኔት" እንኳን ባይባል ለየመስኩ ዋና ተጠሪዎች በመሰየም መልክ
ቢሰማሩና እነዚህ "ዋና ተጠሪዎች" ደግሞ በየበኩላቸው ሊሚያግዙዋቸው በሚችሉ ባለሙያዎች ቢከበቡ ትልቅ እርም
ጃ ይሆናል።

## በመጨረሻም ስለ ዲያስፖራው ሚና

ሰፊ ውይይት ተካሂዶ ትግሉ አሁን ካለበት አስከፊ አጣብቂኝ ስሚወጣበት ዘዴ ስምምነት ከደረስን በኋላ በተለ
ይ በሃገር ቤት ስትራቴጂው ተጨባጭ ስለሚሆንበትም ሁኔታ መወያየት ያስፈልጋል። ሽህ ጊዜ ጥራት ያለው አካሄድ
ቢኖረንም በሜዳው ላይ ተግባራዊ የሚሆንበት ዘዴ ካልተቀየሰ እምብዛም ዋጋ አይኖረውም።

1. በምርጫ 97 ህብረቱም ሆነ ቅንጅቱ የሃገራችንን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ፣
የማህበራዊ ወዘተ አማራጮች በተለይ በህብረቱ በኩል ደግሞ ወደ ተረጋጋ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ስለሚ
ደረገው ጉዞ ዴሞክራታይዜሽንንና ብሄራዊ እርቅን በተመለከተ ሮድ ማፕ ለህዝባችን አቅርበው እነዚህን ደግሞ ህዝባች
ን በማያወላዳ መልክ ድምፁን ሰጥቶባቸው መልሰው ተነጥቀዋል። ቢሆንም ቀጣዩ የተቃዋሚ ሃይሎች እነዚህን በጎ አማ
ራጮች ወደ ጎን በመተው ትግሉን በግንቦቱ ቅልበሳ "የድምፅ ዝርፊያ" ገፅታ እንዲያተኩር አድርገው በመቀጠላቸው

ህዝባችን ከእለት እለት የሚባባሱ የህልውና ቀውሶች ውስጥ እየገባ የጨለምተኝነትና የትጥቅ መፍታት አዙሪት ውስጥ እንዲዘፈቅ በመደረጉ አሁን የምንገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተናል።

2. ለህዝባችን ቀርበው ከነበሩት ዋና ዋና በጎ አማራጮች ምን ነበሩ? መሬት ይዞታ፣ ርሃብ፣ የስራ አጥነት በተለይም የወጣቱ፣ ጤናማ የሃገር ልማት አካሄድ (ሽማችና አምራች) የግል ሴክተሩ እንቅስቃሴ፣ አካባቢ.......እነዚህ ሁሉ ተዘረፉ ስንል ምን ማለት ነው? የህዝባችን ችግሮች እየተባባሱ ሄዱ ማለት ነው። ዛሬ ደግሞ አምስት አመት ጠብቀን እንደ ገና እያነሳናቸው ነው። ግን ሁሉም የሚቀበለው አንድ ነገር አለ። በወያኔ ስር በምንም አይነት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አንጠብቅም አጭበርብሮ እንደገና አሸነፍኩ ይላል። ያለው ምፀት? ወያኔ በምርጫ አይወርድም እያልን እዛው በዛው ደግሞ ህዝባችንን ተነስ፣ ታገል፣ ተሰዋ ምረጠንና እነዚህን አማራጮች በተግባር እናውላለን። ቢበዛ ደግሞ ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ታገል እንላለን። ቀጥለንም በግንቦት 97 አልተቻለም ነበር፣ አሁንም አልተቻለም ስለዚህ ቀጣዩ የ2007 ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን....ወቅቱ ሲደርስ እንንቀሳቀሳለን። በአጭሩ ግን ወያኔ እያለ ነፃ ምርጫ አይካሄድም ማለት ወያኔ እያለ መሬትም ለአራሹ አይሆንም፣ የወጣቱ ስራ አጥነት አይቀነስም ወዘተ እነዚህን አማራጮች በወያኔ ስር በሚደረግ ምርጫ መቼም ቢሆን እውን አናደርጋቸውም።

አቀራረቡ? በመሬት ጥያቄና የርሃብን አዙሪት የመስበር ጥያቄ። የወያኔ..ከዚያ እኛ ያቀረብነው አማራጭ። በምርጫ 97 ወያኔ ተመረጥኩ ሲል ገበሬው የለም ጢሰኝነት ይሻለኛል...አሁንም ይህንን አማራጭ እናቀርባለን። ርሃብ ግን ቀጥሎዋል። ዛሬ ያለው ሁኔታ። የዛሬ 18 አመት ወያኔ ያለው። ከዚያ የሆነው። የመባባሱ ሁኔታ። ሁለት ቅራኔዎች። አንደኛ ህዝባችን በየእለቱ ይራባል። የሚያስርበው ፖሊሲ ይቀየር እያልን የምንታገለው በየ አምስት አመቱ ነው። ይህ ብቻ አይደለም። ሁለተኛ የዚህ ትግል ማእከልና ባለቤት ራሱ ርሃብተኛው ሳይሆን ቢከፋም ቢለማም በቀን ሶስቴ በልቶ የሚያድረው ግንባር ቀደም ሃይል ሆኖ እናገኘዋለን። አሁንም ጢሰኝነት ይሻለኛል ብለሃል ይባላል። የለም አይደለም ምርጫው ተጭበርብሩዋል እንላለን። 2007ትን ጠብቅ ብለን ፋይሉን እንዘጋለን። ያኔም እነዚህ አማራጮች በምርጫ እንደማይገኙ እያወቅን።

*ነጋዴው ...የወያኔ አጥፊ ፖሊሲ....የእኛ አማራጭ። በ97 የለም ይህ ይሻለኛል። አሁንም ወያኔ ያሸነፋል ስንል ነጋዴው "ተስማምቶኛል" ብሉዋል። ይህ እንዳልሆነ እናውቃለን። በምርጫ 2007ም እንደዚሁ ይሆናል። በምርጫ 2012ም።*

3. ያለንበት አዙሪት? ከዚህ ሃቅ ስንነሳ ያለንበት አጣብቂኝ በቅራኔ የተሞላ ሁኔታ ግልፅ ነው። ከወያኔ በምንም አይነት ነፃ ምርጫ አንጠብቅም እያልን እዛው በዛው ወያኔ ለቀጣይ ህልውናው እንደ ህይወት እስትንፋስ ያስፈልጉኛል ብሎ የሙጥኝ ያላቸውን አጥፊ ፖሊሲዎች በምርጫ እንለውጣቸዋለን እያልን እንግደረደራለን። (እነዚህን አማራጮች በምርጫ ሰሞን ስብሰባ እናደርግባቸዋለን፣ አልፈን ተርፈን ከወያኔ ጋር በቴሌም በሬድዮም በህዝብ ፊት እንከራከርባቸዋለን። ከዚያ "ምርጫ" ይካሄዳል። ወያኔ በዝረራ ኣሸነፍኩ ይላል። ማለትም ገበሬው "የመሬት ይዞታ ዋስትና ግድ የለኝም፣ አሁን ያለው የመንደር ካድሬ ጢሰኝነቱ ተስማምቶኛል ብሉዋል፣ ወጣቱ... ነጋዴው ወዘተ... ወዘተ በመሃልስ? እስከ ዛሬ አምስት አመት ድረስ መሬት ለአራሹ ወዘተ እያልን ስብሰባ፣ ሰልፍ የማይታሰብ ነው.......)
1ኛ ጥያቄ - ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ስንል በአጭሩ ምን ማለት ነው - አንደኛ ሁሉም እንደብሶቱ ወዘተ ሁለተኛ አንቀሳቃሽ ሃይል ላይ ማተኮር ሶስተኛ ለዚህ ትግል ህዝባዊ አመራር ለመስጠት መሰባሰብ - ይህ ሁሉ አሁን በምርጫ 2002 ካለው ሁኔታ አንፃር

2ኛ ጥያቄ - አሁን ያለው ሁኔታ

**ሐ/ተአማኒ ህዝባዊ አመራር**

ዛሬ የተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህዝብ ፊት ተወዳድረው ስልጣን ለመጨበጥ የሚያካሂዱት የምርጫ ዘመቻ ወይም ደግሞ የኢህአዴግን መንግስት አስወግዶ በሌላ ’ ’ህብረተሰቡን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ”አሸጋግራለሁ” ለሚል ሌላ መንግስት የመተካት ትግል አይደለም። በዚህ ጉዳይ ከስድስት አመታት በፊት መኢሶን ”ተሸጋጋሪው ማነው? አሸጋጋሪውስ?” በሚል ርእስ ባሰራጨው ጥናታዊ ሰነድ ይህ የጊዜው አንገብጋቢ የሆነ የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉዳይ ከፖለቲካ ድርጅቶችም፤ ከምርጫ ሰሞን ግርግርም፤ ከመንግስት ስልጣን ቅብብሎሽ ሂደትም አልፎ የሚሄድ ሰፊ አገራዊ አጀንዳ እንደሆነ ሲጠቁም

”ዛሬ ከለንደኑም ጉባኤ ጉድለቶችም ሆነ ከሃገራችን ’የሽግግሮች’ ታሪክ መቅሰም ያለብን ትም-ህርት ሽግግር በአመፅ፤ ጊዜያዊ የበላይነትን ያገኘው ወገን የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ህብረተሰቡን እስከ ወዲያኛው ’አሸንፍኩ’ በሚልበት ፍጥጫ፤ በአሸናፊና ተሸናፊ መሃከል ወይም ደግሞ በባእዳን አቀነባባሪነትና አስተናጋጅነት ’አሉ’ በሚባሉ ጥቂት የፖለቲካ ሃይሎች መሃከል በዝግ ችሎት የሚደረግ የስልጣን ቅብብሎሽ ላይ ማተኮር የለበትም የሚል ትምህርት ነው። ከዚህ ይልቅ ሽግግሩ እስከ ተቻለ ድረስ በስምምነት፤ በ’ኮምፕሮማይዝ’ እንዲከናወን፤ ህብረተሰባችንም በዚህ የሽግግር ወቅት በእያንዳንዱ ቀን ይበልጥ ዴሞክራቲክና ይበልጥ የተረጋጋ መልክ እየያዘ፤ ህዝባች-ን በእያንዳንዱ ቀን ይበልጥ ንቁ ተሳትፎ እያደረገና ይበልጥ እየተደራጀ፤ ለመጭ-ው የተሻለ ስርአት ይበልጥ ራሱን እያመቻቸ የሚሄድበት የታሪክ ወቅት እንዲሆን መታገል ያስፈልጋል ማለት ነው።” ካለ በኋላ ድርጅታችን በዚሁ ሰነድ ላይ ሃገራችን የሚያስፈልጋት ”የህብረተሰብ ሽግግር” እንደሆነ በግልፅ አስረግጦ እንደዝህ አይነቱ ሽግግር የማን ሃላፊነትና በማን ላይ የተጣለ አደራ እንደሚሆን በጠቆመበት ክፍል፤

”ተሸጋጋሪው ህብረተሰባችን እንደአለ እንደ መሆኑ መጠን አሸጋጋሪውም ራሱ ህብረተሰቡ መሆን ይገባዋል እንላለን። ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ.....የዚህ የሽግግር ሃላፊነት ለማንም ይሁን ለማን ’ሃገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አሸጋግራለሁ’ ብሎ ቃል ለሚገባ ጊዜያዊ ይባል የሽግግር፤ ጥምር ይሁን አንድ ’ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ግንባር’ ለሚመራው መንግስት የሚተው ጉዳይ መሆን የለበትም። ይህ ሃላፊነት እንደ ደቡብ አፍሪካው የሽግግር ሂደት ከማንኛውም መንግስት ውጭ ሆኖ ለሚሰራ፤ በአጠቃላይ የሃገሪቱን የዴሞክራታይዜሽን ሂደት ከማንም የፖለቲካ ሆነ ሌላ ሃይል ወገናዊ ቁጥጥር ውጭ በበላይነት ለሚያቅድና ለሚያስፈፅም አካል መተው ይኖርበታል።” በማለት ሰፊና አገራዊ የሆነ ራእዩን አስቀምጧል።

በዚህ የሽግግር ወቅት ሃገሪቱን የሚያስተዳድር መንግስታዊ መዋቅርም አስፈላጊነቱ የማያጠራጥር በመሆኑ ስለሚቋቋመው አስተዳደር (ኬር ቴከር ገቨርንሜንት) ያለውን አማራጭ ሲያቀርብ የኢህአዴግ መሪዎች በጥፋት ሂደታቸው ቀጥለው በህዝብ ትግል ከተወገዱ በኋላ

”በሽግግሩ ሂደት እጁን የማያስገባና ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥያቄዎች ምንም አይነት ዘላቂነት ያላቸው ውሳኔዎች የማድረግ ስልጣን የሌለው ጊዜያዊ አስተዳደር መሰየም” አስፈላጊ እንደሚሆን ጠቁሟል።

ኢዴሃህም ለግንቦት 97 ምርጫ ባወጣው አማራጭ ሰነድ ሃገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ህብረተሰብ የማሸጋገሩን ጉዳይ በሚገባ በማጤን በፕሮግራሙ ሁለተኛ ክፍል ለዚህ ሽግግር አስፈላጊ ያላቸውን ሁለት አካላት ማለትም የዴሞክራሲያዊ ሂደት የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽኖች ስለሚሰየሙበት ሁኔታና ስለሚጠብቃቸው ተግባር በሰፊው አስቀምጧል። ከዚህም በመነሳት የሚባል አንድ ቁምነገር ቢኖር የዛሬው የኛ የዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ሃይሎች ስትራቴጂያዊ አላማ የኢህአዴግ መንግስት በህዝብ ትግል እንዲያፈገፍግ ወይም ደግሞ እንዲወገድ ተደርጎ ለተያዘው ህዝባዊ ተጋድሎ ወሳኝ ወደሚሆነው ”የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ” እውን እንዲሆንና በዚህ ጉባኤ በሚሰየሙት ሁለቱ ኮሚሽኖች አማካኝነት ዴሞክራሲ ጎልብቶ፣ ብሄራዊ እርቅ ወርዶ አጠቃላዩን ሂደት በዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ብሎም በነፃ ምርጫ ለመቋጠር መታገል ይሆናል ማለት ነው።

እንደዚህ አይነቱ የሽግግር ጉባኤ ተሳታፊዎቹ እነማን እንደሆኑና ተግባራቱስ ምን እንደሚሆኑ በኢዴሃህ መግለጫዎች በተደጋጋሚ የተጠቀሙ ስለሆኑ እንባቢ ከህብረቱ አማራጭ ሰነድ ክፍል ሁለትን እንዲመለከት እንጋብዛለን። እዚህ ላይ ትኩረት የምንሰጠው ጉዳይ እዚህ ወሳኝና ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለመድረስ ስለሚደረገው የግድ ዘርፈ ብዙ የሆነ ህዝባዊ ትግልና ሁሉን አቀፍ የሆነ፣ ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው አመራር ጉዳይ ይሆናል።

ትግሉ ዘርፈ ብዙ ይሆናል ስንል ምን ለማለት ነው? ከፍ ብለን በጠቀስነው መሰረት የግንቦትን ድሎች ለማስመለስ የሚደረገውና መደረግ ያለበት ህዝባዊ ተጋድሎ በዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች፣ በመብት ረገጣዎች ዙሪያ፣ "በድምፅ ዝርፊያ" ላይ ብቻ ያተኮረ የፖለቲካ ትግል አይሆንም። ከዚህ ይልቅ ወይም ከዚህ በተጓዳኝ ህዝባችን በቅልበሳው ሳቢያ እየተባባሱ የመጡትንና ወደፊትም እየተባባሱ የሚሄዱትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች ተቃውሞ ለተሻለ ህልውና ለትግል እንዲነሳሳ መቀስቀስ ይኖርበታል። ስራ አጡ ወጣት ለስራ፣ ተፈናቃዩ ገበሬ ማሳውን መልሶ እጁ እንዲያስገባ፣ የዋጋ መናር በኑሮ ጠርዝ ላይ ያንጠለጠለው ወዛደር ለደመወዝ ጭማሪና ለተሻለ የስራ ሁኔታ፣ በተቃዋሚነት ተፈርጆ ከስራው የተፈናቀለ የመንግስት ሰራተኛ ወደ ስራው እንዲመለስ፣ በአድልኦ ፖለቲካ ወይም እንደዚሁ በተቃዋሚነት ተፈርጆ የንግድ እንቅስቃሴውን ለማቋረጥ የተገደደው ነጋዴ ወይም ኢንቬስተር አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ስራውን ቀጥሎ ራሱንም ሃገሩንም እንዲጠቅም.......በነዚህና ሌሎች ስፍር ቁጥር በሌላቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ሁሉም ብሶቱን እንገቦ እንዲነሳ ችግሮቹን አጉልቶ በማሳየት ለቀባሪ የሚያረዳ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ችግር ለመውጣት ያለውን ህዝባዊ አማራጭ አጉልቶ የሚያሳይ አመራር ያስፈልጋል።

እንዲህ አይነቱ አመራር ሁሉም ብሶቱን እንገቦ እንዲነሳ ጥሪ ከማድረግ አልፎ መሄድና እንደ የካቲት ማለዳ ወቅት ሁሉም "ብሶትህ ብሶቴ" በሚልና "በእርዳ ተራዳ" መንፈስ በአንድ ላይ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ተጨማሪ ሃላፊነት ይጠበቅበታል። እንደዚሁ አይነቱ ህዝባዊ አመራር በዚህ መልክ የሚንቀሳቀሱት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዛሬ የሚገኙበት ከባድ ቀውስ የግንቦት አማራጮች ዝርፊያ ወጤት እንደሆኑ ተገንዝበው ማንኛውም ዘላቂነት ያለው መፍትሄ ከኢህአዴግ መንግስት ከስልጣን መወገድና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ከህዝብ ድምፅ የፈለቀና በህዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግስት እንደሆነ ተገንዝበው ለዴሞክራሲ እንዲታገሉ የመቀስቀስና ትግላቸውንም የማስተባበር ሃላፊነት የሚቀበል አመራር መሆን ይኖርበታል።

ዛሬ አገራችን ባለችበትና የህዝብ ትግል ግራ ተጋብቶ በተዳከመበት ሁኔታ ህዝባችንን "ተነስ ታገል!" ብሎ ለመጥራትና ይህ ጥሪያችን ተደማጭነት እንዲያገኝ የመጀመሪያ መጀመሪያ ተግባር ግንባር ቀደም ነኝ አመራር እሰጣለሁ የሚለው ሃይል በህብረተሰቡ ያጣውን ተአማኒነት መልሶ የመገንባት ተግባር ይሆናል። ሁለተኛ ደግሞ ይህ ግንባር ቀደም ሃይል ተደማጭነት አግኝቶ የትግል ጥሪው ቢሰምር ህዝባችን እንደገና የነብር ጭራ ጨብጦ መልሶ የሚለቅበት አደገኛ ሁኔታ እንዳይፈጠር ቀጣይነት ያለው አመራር የመገንባቱ ጉዳይ ከወዲሁ በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል እንላለን። ተአማኒነት ያለው፣ ቀጣይነት ያለው አመራር ስንል ምን ለማለት ነው?

ከጨለምተኝነትና ከትጥቅ መፍታት ጋር ግንባር ቀደም ሃይሎች በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸውን ማታለል አቁመው በህብረተሰቡ ውስጥ በቅድመ ግንቦቱና በግንቦት አፍላ ወቅት በህብረተሰቡ የነበራቸው ተአማኒነት ዛሬ እንደሌለ ጠንቅቀው መገንዘብ አለባቸው። በትግሉ አፍላ ጊዜ የነበራቸውን ተአማኒነት ያጡባቸው ምክንያቶች እዚህ ተዘርዝረው የማያልቁ በርካታ ምክንያቶች ናቸው። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል።

መጀመሪያ በግንቦት ማግስት አንስቶ በግልፅ የታየው ጉድለት ያ ህዝባችን በአፍላ ትግል ላይ እያለ በግብታዊነት ሰላማዊ ሰልፎች፣ የስራ ማቆም አድማዎች ወዘተ እያደረገ ሲሰዋ በነበረበት ወቅት ለዚህ ትግል የተቀነባበረ አመራር የሚሰጥ ሃይል ጠፍቶ ሁሉም ተራ በተራ እየተነሳ የተሰዋበት ሁኔታ ነበር። ሌላው ቀርቶ ተማሪውና ወጣቱ አንዴ ደሴ፣ አንዴ ድሬዳዋ፣ አንዴ ጎንደር፣ አንዴ አዋሳ፣ አንዴ ጅማ አንዴ አዲስ አበባ ተራ በተራ እየተነሳ ሲታገልና ሲሰዋ ከማንኛውም እለሁ ከሚል ግንባር ቀደም ሃይል ይጠበቅ የነበረውና (እይታው ካለ ብዙም አስቸጋሪ ያልነበረው) ወጣቱና ተማሪው በያለበት በአንድ ቀን እንዲነሳ ጥሪ የማድረግና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል መሪና አቀናባሪ ሃይል ብቅ አላለም። እንዲህ አይነቱ የወጣቱ የተቀነባበረ አነሳስ ምን ያህል ስነልቡናዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ እምርታ ሊሰጥ ይችል እንደነበረ እየታወቀ ይህ አለመደረጉና ትግሉን የማቀነባበሩ ተግባር ሌላው ቀርቶ በአዲስ አበባ ደረጃ እንኳን

ሲሞከር አለመታየቱ በሃገራችን ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግል ከባድ የሆነ የአመራር ክፍተት ተጠናውቶት እንደነበረ
ያሳያል። ያውም እንግዲህ የሃገራችን ወጣቶች ''የተሰበጣጠሩ አላማዎች'' አንግበው ሳይሆን የትግል አጀንዳቸው ምንም
''ዘርፈ ብዙነት'' የሌለው ለአንዲት ''የህዝቡ ድምፅ ይከበር'' ለምትለው መፈክር እንደ አንድ ሰው ቆመው ሳለ የፖለ
ቲካ መሪዎች ይህንን አለማድረጋቸውና አንዳንዴ እንዲያውም ''ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል'' እንደተባለው ''መንግስ
ትም ተቃዋሚውም ወገን ነገሮችን በጥሞና እንዲይዙ'' የሚል ይፋ ጥሪ እስከማስተጋባት መሄዳቸው ትግሉን አስተባብሮ
ለመምራት ስላላቸው ብቃት ህዝቡ ራሱን እንዲጠይቅ እንዳደረገው ግልፅ ነው።።

ሁለተኛ የተአማኒነት ችግር የሚፈልቀው በነዚሁ ቁልፍ በሆኑ የግንቦት ማግስት ወራት ህዝቡ ለመታገልና ለመ
ሰዋት ይህ ነው የማይባል ወኔ እያሳየ ሳለ ግንባር ቀደም ነን የሚሉ ሃይሎች አመራር እንሰጣለን ብለው በተግደረደሩባቸ
ው አንዳንድ አጋጣሚዎች እንኳን ለህዝቡ የትግል ወኔ የሚመጥን ቆራጥነትና ፅናት አለማሳየታቸው ህብረተሰቡ አመኔ
ታ እንዲያጣ እንዳደረገው ግልፅ ይመስለናል። ግንባር ቀደም ነን ይሉ የነበሩ ሃይሎች በዚያ ቀውጢ ጊዜ አንዴ ሰልፍ
ውጣ ብለው ጥሪ አድርገው በማግስቱ ሰልፉ ተሰርዟል ሲሉት፣ አንዴ የሙት ከተማ አድማ ቀትር ላይ አውጀው ኢህአ
ዴግ ብርክ ሲይዘውና ህዝባችን ደግሞ በአጥቂነት መንፈሱ ተመቻችቶ ለአድማው ሲዘጋጅ ማታ በቴሌቪዥን ቀርበው
''ተሰርዟል'' ብለው ሲያረዱት፣ አንዴ ለአገር አቀፍ የተወዳዳሪዎች ጉባኤ አዲስ አበባ ከተቱ ተብለው ሰባት መቶ የሚ
ጠጉ ዜጎች ከመላ ሃገሪቱ ይህንን የትግል ጥሪ አክብረው አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ ሌላው ቢቀር በወቅቱ አዲስ አበባ
እየደወልን በወተወትነው መሰረት ድንኳን ጥሎ መሰብሰብ ሲቻል ''የስብሰባ አዳራሽ ጠፋ'' ተብሎ ይህ ታሪካዊና ለትግ
ሉ አዲስና አገር አቀፍ እምርታ ሊሰጥ ይችል የነበረ ጉባኤ ተሰርዞ ታጋዩ ሁሉ አንገቱን ደፍቶ ወደ የመጣበት ሲመለስና
በዚህም ጨካኝ ኢህአዴግ ካድሬዎች አይን በመግባቱ በያለበት ሲመታ.....የዚህ ሁሉ ''የመመሪያዎች ዥዋዥዌ'' ውጤት
የትጥቅ ትግል መፍታት ብቻ ሳይሆን ይህንን ትግል እመራለሁ ባዮችም በህዝብ ፊት ተአማኒነት እንዲያጡ እንዳደረ
ጋቸው ግልፅ ይመስለናል።

ሶስተኛው የተአማኒነት መጥፋት ምክንያት በሚሰበከውና ለህዝብ በሚደረገው ''የትግል አንድነት'' ጥሪና በዚህ
አንፃር ግንባር ቀደም ነን ባዮቹን የተጠናወታቸው የህዝብ ቅስም ሰባሪ የሆነው- የመከፋፈልና የመቦጫጨቅ አባዜ ሊባ
ል ይቻላል። ዛሬ የፖለቲካ መሪ ነኝ ብሎ በየስብሰባው፣ በየሴሚናሩ፣ በየመድረኩና በየጉባኤው ስለ ''ጋራ ትግል አስፈ
ላጊነት'' የማይለፍፍ መሪ ወይም ታጋይ የለም። ደግሞ ተደጋግሞ ለህዝባችን ''እንደ አንድ ሰው ሆኖ እንዲነሳ'' ጥሪዎ
ች ይጎርፉሉ። እንዲህ አይነቱ ጥሪ እስካሁን ያልሰራው ግንባር ቀደም ነኝ ባዩ ሃይል ራሱ አስቀድሞ አንድ ሆኖ በአርአ
ያነት ከመቆም ይልቅ ሁሉም በየፊናው የሚያደርገው ጥሪ ''ከኔ ጀርባ ሆነህ'' በሚል መንፈስ ስለሚደረግ ነው። በሌላ
በኩል ደግሞ ያለው ችግር ሰፊና ዘርፈ ብዙ የሆነው የዴሞክራታይዜሽን ትግል በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ዴሞክራሲያ
ዊ ሃይሎች የጋራ ትግል መሆን ሲኖርበት የፖለቲካ ሃይሎች ጉዳይ፣ ከዚያም ዘቅጦ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ወይም አ
ንጃ አድርጎ እጅግ ጠባብ በሆነ ገፅታው የማየት ችግር አለ። ነገሩን እንደዚህ አጥብበው የሚያዩ ወገኖች እርግጥ ''ለመ
ድበለ ፓርቲ ስርአት'' እንታገላለን ይላሉ። ነገር ግን በተጨባጭ ስናየው አካሄዳቸው የትም አያደርስም እንጂ ቢሳካ እ
ንኳን የአንድ ፓርቲን አገዛዝ በአንድ ፓርቲ ተቃውሞ ለመታገል የሚሞክር በቅራኔ የተሞላ አካሄድ ነው።

ከዚህ ሁሉ ስንነሳ ተአማኒነት ያለው አመራር ልንገነባ የምንችለው ካለፉት ስህተቶች ተምረን ለዚህ ዘርፈ ብ
ዙ ተጋድሎ ከፖለቲካ ድርጅቶች-፣ ከሲቪክ ማህበራት ተወካዮች፣ ከወጣቶች፣ ከሴቶች፣ ከታዋቂ አገር ወዳድ ግለሰቦ
ች፣ ከተለያዩ የሙያ ዘርፎች፣ ከምሁራን ወዘተ የተውጣጣ የጋራ አመራር ፈጥረን በአንድነት ተነስ ለምንለው ህዝብ በ
አርአያነት የምናሳየው ሁሉን አቀፍ የሆነ አመራር ስንገነባ ብቻ ነው። ለዚያውም ደግሞ እንዲህ አይነቱን አመራር የመ
ገንባቱ ጉዳይ ለትግላችን ወሳኝ ምእራፍ ቢሆንም በቂ እንዳልሆነ ግልፅ መሆን ይኖርበታል። ተአማኒነት ያለው አመራር
ፈጥረን ህዝባችን ለትግል መልሶ ቢነሳሳ ይህ አመራር የትግሉን ቀጣይነት የሚያረጋግጥበት ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርበ
ታል።

የትግሉን ቀጣይነት እናረጋግጥ ስንል እዚህም ላይ ካለፈው ሂደታችን ከቀሰምነውና ህዝባችን ከባድ መስዋእትነ
ት እንዲገብር ካደረጉት ስህተቶች አስፈላጊውን ትምህርት በመቅሰም ነው። ይህ የአመራር ቀጣይነት ጥያቄ በየካቲት
ማግስት በተለይ እንደ መኢሶን ያሉ ተራማጅ ሃይሎች ህዝባችንን ማንቃትና ማደራጀት በሚል የተቀደሰና ትክክለኛ አላ

ማ ሲሉ ያለ የሌለ ሃይላቸውን በህጋዊው የትግል መድረክ በይፋ ሲያሰማሩ ''ችግር ቢደርስስ?'' የምትለዋን ጥያቄ ቢያን
ሱም ለቀጣዩ የትግል ምእራፍ የህቡእ መዋቅራቸውን ሁኔታው በሚጠይቀው መልክና ፍጥነት ባለማደራጀታቸው የደረሰ
ውን ጥፋት እናውቀዋለን። ዛሬም በግንቦት ማግስት የደረሰውና በመድረስ ላይ ያለው ችግር ከዚህ የተለየ አይደለም።
ግንቦትን በቀደሙት ወራት በተለይ በምርጫው ዘመቻ ወቅት በሃገራችን በነበረው በውይይት፣ በክርክር፣ በህዝባዊ ስብ
ሰባዎችና መሬት አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎች የህብረቱንም ሆነ የቅንጅት መሪዎች እንቅስቃሴ ከወዲሁ ዴሞክራሲ በሰ
ፈነባት አገር የሚደረግ ትግል ገፅታ ይዞ የተያዘው ትግል ገና እውን ለሚሆን ዴሞክራሲ እንደሆነ በቅጡ ግንዛቤ ነበረ
ማለት አይቻልም። እነዚህ መሪዎች በዘመቻው ወቅት ለኛም፣ ለኢትዮጵያ ህዝብም፣ ለአለም አቀፉ ኮሙኒቲም ሃገራ
ችን ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብ የረቀቁና የበሰሉ መሪዎች እንዳላት ያሳየውን ያህል በቀጠሉት ወራት ደግሞ ገና
ዴሞክራሲን ለማምጣት ሽብርተኛ ሊሆን ከሚችል መንግ-ስት ጋር ለሚደረገው ቀጣይ፣ ውስብስብና እልህ አስጨራሽ
ሊሆን የሚችል ትግል በቂ ዝግጅት እንዳልነበራቸው አሳይተዋል።

ትግሉ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ እንዳለን ተቆጥሮ መካሄዱ ከግንባር ቀደሙ ታጋይ የተወሰነው ክፍል ''ች
ግር ቢመጣ'' በሚል የጥንቃቄ አካሄድ ይፋ ከመውጣት ተቆጥቦ ጠንካራ የሆነ የህቡእ መዋቅር እንዳይዘረጋ፣ ሌላው ቀ
ርቶ ደጋፊው ነጋዴም ሆነ የመንግስት ሰራተኛ ሁሉ የሚያደርገው መዋጮ ደረሰኝ በስሙ እየተመዘገበ በኮምፒዩተር እ
ንዲያዝ የማድረግ አይን ያወጡ ስህተቶች ተፈፅመዋል። ይህ ራሱ በርካታ ዜጎችን ለአስከፊ አፈና ያጋለጠ ሲሆን በሌላ
በኩል ደግሞ ''ለክፉ ቀን'' ተብሎ የተዘጋጀ ህቡእ አመራር ባለመኖሩ በያለበት የታወቁ የትግሉ መሪዎች ሲገደሉ፣ ሲ
ታሰሩ፣ ሲሰደዱ ትግሉ በዚያው ልክ እንዲዝረከረክና ቀጣይነት እንዲያጣ አድርጎታል። ይህ በመሆኑም የህዝባችን ትግ
ል በሽብር ብቻ ሳይሆን በአመራር ክፍተትም የተነሳ ቅ-ስሙ እንዲሰበር ተደርጎ ዛሬ ያለንበት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ እ
ንገኛለን። ከዚህ ሁኔታ ለቀጣዩ ትግላችን የምንቀስመው ትምህርት ከፀሃይ በደራ ሁኔታ ግልፅ ይመስለናል። ከላይ ድሮ
ውንም ተአማኒነት ያለው አመራር ሳንፈጥር ካሁን ወዲያ ለህዝባችን የትግል ጥሪ እናድርግ ብንል እንዲህ አይነቱ የኛን
ም የመዝረክረክ የህዝባችንንም በጨለምተኝነት የመዋጥ ክስተት ሳያገናዝብ የሚደረግና አዳማጭ አጥቶ ተግባራዊ ሳይ
ሆን ሲቀር ደግሞ የትጥቅ መፍታቱንና የጨለምተኝነቱን ክስተት የሚያግዝ አደገኛና የአጉል ግንባር ቀደሞች አካሄድ
እንደሚሆን ግልፅ መሆን ይኖርበታል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ደግሞ ተአማኒነትን ገንብተን ህዝባችን ለትግል ጥሪያችን አ
ወንታዊ መልስ ሰጥቶ መንቀሳቀስ ቢጀምር ''አደጋ ቢደርስ'' አመራሩን የሚተካ ሌላ ህቡእ አመራር ሳንገነባ የሚወረወ
ር ማንኛውም ጥሪ ሃላፊነት የጎደለው፣ ካለፈው ምንም ትምህርት ያልቀሰመ፣ አንድ ህዝብ ታግሎ ገዥዎችን ብርክ ካስ
ያዘ በኋላ ቀጣይ ትግል ከሌለ አስከፊ ቀጣይ አፈና እንደሚጠብቀው ያልተገነዘበና ካለፈው አፈና ያላገገመውን ህዝባች
ንን ለሌላ አስከፊ የአፈና ዙር አጋልጦ የመስጠትን ያህል አደገኛ አካሄድ እንደሆነ በግልፅ መቀመጥ ያለበት ይመስለና
ል።

እንግዲህ ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው አመራር አስፈላጊነት በዚህ መልክ ካስቀመጥን ዘንዳ እንዴት እንዲህ
አይነቱን አመራር እንፍጠር የሚለው ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። በዚህ በኩል የምንሰጠው አጭር መልስ በግንቦት ህዝባ
ዊ አጀንዳ አምነው፣ ለዚህ ደግሞ ሚልዮኖችን የሚያንቀሳቅስ ህዝባዊ ትግል ያስፈልጋል ብለው የሚያምኑ የኢትዮጵያ
ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ሃይሎች ለጊዜው በሁኔታው አስገዳጅነት በውጭ አገር አንድ በቅድሚያ በጥንቃቄና ዴ
ሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ የሚዘጋጅ ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጠርተው ሰፊ ውይይት የሚያደርጉበት ጉዳይ ይሆናል ብለን እና
ምናለን።

ወደዚህ ወሳኝ ጉባኤ ለሚደረገው የጋራ ትግል አስተዋፅኦ ለማድረግ በሁኔታው አስገዳጅነት በውጭ አገር የ
ምንጠራውና ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ በሃገር ውስጥ ያሉ የተሰበጣጠሩ ሃይሎች በተዘዋዋሪ ሰነዶችም ሆነ ሌሎች ግብ
አቶች የሚያቀርቡበት መንገድ ተፈልጎ የጋራ የትግል ስትራቴጂና መዋቅር ዘርግቶ ትግሉን ፈር ለማስያዝ የሚሰራ ጉባ
ኤ ይሆናል። እርግጥ የእንዲህ አይነቱን ጉባኤ ሃሳብ ''ዋናው ትግል አገር ቤት ነው'' በሚል ማንም በማይክደው ሰበብ
ተነስተው በማጣጣል የዲያስፖራውን ሚና በስንቅ አቀባይነት ብቻ ለመወሰን የሚጥሩ ወገኖች አሉ። ይህ አይነቱ ክርክ
ር ልክ የኢህአዴግ መንግስት በአንድ በኩል በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ተሳትፎ በህገ መንግስቱ አግዶ
በሌላ በኩል ደግሞ በኢኮኖሚው መስክ ''ኑ ገንዘባችሁን ይዛችሁ ለሃገር እድገት አስተዋፅኦ አድርጉ'' እያለ ነጋ ጠባ ከ

ሚሰነዝረው ጥሪ የተለየ አይደለም። የሆነ ሆኖ ግን ይህንን ሃሳብ ለመቃወም የሚቃጣቸው ወገኖች ክርክሩን ባልተባለ
አቅጣጫ ለመውሰድ እንደሚጥሩ ግልፅ ነው። የሃገራችን የነፃነት ተጋድሎ ዋናው ሃይልና የትግሉ አምብርት እዛው ሃገ
ራችን ውስጥ እንደሆነ የሚክድ ማንም የለም። ጥያቄው በኢኮኖሚ አቅም፣ በእውቀት፣ በፖለቲካ ትግል ልምድ፣ በሃገ
ር ፍቅር በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የዳበረው በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ለዚህ ትግል አስተዋፅኦ ሊያደ
ርግ ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። መልሳችን ደግሞ የማያወላዳ "አወን ይችላል" የሚል መልስ ነው። ይህንን ካ
ልን ደግሞ ሌላ መሰረታዊ ጥያቄ ይነሳል። ይህ አስተዋፅኦ የጎለበተ የሚሆነው እንደ አሁኑ በተዘበራረቀ ሁኔታ አንዱ አ
ራምባ ሌላው ቆቦ ቢረግጥ ነው ወይስ ተሰባስቦና መክሮ በጋራ በአንድ አቅጣጫ ቢገፋ? መልሱ ግልፅ ይመስለናል። የእን
ዲህ አይነቱ አካሄድ ጠቀሜታ አይን በሚያወጣ መልክ ግልፅ በመሆኑ በውጭ ከወዲሁ በትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓር
ቲዎች፣ የሲቪክ ስብስቦች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የጋዜጠኞች ወዘተ ማህበራት የምሁራንና የታዋቂ አገር ወዳድ ተወካ
ዮች ተገናኝተው ለጋራ ትግል፣ የጋራ ስትራቴጂና አታጋይ አካል ለመፍጠር ይጣሩ የሚለውን ሃሳብ ለመቃወም እስካሁ
ን አንድ እዚህ ግባ የሚባል ምክንያት የሰጠ ዜጋ አላጋጠመኝም።

ያልነው አካሄድ "መሸጋሸግ" የሚል ነውና እንዲህ አይነቱ ጉባኤ "ተቃዋሚ ነኝ" የሚለው ሁሉ እስኪሰባሰብ
መጠበቅ የግድ የለበትም። ጊዜ ለቀልባሾቹ እንጂ ለኛ እንደማይሰራና ትግላችን ከአደገኛ ዳተኝነትም ጋር መሆኑን ተገን
ዝበን በሆነ ባልሆነ ነገር ሊያራዝሙ የሚሞክሩ ሃይሎችን ወደ ጎን ትቶ ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር ይህንን ጉባኤ ተግባ
ራዊ ለማድረግ መስራት ያስፈልጋል። ያልነው አካሄድ የህዝባዊ ሃይሎች "የመሰባሰብ" ሂደት ነውና በህዝባችን ጎን የፀ
ናን ወገኖች ቁጥራችን አነሰ የሚል ስጋት ሊኖረን አይገባም። ተሸጋሽገንና ተሰባስበን እናካሂድ የምንለው የሃገሩም፣ የት
ግሉም ባለቤት የሆኑትን ሚልዮኖችን በግልፅና ህዝባዊ አማራጭ ዙሪያ ታግሎ ለማታገል የሚሞክር አካሄድ ስለሆነ የጥ
ራትና የቁርጠኝነት እንጂ የቁጥር ችግር እንደሌለበት ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

# የሰፊው ህዝብ ድምፅ

## ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ መአከላዊ ኮሚቴ

### የተሰጠ ልዩ መግለጫ

## የት ደርሰናል? ከዚህስ?

### የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት
### ለውይይት የቀረበ ምስጢራዊ ሰነድ

## የትግል አቅጣጫችን በተጨባጭ ምን ይሁን?

ባለፈው "ህዝባዊ ሰላማዊ ትግል ስንል" በሚል መግለጫችን ህብረቱ ከእንግዲህ የሚከተለው የትግል ስልት ምን እንደሚመስል አስቀምጧል። ለሃገራችን ችግሮች ዘላቂ መፍትሄዎች ለመስጠት በሚደረገው ትግል ወሳኝ የሚሆነው ምእራፍ የኢህአዴግ መሪዎች በህዝብ ትግል ተገደው ሁሉን አቀፍ የሆነ "የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባኤ" መሰየም ጉዳይ ነው። በመሆኑም የትግላችን ስትራቴጂያዊ አላማ ይሆናል። ወደዚህም በሚደረገው የትግል ጉዞ ቁልፍ የሚሆነው ጥያቄ ህዝባችንን መልሰን እንደ ግንቦቱ የትግሉ ባለቤት ማድረግ እንደሆነ ጠቁመናል። ለዚህ ደግሞ ዛሬ ባለው ጠቅላላ የተጥቅ መፍታት አባዜ ይህንን ህዝብ ምን ክቡር ቢሆኑ በትላልቅ ሃገራዊና ዴሞክራሲያዊ ራእዮች ብቻ ለማንቀሳቀስ መሞከር ከተጨባጩ የህብረተሰባችን ሁኔታ ሳይሆን ከራሳችን ህልም የሚፈልቅ ጨርሶ የማይሰራ ስትራቴጂ እንደሚሆንም አስቀምጠናል። በእርግጥም አሁን በአጠቃላይ በተቃዋሚዉ ጎራ ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች ይልቅ ለፖለቲካውና ለተቋማት ግንባታ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥተን ታግለን ከዚያ ይህ ትግል ድል ሲያደርግ እነዚህን ችግሮች መያያዝ እንጀምራለን የሚል አዝማሚያ አለ። በዚህ "የትግል ስልት" ከተመራን ከትግሉ ሜዳ ባገለልነው ህዝብ እኛም ተረስተን ትግል እያልን መኳተን እንደምንቀጥል ግልፅ ይመስለናል።

ከየካቲት ሽንፈት በኋላ በእንደዚህ አይነቱ አካሄድ ለአመታት "ሁሉም ነገር ከደርግ በኋላ ይደረስበታል" እየተባለ የህዝባችንን የሰማይ ስባሪ የሚያክሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የኑሮ ችግሮች በይደር ትተው "ከሰማይ በራቁ" መፈክሮች ዙሪያ ሲታገሉ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ተዝረክርከው ስመ ጥፉው የለንደን ጉባኤ እንደደረሰባቸው አይተናል። ከዚያም ወዲህ አስፈላጊና የግድ በሆነው የፖለቲካ ለውጥ ትግልና በማህበራዊና ኢኮኖሚው ዘርፍ በሚደረጉት ትግሎች ሚዛናዊ ግንኙነት መፍጠር ስላልቻልን እኛም ህዝባችንም የምንመኘውን በጎ ለውጥ ለማምጣት አልተቻለም። ከዚህ ስህተት በመማር ነው ትግላችን ህዝባችንን መልሶ የትግሉ ባለቤት ማድረግ ላይ ማተኮር ይኖርበታል የምንለው። ይህንን አላማ በተግባር ለመተርጎም ከፈለግን ደግሞ ብዙ አማራጮች የሉንም። ሚልዮኖች ዛሬ ዘግናኝ የሆነ የኑሮ ቀውስ ውስጥ ቢዘፈቁ ይህ የሆነው በግንቦት 97 ከድምፃቸው ጋር ቀርበውላቸው የነበሩት በጎ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጮች ተዘርፈው የኢህአዴግ አጥፊ ፖሊሲዎች በመቀጠላቸው መሆኑን ተረድተው በፖለቲካ ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆን በነዚህ በጎ አማራጮችም ዙሪያ እንዲታገሉ መቀስቀስም ያስፈልጋል።

ይህ አካሄዳችን እንዲሰምር ከፈለግን የትግሉ አመራር በሶስት በምንም አይነት ሊነጣጠሉ በማይችሉ ቁልፍ ጥያቄዎች ዙሪያ መስራት ይኖርበታል ብለናል። አንደኛ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው ለችግራቸው መፍትሄ ለመሻት እንዲታገሉ መቀስቀስ ሁለተኛ እነዚህ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች "ብሶትህ ብሶቴ" በሚል መንፈስ በትግግዝና በአንድነት እንዲነሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ሶስተኛ ደግሞ ይህ ትግል ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ከሚደረገው ትግል ጋር ተቆራኝቶ መካሄድ እንደሚኖርበት ያለንን እምነት በተጠቀሰው ሰነዳችን ገልፀናል።

### 1. ሁሉም ብሶቱን እያነገበ እንዲንቀሳቀስ ምን እናድርግ?

ለግንቦት ድሎች እየተባለ የሚካሄደው ትግል የግንቦትን ቅልበሳ መዘዞች ለመቋቋም የሚካሄድ ትግልም መሆን ይኖርበታል። ዛሬ ህብረተሰባችን በፖለቲካውም ሆነ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ጥያቄዎች ከግንቦት በፊት ከነበረበት ይበልጥ የከፋ ሁኔታ ውስጥ በመሆኑ እየተባባሰና በየእለቱ እየተበላሸ በመሄድ ላይ ባለው የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ የተነሳ ቀውሱ ያልዳሰሰው የህብረተሰብ ክፍል አይገኝም። ከዚህ ተነስተን "ሁሉም እንደብሶቱ" ስንል የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የምንቀሰቅስበት መሳሪያችን ምንድን ነው? ህብረታችንን በሚመለከት ይህ መሳሪያ

በምርጫው ወቅት አቅርበን የነበረውና ዛሬ ''የተቀለበሰው'' አማራጭ ሰነዳችን ነው። ይህ ሰነዳችን እንደ ተራ የምርጫ
ማኒፌስቶ የራስን አማራጭ ብቻ ከማቅረብ ይልቅ እዚያው በዚያው በአንድ በኩል ''የኢህአዴግ አጥፊ ፖሊሲ ይኸ ነ
ው'' ብሎ ከዚያ በተጓዳኝ ደግሞ ''የኛ አማራጭ ደግሞ ይኸ ነው'' በሚል መንፈስ ጥንድ ይዘት እንዲኖረው ተደርጓል
። ከዚህም በተጨማሪ ሰነዱ ''ብናሸንፍ በተግባር የምንተረጉመው' ከሚል አንድ ወጥ የሆነ ስሌት ብቻ በመነሳት አልተ
ነደፈም። በዚህ ፕሮግራም ዙሪያ ተንቀሳቅሶ ኢህአዴግ በማጭበርበር አሸንፍኩ ካለ የፈቀደውን አማራጭ ለመምረጥ
መብቱን የተነፈገውና ድሉን የተቀማው ህዝባችን በነዚህ አማራጮች ዙሪያ ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል የሚል እምነ
ት ነበረን። ሶስተኛ በኛ በኩል በተለያዩ የራሳችን ችግሮችና ድክመቶች ምክንያት አላማችንን ለህዝብ ማስጨበጥ አቅ
ቶን ኢህአዴግ በሃቅ ካሸነፈ ደግሞ የሚከተላቸው አጥፊ ፖሊሲዎች የህዝባችንን ችግሮች እያባባሱ ስለሚሄዱ የህዝባ
ችን የእለት ከለት ችግሮች መፍትሄዎች እየጠቆመ ትግሉን ለመቀጠል በሚያስችል ሁኔታ የተሰናዳም ሰነድ ነበር።

በወቅቱ የነበረው አስተሳሰብ በምርጫው ማግስት ኢህአዴግ በእነዚህ አገር አውዳሚ ፖሊሲዎች ከቀጠለ በአን
ድ በኩል የነሱ አጥፊነት በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ያቀረብናቸው አማራጮች ትክክለኛነትና ህዝባዊነት እየጎሉ የሚሄዱ
በት ብሎም ህዝቡ ትግሉን አፋፍሞ ሊቀጥል የሚችልበት ክስተት ይፈጠራል የሚል ነበር። ይህ አልሆነም። ምክንያቱ
ም ግልፅ ነው። ሰነዳችንን ህዝባችን ብቻ ሳይሆን እኛም ረስተነዋል። ከዚህ ተነስተን ''ሁሉም እንደ ብሶቱ'' ስንል ሌላ
ምንም ትርጉም የለውም። የኢህአዴግን ፖሊሲዎች አጥፊነት በየእለቱ በኑሮው እያየው ላለው ህዝብ ይህንን መንግስት
በፖለቲካው መስክ ብቻ ሳይሆን በነዚህ ያኔ በምርጫው ዘመቻ ወቅት አብረን በተዋጋናቸው አጥፊ ፖሊሲዎቹም ለመ
ዋጋትና ከነዚህ ፖሊሲዎች አንፃር የኛ ምን ያህል ትክክለኛ እንደነበሩና እንደሆኑ ለማሳየት በቀላሉ ሊሰርፁ በሚችሉ የ
ቅስቀሳ ስልቶች በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መሰማራት ይኖርብናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የእይታ ጉዳይ እንጂ
ስነ ስርአትና ተከታታይነት ባለው መልክ ከተሰራ አስቸጋሪ አይሆንም።

ይህንን አባባላችንን ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግና የቅስቀሳችን አቅጣጫ ምን ይዘት እንደሚኖረው ለማሳየት
የሃገራችንን ህዝብ ከሰማንያ ከመቶ በላይ የሚመለከተውን የእርሻ ፖሊሲና አሁን የተከሰተውን አስከፊ ርሃብ ሰፋ አድ
ርገን እንመልከት። በሃገራችን መልሶ የገባውን ርሃብ እነ አቶ መለስ ዛሬም እንደ ንጉሱና ደርግ ዘመን በድርቅ በማላከክ
ብቻ አይወሰኑም። ከዚያም ተጨማሪ ሰበብም እያመጡ ናቸው። ይኸውም በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ሁኔታና በተለይ '
'በቻይናና ህንድ አገር የኑሮ ደረጃና የህዝቡ ፍጆታ ከፍ ማለት'' በተከሰተው የዋጋ መናር የሚለው አዲስ ሰበብ ነው።
ይህ ''ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይክፋሽ...'' እንደተባለው መሆኑ ነው። ''የአለም አቀፉ ኢኮኖሚ'' ሰበብ ራሱ ሊመ
ጣ የቻለው በሰነዳችን ያጋለጥናቸው ፖሊሲዎች በመቀጠላቸው እንደሆነና በዚህ የኢህአዴግ መሪዎች በያዙት አካሄድ
ደግሞ ሃገራችን ምንጊዜም ቢሆን ከርሃብ አዙሪት መውጣት እንደማትችል ማሳየት በጣም ቀላል ነገር ይመስለናል።

በአማራጭ ሰነዳችን ላይ በእርሻ ጉዳይ የኢህአዴግ ፖሊሲ በግልፅ ከተቃወምንባቸው በርካታ ምክንያቶች ሁ
ለት መሰረታዊ ሊባሉ የሚችሉና አማራጭም ያቀረብንላቸው ፖሊሲዎች አሉ። የመጀመሪያው የእርሻ ፖሊሲ ኢህአዴ
ግ በፕሮግራሙ ''በአለም ገበያ የተቃኘ'' ብሎ በግልፅ ያስቀመጠው ፀረ ገበሬና ፀረ ህዝብ ''የእድገት'' ተብየ ፖሊሲ ሲ
ሆን በኛ በኩል የቀረበው እዛው አገራችን ''አምራችና ሸማች ተያይዘው የሚያድጉበት'' የሚለው አገር ተኮር የሆነ አጠ
ቃላይ የልማት ስትራቴጂ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሃገራችንን ገበሬዎች የይዞታ ዋስትና ነስቶ መልሶ የመንግስት ብሎ
ም የመንደር ካድሬዎች ጭሰኛ ያደረገው የመሬት ስሪትና በኛ በኩል ገበሬው ከዚህ ጢሰኝነት ሙሉ በሙሉ ነፃ ለማው
ጣት የተቀየሰ አቋማችን አለ።

በማንኛውም ቅስቀሳችን ዛሬ በሃገራችን አንዳንድ ዘጋቢዎች እስከ አስራ አራት ሚልዮን የሚያደርሱት ህዝብ
ቢራብ በቅልበሳው ሳቢያ እነዚህ ሁለት አጥፊ ፖሊሲዎች እንዲያውም ተፋፍመው በመቀጠላቸው እንደሆነ ግልፅ በ
ሆነ ሁኔታ መቀመጥ ይኖርበታል ማለት ነው። እኛ የህዝብ ወገኖች ስለ ርሃብና የሰቀቀን ኑሮ ስናወራ እነ አቶ መለስ ከ
ዚሁ ከተከሰተው ርሃብ ጋር በተያያዘ ለአለም መገናኛ ብዙሃን በሚሰጧቸው ቃለ ምልልሶች በሃገራችን የእርሻ ምርት 1
0% እድገት እያሉ ሲያሾፉ እናያቸዋለን። ይህ ምን ያህል እውነት ነው? ታዲያ እንዲህ ከሆነ ህዝብ ለምን ይራባል? ለ
ዚህ ያለው መልስ ሁለት ነው። አንደኛ በዚሁ አመት የአለም ባንክ ባቀረበው ዘገባ በሃገሪቱ የነፍስ ወከፍ ምርት እንደ

ቀነሰ ያሳያል። ሁለተኛ ደግሞ የትኛው የእርሻ ምርት የሚለው ጥያቄ አለ። ይህ ደግሞ "አለም ገበያ ተኮር" ወደሚለው ፖሊሲያቸው ያመጣናል።

"የእርሻ ምርት ጨመረ" ሲባል ለተራበ ህዝባችን ፍጆታ ሳይሆን የምናወራው ለውጭ ገበያ ስለሚመረተው አበባ ከሆነ በዚህ ሴክተር የሚታየው እድገት እጅግ አስገራሚ የሚባል ነው። በአለፉት አምስት ስድስት አመታት ይህ ዘርፍ ተአምራዊ ሊባል የሚችል እድገት እያሳየ ይገኛል። በ1997 ኢ.ም. (ማለት በምርጫው አመት) ከዚህ ዘርፍ ኤክስፖርት የሚገኘው ሃያ ሚልዮን ዶላር ብቻ ሲሆን ከሁለት አመት በኋላ ሶስት መቶ ሚልየን ይጠበቅ እንደነበረ መገለፁ ይታወሳል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ደግሞ በጥቂት አመታት ውስጥ ይህ ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች አልፎ አካባቢ አውዳሚ የሆነ የኤክስፖርት ዘርፍ ከቡና ይበልጥ ገቢ እንደሚያስገኝ እየጠቆሙ ይገኛሉ። በመስከረም ወር 2007 "የኢትዮጵያ የአበባ ዘርፍ ኬንያን አልፎ ለመሄድ የሚችልበት ሁኔታ እየተከሰተ ነው" በሚል ርእስ " ዘ ኢስት አፍሪካን" የተባለ የናይሮቢ ጋዜጣ በአንድ አመት ውስጥ የአበባ ኤክስፖርት በ500% ማደጉን ዘግቧል።

"በአለም ገበያ የተቃኘ" የሚለው የኢህአዴግ የእርሻ ፖሊሲ በዚህ መልክ በመቶ ሽህዎች ሄክታር የሚቆጠር ለም መሬት ለአውሮፓ አበባ ያውላል። ከዚህ በተጨማሪ ለአግሮ ፍዌል እየተባለ እየተቸበቸበ ያለው ለም የእርሻ መሬት አንድ ፀረ ግሎባላይዜሽን የሆነ አውሮዳዊ እንዳለው "ከደቡብ ህዝቦች አፍ ነጥቆ የአውሮዳን መኪናዎች ለመመገብ" የሚሰራ ግፈኛና አጥፊ አካሄድ እንደሆነ ግልፅ ነው። የኢህአዴግ መሪዎች ይህንኑ የጥፋት ሎጂክ በመከተል አሁን ደግሞ "የእሷ እያረረባት የሰው ታምሳለች" እንደተባለው የነሳውዲ አረብያንና የነጂቡቲን "የምግብ ዋስትና" (ፉድ ሴኩሪቲ) ለማረጋገጥ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ነው። ሌላው ቀርቶ የተባበሩት መንግስታት የምግብና የእርሻ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ሴኔጋላዊውና በግራ አክራሪነት "ታምተው" የማያውቁት ዣክ ድዩፍ ሳይቀሩ "የእርሻ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ" (ኒኦ ኮሎንያሊዝም) ብለው በጠሩት ክስተት ሳቢያ እነዚህ አገሮች ለራሳቸው ፍጆታ የሚሆነውን ምግብ እኛ አገር እያመረቱ ወደ ሃገራቸው ለመጫን መሬት እየተሰጣቸው ነው።

ከሃገራችን የእርሻ ችግሮች አንዱ የእያንዳንዱ ገበሬ ቤተሰብ ማሳ ከአመት አመት እየሟሸሸ አንድን ቤተሰብ ከአመት አመት ለመመገብ አልበቃ እያለች በመሄዷ እንደሆነ ይታወቃል። ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር ጥናቶች እንደሚታየው በሃገራችን የአንድ ገበሬ ቤተሰብ ማሳ አማካኝ ስፋት 1.02 ሄክታር ነው። ለዚያውም ይህ አማካኝ ተባለ እንጂ ከሃገራችን ገበሬዎች 37.6% ደግሞ የሚያርሱት ማሳ 0.38 ሄክታር እንደሆነ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር ጥናቶችና ሌሎች በርካታ ሪፖርቶች ይገልፃሉ። ከዚህ አልፎ ተርፎ 11% ጨርሶ መሬት የሌላቸው ናቸው።

የሃገራችን አርሶ አደሮች ያሉበት እንዲህ አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ መሆኑ እየታወቀ መለስ ዜናዊ በሃምሌ አጋማሽ ላይ "መሬት ለመመራት" ሃገራችን ለመጡ የሳውዲ አረብያ ልኡካን "በመቶ ሽዎች ሄክታር የሚለካ የእርሻ መሬት ልንሰጣቸው ዝግጁ (ኢ.ገ) መሆናችንን ገልፀንላቸዋል።" እስከ ማለት መሄዱን ፋይናንሻል ታይምስ 21/08/08 እትሙ ዘግቧል። በዚህ ጉዳይ በርካታ ኤክስፐርቶች ከፍተኛ ስጋት እንዳላቸው ሲገልፁ አንዱ የተመድ ኤክስፐርት ህዝብ እየተራበ "ሌሎች በዚች አገር ምድር ላይ አምርተው እህል ሲያግዙ ሲታዩ" ሊፈጥር ስለሚችለው አደጋ ያለውን ስጋት ገልጿል። በዚህ "ኤክስፖርት ኦርየንትድ" በሚሉት አደገኛ ፈሊጥ የተነሳ የሚከሰተው ችግር በርካታ አራሾች ከመሬታቸው እየተፈናቀሉ ለጅብ መሰጠታቸው ብቻ አይደለም። ለሃገር ምግብ ፍጆታ የሚመረተው እየቀነሰ ሲሄድ የዋጋ መናር የሸማቹን ህዝብ ኑሮ የሚያናጋም እንደሆነ ግልፅ ነው። በዘንድሮው ርሃብ ሳቢያ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የታዛቢዎችን ትኩረት የሳበው በቀደሙት አመታት ቢከፋም ቢለማም በቀን ሶስቴ በልቶ ያድር የነበረው ከተሜ አሁን ከነልጆቹ የመራቡና በአጠቃላይ የከተማ ድሆች (Urban Poor) መበራከት የዚህ ውልግድግድ ፖሊሲ ውጤት መሆኑ የሚካድ አይደለም። እነ አቶ መለስ የአዳን መሬት ለአበባ ለባእዳን ቸብችበው ስለጤፍ መወደድ ሲያወሩን ይህ ሁሉ የዚህ ፖሊሲያቸው ውጤት እንደሆነ አይገነዘቡም ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ባይገነዘቡም ሃቁን አፍረጥርጦ ለህዝባችን መናገር የኛ ፈንታ ይሆናል።.

የሃገራችን ችግሮች ሁሉም የተያያዙ እንደ መሆናቸው መጠን ይህ "መሬታችንን ለውጭ ገበያ ለማምረት" የሚለው ፖሊሲ በሰነዳችን ላይ ካወገዝነው ግፈኛ የመሬት ስሪት ጋር የተያያዘ ነው። ከአራት አመታት በፊት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር የተካሄደ አንድ ጥናት "መሬት ለአራሹ" ተብሎ ስንት መስዋእት የጠየቀ ትግል በተካሄደባት

አገራችን ከየካቲት የመሬት አዋጅ ሰላሳ አመት በኋላም ከሃገራችን ገበሬዎች 84% ያህሉ መሬት የነሱ የአራሾቹ ሳይሆን የመንግስት ነው ብለው እንደሚያምኑ አሳይቷል። ከዚህም እምነት በመነሳት 76% ያህሉ ዋና ጭንቀታቸው "የያዙት ማሳ የዛሬ አምስት አመት የነሱ ሆኖ መቀጠሉን ወይም አለመቀጠሉ እርግጠኞች አለመሆናቸው" እንደሆነ ይጠቁማል። በሰሞኑ የርሃብ ዙር በተደጋጋሚ እንደ ምክንያት ሆኖ በራሳቸው በገበሬዎች የሚነሳው ጉዳይ ይህ የመሬት ይዞታ ዋስትና ጉዳይ ነው። የሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጠኛ አገስት 5 ቀን ባወጣው እትሙ በዚህ ጉዳይ አንድ ገበሬ ጠቅሶ እንዳለው "መንግስት በፈለገው ጊዜ መሬቴን የሚቀማኝ ከሆነ ተግቶና ለፍቶ መስራት ምን ዋጋ አለው?" በማለት በምሬት እንደተናገረ አስፍሯል።

በኛ በኩል ግልፅ የሆነና የገበሬውን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን ማሳውን እንዲያሻሽል፣ ዛፍ ተክሎ አስከፊ የሆነውን የጫካ ምንጠራና ተከታዩን የአካባቢ ውድመት እንዲዋጋ፣ ከኢህአዴግ የመንደር ካድሬዎች የፖለቲካ ቁጥጥር ነፃ በሆነ ሁኔታ እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ሳይሆኑ በመሬቱ ላይ አራሹ ራሱ የሚወስንበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል ብለን ታግለናል። ከግንቦት 97 በፊት በውጭ አሳዳሪዎቻው ግፊትም ሆነ የገበሬውን ድጋፍ ለማግኘት በያዝ ለቀቅ ተጀምሮ የነበረው የይዞታ ሰርቲፊኬት ለገበሬው የማደል ጉዳይ ዛሬ ጨርሶ አይነሳም። እንዲያውም ኢህአዴግ በዚህ አጥፊ ፖሊሲ ቀጥሎ ተቃዋሚ ደግፋችሁ ነበር የተባሉ ገበሬዎችን ከመሬታቸው በገፍ እየነቀለ እንደሆነ ሂውማን ራይትስ ዎች ባለፈው አመት አጋልጧል። በየመንደሩ ገበሬዎች በዚህ መልክ የተቃዋሚ ደጋፊዎች እየተባሉ ከማሳቸው ሲፈናቀሉ በጠቅላላው "ይህንን አይተህ ተቀጣ..." እየተባለ ማስጠንቀቂያ በሚደርሰው በአካባቢው ገበሬ ላይ የሚነዛው ሽብርና አለመረጋጋት ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት አስቸጋሪ አይመስለንም።

የሆነ ሆኖ ይህ የኢህአዴግ ፖሊሲ ገበሬውን በፖለቲካ ቁጥጥሩ ስር ለማዋል ብቻ የተቀየሰ አይደለም። በኢኮኖሚውም መስክ የሄድን እንደሆነ "አለም ገበያ ተኮሩ" የእርሻ ፖሊሲ እንዲሰራ ከተፈለገ የይዞታ ዋስትና ያልተረጋገጠበት፣ በዘፈቀደ የሚሰራ ሙሰኛ ስርአት ያስፈልገዋል። ከፍ ብለን የጠቀስነው ፋይናንሻል ታይምስ የተያዘው የባእዳን ለመሬት የመራኮት ሂደት በመፈፀም ላይ ያለው "የህግ የበላይነት እጅግ ደካማ በሆነባቸውና ገበሬዎች የይዞታ ዋስትና በተነፈጉባቸው አገሮች" እንደሆነ አብራርቷል። "
የኢህአዴግ መንግስትና የየአካባቢው ባለስልጣናት መለስ እንዳለው "በመቶ ሽዎች ሄክታር የሚቆጠር የእርሻ መሬት" ለውጭ ገበያ ምርት እንዲውል ወይም ለባእዳን እንዲቸበቸብ ከፈለጉ መንግስት የሃገሪቱ መሬት ብቸኛ ባለቤት ሆኖ የፈለገውን ማሳ ለፈለገው ባእድም ሆነ አገር በቀል አምራች ለመስጠት ገበሬውን የማፈናቀል "መብቱን" መጠበቅ ይኖርበታል ማለት ነው።

ይህንን ሁሉ በዚህ መልክ በሰፊው ማውሳት ያስፈለገው እይታ ቀይረን ትግላችንን በህዝባችን ተጨባጭ ችግሮችና ባሉን አማራጭ መፍትሄዎች ላይ እንዲያተኩር ካደረግን ህዝባችንን ይዘን ለመታገል ማለቂያ የሌላቸው ተጨባጭ የትግል መፈክሮች እንዳሉ ለማሳየት ነው። በዚህ መልክ ገበሬውን እንደምንቀሰቅስ ሁሉ እንደዚሁ ከፕሮግራማችን እየተነሳን ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች - ለስራ አጡ፣ ለተማሪው፣ ለነጋዴው፣ ለሰራተኛው፣ ለኢንቬስተሩ፣ ለጅምላ ድህነት ለተጋለጠውና ከዚህ ርሃብ ጋር ተያይዞ አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ቁጥሩ እያደገ ለሚሄደው 'ድሃ ከተሜ' (Urban Poor) ወዘተ....ተጨባጭ ሃቆች ላይ የሚመረኮዙ አማራጭ አዘል ቅስቀሳዎች ማካሄድ እንችላለን። ነገር ግን ይህ በራሱ ከእስካሁኑ የተቃዋሚዎች አካሄድ ለየት ያለ አወንታዊ እርምጃ ቢሆንም ብቻውን በቂ አይሆንም። በዚህ መልክ የምናካሂደው ቅስቀሳ አንደኛ ለሁሉም ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስና ሁለተኛ ደግሞ በሁለቱ የስትራቴጂያችን ሌሎች ዘርፎች ማለትም ሁሉም ከግል ብሶቱ ብቻ ሳይሆን በትግግዝ መንፈስና ለፖለቲካ ለውጥ "ይቻላል" ብሎ ተነሳስቶ በአንድ አቅጣጫ እንዲገፋ ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታና ካለን አቅም የሚመጥን ስትራቴጂ ያስፈልገናል።

### 2. "እንቀሳቃሽ" ሃይሎች ላይ ማተኮር አስፈላጊነት

ባለፉት አመታት በርካታ የትግል ጥሪዎች ስናስተጋባ ቆይተናል። በህብረታችን ደረጃ እንኳን ደግመን ደጋግመን "የትግል አንድነት ጥሪ" "አስቸኳይ ጥሪ" ወዘተ እያልን ብዙ መግለጫዎች አውጥተናል፤ ብዙ ገለጣዎች አድርገናል

። ነገር ግን እስካሁን እንደሚታየው ከሆነ እንኳን ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው በጋራ ሊነሱ ቀርቶ ተማሪውንና ወጣቱን በአንድ ቀንና በአንድ መፈክር ከዳር እስከዳር በሃገሪቱ ከዚያም ወረድ ብለን በአዲስ አበባ ደረጃ እንኳን ቢሆን ሁሉም በአንድ ላይ እንዲነሳ ማድረግ የተቻለ አይመስልም። ይህ የሚያሳየን አንድ ቁም ነገር ነው። አመራር መስጠት ማለት ጥሪ ከመወርወር አልፎ ከፍ ብለን የጠቀስናቸው የተሰበጣጠሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በተቀነባበረና በተደራጀ መልክ ተሰማርተው እነዚህ ክፍሎች ለትግል እንዲነሳሱ ጥንቃቄ በተመሳበት - ማለትም ዛሬ ባለው በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አስገዳጅነት በህቡእ - ድርጅታዊ ስራ የሚሰሩ ጥቂትም ቢሆኑ የተዋቀሩ ዜጎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው። ከዚህ ግንዛቤ ከተነሳን መከተል የሚኖርብንን አካሄድ በአጭር በአጭሩ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል።

መጀመሪያ የቅስቀሳ ርእሶቻችን ወይም ቴሞቻችን በተቻለ ተጨባጭ፣ ግልፅና ማራኪ እንዲሆኑ ታስበው በየህብረተሰቡ ክፍል ያሉትን ችግሮች አብጠርጥረው በሚያውቁ ''ውስጥ አዋቂ'' ዜጎች (ወይንም በነሱ ትብብር) ካልተሰሩ እንደ እስካሁኑ የደፈና ቅስቀሳዎች የመሆናቸው አደጋ አለ። ስለዚህ ከፍ ብለን በጠቀስናቸው የተሰበጣጠሩ የህብረተሰባችን ችግሮች ዙሪያ በጉዳዩ በመያድ መልክ የተሰማሩ ዜጎች በቅስቀሳው ጥረት የሚገቡበት ወይም ደግሞ አብዛኞቹ የየራሳቸው ድረ ገፆች ስላሏቸው ከነዚህ በኛው ጥረት በምናገኛው ጭብጦች ወይም ደግሞ በውጭ ሆነው በአለም አቀፍ ድርጅቶችም ሆነ በሌሎች መስኮች በነዚህ ችግሮችና በመፍትሄዎቻው ላይ የዳበረ እውቀት ያላቸው ዜጎች ትብብር የሚገኝበት ዘዴ ሆን ተብሎ ሊፈለግ ይገባል።

ሁለተኛ በዚህ መልክ ለየህብረተሰቡ ክፍሎች የምናደርገው ጥሪ ምን ያህል ተጨባጭ ቢሆን ወደእነሱ ደርሶ የትግል ቀስቃሽ መሳሪያ እንዲሆን የኛ ጥረት ብቻ ይበቃል ማለት አይቻልም። አንደኛ ራሱ ቅስቀሳው በቀላል ቋንቋ በነዚህ ክፍሎች እንዲደርስ ሁለተኛ ደግሞ እነዚህ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በቅስቀሳው ተደፋፍረው ወደ ትግሉ ''ይቻላል'' ብለው እንዲገቡ የእንቅስቃሴ እምርታ የሚፈጥር ግንባር ቀደም አንቀሳቃሽ ሃይል መፍጠሩ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ይህ ''አንቀሳቃሽ ሃይል'' ሌላ ምንም ሳይሆን እስካሁን ድረስ በሃገር ውስጥ ወጣቱንና ተማሪውን ጨምሮ ''የህዝብ ድምፅ ይከበር'' ''ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ይኑር'' ''ነፃው ፕሬስ አይታፈን'' ''የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ'' እያለ አሁን የቀዘቀዘውን ትግል በግንባር ቀደምነት ሲያካሂድ የነበረው ሃይል ስለሆነ ከዚህ ውስጥ በሙሉ እንኳን ባይቻል የተቻለውን ያህል መልሶ በህቡእም ቢሆን ማደራጀት ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሶስተኛ በኛ ግምት ለእነዚህ ''አንቀሳቃሽ'' ሃይሎች በተለይም የተማሪውና ወጣቱ ሚና ሃሳቦቹን በማስፋፋት ላይወሰን ይችላል። እነዚህ ግንባር ቀደም ሃይሎች ከዚህ አልፈው ህብረተሰቡ ተበራቶና እምነት አድሮበት በሙሉ ልብ ከትግሉ እንዲደባለቅ በነዚህ ተጨባጭና ህዝባዊ የተቃውሞ መፈክሮች ዙሪያ እምርታ ለመፍጠር የሚችሉ ተጨባጭ እንቅስቃሴዎች በግንባር ቀደምነት ሊጀምሩና መላውን የህብረተሰብ እንቅስቃሴ ሳይጠብቁ ''ለኳሽ'' የተቃውሞ እርምጃዎች ሊጀምሩ የሚችሉ ሃይሎች ሆነው መታየት ይኖርባቸዋል።

አራተኛ ይ-ህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠብቀንም ድርጅታዊ ስራ ግልፅ ይመስለናል። ከፍ ብሎ በጠቅላላው በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ጥሪያችንን የሚያስተጋቡና ወደ ተግባር የሚገፋፉ ዜጎች በህቡእ ማደራጀት አለብን እንደተባለው ሁሉ በተማሪው፣ በወጣቱና በነጋዴው፣ በታክሲ ነጅው፣ በሰራተኛው፣ በሴቶችና በሌላው ዴሞክራሲያዊ ሃይል አካባቢ በጣም ጥቂትም ቢሆኑ ቆራጥና ''የኛ'' የምንላቸው በህቡእ የተደራጁ ዜጎች ያስፈልጉናል ማለት ነው።

## የቅድመ ምርጫና ድህረ ምርጫ ትግላችን በውስጥና በውጭ እንዴት ይሁን?

**አንደኛ በቅድመ ምርጫው ወቅት - በውስጥና በውጭ**

1. በደንብ መገንዘብ ያለብንና ህዝባችንም እንዲገነዘበው ማድረግ ያለብን በምርጫው ዘመቻ ወቅት የሚቀርቡት አማራጮች በምርጫ ውጤት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉበት ምንም ተአምር እንደሌለ ነው። የሃገራችን ገበሬ በማሳው ላይ የይዞታ ዋስትና ይፈልጋል። ስራ አጡ ወጣት ስራ ይፈልጋል። ነጋዴው ያለ አንዳች አድልኦ ነግዶ መኖር፣ ኢንቬስተሩ ያለ አንዳች ስጋት ኢንቬስት አድርጎ መበልፀግ ይፈልጋል። ነገር ግን መሬት ለአራሹ አልን፣ ላንድ ግራብን ተቃወምን፣ ስራ ለስራ አጡ አልን ወዘተ እነዚህ ጥያቄዎች ዛሬም እናቀርባቸዋለን፣ በቀጣዩ ምርጫ 2007ት እናቀርባቸዋለን ግን የትም አያደርሱንም። ለምሳሌ ባለፈው ምርጫ 97 ያቀረብናቸው በጎ አማራጮች ነበሩ። "ተሸንፈን" በተግባር አልዋሉም። ይህ ብቻ አይደለም። የወያኔ አጥፊ ፖሊሲዎች በመቀጠላቸው ከአመት አመት የባሰ ችግርና ቀውስ ተከተለ። ዛሬ እንዲያውም የምናየው የመሬት ችብቸባ አዲስ የጥፋት ፖሊሲ ያኔ ያልነበረ ነው። ነገም ማለትም እስከ ምርጫ 2007 በሚኖረው ጊዜ ሁኔታዎች እየተባባሱ ሌሎች አጥፊ ፖሊሲዎች እየተከሰቱ ይሄዳሉ እንጂ የተለየ ነገር አይመጣም። በመሆኑም ለህዝባችን አማራጮች ስናቀርብ እነዚህ በየአምስት አመቱ በሚደረጉ ምርጫ ተብየ ግርግሮች እንደማይሆን ብቻ ሳይሆን የወያኔ ፖሊሲዎች ከቀጠሉ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በአካባቢ ውድመት እየተባባሱ የሚሄዱት ቀውሶች ከዚህ በፊት እንደተባለው ሃገራችንን እንደ ሃገር ህዝባችንን እንደ ሰብአዊ ፍጡር ህልውናቸውን የሚፈታተኑ እንደሚሆኑ ማስረገጥ ያስፈልጋል።

2. ነገሮች በምርጫ አይሆኑም የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ለህዝባችን ለማስጨበጥ ምንም ችግር የለውም። እንዲያውም ከእለት እለት በመንደር ካድሬዎች ግፍ የሚሰቃየው ህዝባችን በተጨባጭ በሜዳው ያለውን ሁኔታ እኛ ልንገምተው ከምንችለው በላይ ጠንቅቆ ያውቀዋል። በመሬት ጥያቄ ለምሳሌ የይዞታ ዋስትናውን የሚያረጋግጥለት አማራጭ ቀርቦለት የምርጫው ውጤት ሲመጣና ገበሬው "የለም ይኸው አሁን ያለው የመንደር ካድሬ ጢሰኝነቴ ይሻለኛል" ብሎ ከፅድቅ ይልቅ ኩነኔን እንዳልመረጠ ጠን-ቅቆ ያውቀዋል። ምርጫው የተጭበረበረ ለመሆኑ ከዚህ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገውም። ዋናው ችግር ከዚያስ? የሚለውን ጥያቄ የመመለስ ችግር ነው። ዋናው ጥያቄ እኛ ከዚህ በምርጫ አይሆንም ከሚለው አቋም ተነስተን ከዚህ ለሚፈልቀው ትግል የሚመጥን ሃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ይኖረናል ወይ የሚለው እንጂ ህዝባችን ለትግል ሊነሳሳ ይችላል ወይ የሚለው አይሆንም። ይህንን ካልን በኋላ ደግሞ ተአማኒነት ያለው የትግል ስትራቴጂና አመራር ፈጥረን አማራጭ ካላቀረብን የህዝባችንን የተስፋ መቁረጥና የትጥቅ መፍታት ሂደት ከማገዝ ሌላ የምንፈይደው ነገር የለም።

3. አመራር ስንል? ብቻህን አይደለህም። እንዳንተው ባለው ግፍ የተንገፈገፉ ሚልዮኖች አሉ። ትግላችንን አስተባብረንና አስተጋግዘን በአንድ አቅ-ጣጫ መግፋት ከቻልን እነዚህን በምርጫ ያልተሳኩና ምንጊዜም ቢሆን የማይሳኩ አማራጮች ፋይዳ ቢስ በሚሆኑት ቀጣይ ምርጫዎች ሳይሆን በትግል እውን ማድረግ እንችላለን የሚል መልእክት ማስተላለፍ ይኖርብናል። ዋናው ችግር በኛ በኩል እነዚህን ሚልዮኖች አስተጋግዞና አስተባብ-ሮ የሚመራ ተአማኒነት ያለው ሃይል የመፍጠሩ ችግር ነው። የዚህን አማኒነት ያለው አመራር ደግሞ የመጣ አፈና ቢመጣ ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ካልቻልን ህዝባችንን እንደገና ለትግል ቀስቅሰን እንደገና ለማስመታት ከሆነ መጀመሪያውኑ የትግል ጥሪ አለማስተላለፉ ይመረጣል። ምክንያቱም ይህ ከሆነ እንደ ገና ለረጅም ጊዜ ህብረተሰቡን የተስፋ መቁረጥ ባህር ውስጥ መጨመር ይሆናልና። በዚህ ከተስማማን በቅድመ ምርጫውና በምርጫ ዘመቻው ወቅት ከዚያም ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ስለሚጠብቀን ተግባር ግልፅ የሆነ ስእል ይኖረናል።

4. በቅድመ ምርጫው ወቅት በህዝባዊ ትግል እንጂ ዛሬም፣ 2007ትም፣ 2012ትም በአጭሩ እስከ ወዲያኛው በምርጫ ሂደት ካልን ህልም ሆነው የሚቀሩትን ህዝባዊ አማራጮች ግልፅ በሆነ መልክ ለህዝባችን ማቅረብ ይኖርብናል። የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ከቻሉ እንደ ምርጫ 2002 ስነምግባርን አክብሮ በሰከነ ሁኔታ በሚካሄድ ምርጫ፣ ይህ ካልተሳካ ደግሞ ሌላው ቢቀር በውጭ አሳዳሪዎቻቸው ፊት መጋለጥን መርጠው እንደ ምርጫ 97 በለየለት አመፅ ተሰማርተው "አሸነፍን" እያሉ መቀጠላቸው አይቀሬ ነው። በመሆኑም አማራጭ ስናቀርብ አካሄዳችን ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ቢሆን "በትግል እንጂ በምርጫ እውን አይሆኑም" ከሚለው ሌላው የቅስቀሳችን ዘርፍ ተገንጥሎ መታየት የለበትም

። ከዚህ ስንነሳ በሃገር ውስጥ በትግል ላይ ያሉ ህጋዊ ድርጅቶች በምርጫው ሂደት ሲሳተፉ አንዳንዶቹ "ይኸው የምና ቀርብልህ አማራጭ። ምረጠንና የመንግስት ለውጥ ተደርጎ እነዚህን እውን እናደርግልሃለን።" በሚል አጉል ቅስቀሳ እን ደሚሰማሩ ከወዲሁ እያየነው ነው። በእኛ በኩል ተሳትፎ ለቀጣዩ ትግል ሁኔታዎችን እንዲያመቻችልን ከፈለግን ይህን ን አጉል ቅስቀሳ አጋልጠን እነዚህ ሁሉ በምርጫ ፈፅሞ አይታሰቡም በሚለው ዙሪያ የተቃኘ ቅስቀሳ ማድረግ ይጠበቅ ብናል።

6. እኛ እንደ ህብረት በአንድ በኩል በሃገር ቤት ውስጥ በሚካሄደው ዘመቻ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ የምንሳ ተፍበት ቀዳዳ እንዳለ መርምረን በዚህ ለመጠቀም መሞከር ይኖርብናል። ይህም ማለት አንደኛ በህጋዊ መስክ ተሰማር ተው በምርጫው ዘመቻ ከሚሳተፉት መሃከል የዚህን ሂደት ነፃና ፍትሃዊ አለመሆን እየጠቀሙ ይህም ሆኖ አማራጭ እ ያቀረቡ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ከዲያስፖራው ድጋፍ እንዲያገኙ የተቻለውን መስራት። ሁለተኛ ደግሞ በቀጥታ በሂደቱ ለመሳተፍ "በህዝባዊ ትግል እንጂ በምርጫ እውን የማይሆኑት አማራጮቻችን" በሚል መልክ ለምርጫ 97 አቅርበናቸ ው ከነበሩት አማራጮች ተነስተንና ዋና ዋናዎቹን በሬዙሜ መልክ አቅርበን በጣም አጭር የሆነች ሰነድ አሰናድቶ በሃገ ር ውስጥ በህቡእ የሚበተንበት ሁኔታ እንዳለ (የይቻላል ልዩ እትም ሊሆን ይችላል) መመርመር።

7. በውጭ አገር ደግሞ ከሌሎች ወገኖች ጋር በመተባበር በሰፊው ተንቀሳቅሶ ካስፈለገም ለጊዜው በዚሁ በምር ጫ ጉዳይ የሚንቀሳቀስ የጋራ ግብረ ሃይል ፈጥረን ይህንን ቧልት በአለም አቀፍ ደረጃ በተቀነባበር ዘመቻ ማጋለጥ ይጠ በቅብናል። ። Free Elections under a regime on the Stalinist side of History? No we can't! በምትል አጭር መፈክር ስር በስታሊናዊ ስርአት ስር ያሉትን ህገ መንግስታዊና የፖለቲካ እንቅፋቶች በመጥቀስ ወይም ደግሞ ከዚህ በመነሳት በተለይ የግንቦት 97ን ልምድ እየጠቀስን No They Can't! በሚል መፈክር የኢህአዴግ መሪዎች እንዴትና ለምን ነፃ ምርጫ ማካሄድ እንደማይችሉ የሚያብራራ ዘመቻ ማካሄድ እንችላለን።

## ሁለተኛ በድህረ ምርጫው ወቅት በውስጥና በውጭ

በኛ ግምት ዋናው የትግላችን ትኩረት ይኸ መሆን ይኖርበታል። እንደ ግንቦት 97 ማግስት "ምርጫው ተጭበ ርብሯል። የህዝብ ድምፅ ይከበር..." ወዘተ በሚለው ዙሪያ መንቀሳቀስ እስከዚህም የሚያዋጣ አይሆንም። ይህንን እንደ ው ለሪከርዱ ሲባል በአንዲት መግለጫ አጋልጦ በነዚህ በምርጫው ዘመቻ ሳቢያ መልሰው በህዝባችን እእምሮ መሰረፅ በጀመሩ አማራጮችና መባባሳቸው አይቀሬ በሚሆነው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውሶች ዙሪያ ትግሉን ለመቀጠል ዝግ ጅት ማድረግ ይኖርብናል። በውጭ? በምርጫው ሳቢያ አንድ የሆነ ኮአሊሽን ከፈጠርን ያንን አጠናክሮና ለአዲሱ የትግ ል አጀንዳ በሚያመች መልክ አዋቅሮ ለመታገል መሞከር። በውስጥ ደግሞ በህቡእ ስራና በተለይ "አንቀሳቃሽ ሃይሎች " ብለን የጠራናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ዙሪያ የተቀነባበረ ስራ መስራት። ትልቁና ለመመለስ አስቸጋሪ የሆነው ሰፊ ውይይት የሚያስፈልገው ይኸኛው የትግላችን ዘርፍ ነው።